# አማርኛ
# እንደሁለተኛ ቋንቋ
# የተማሪ መጽሐፍ
# ሰባተኛ ክፍል


**አዘጋጆችና አርታኢዎች**

ሰሎሞን ዮሃንስ MA (አማርኛን በማስተማር)

ትዝታ ይርጉ MA (አማርኛን በማስተማር)

ነገሰ ገብረጻዲቅ MA (አማርኛን በማስተማር)

አዕምሮ ተፈሪ MA (ስርዓተ ት/ትና ጥራት ቁጥጥር)

**ያስገመገመና ያጠናቀቀ**

ነገሰ ገብረጻዲቅ MA (አማርኛን በማስተማር)

**የቡድን (ፓናል) መሪ**

መኩሪያ ላንቃሞ (BA)

**አማካሪ**

ሂሩት አምሃ MA (አማርኛን በማስተማር)

**ዲዛይነር**

አዲሱ አና (BSC)

**ሰዓሊ**

መሰለ በርሄ (BA)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ምክረ ሐሳብ መሰረት በኢፌዲሪ ትምህርት ሚንስቴር ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍት ማዘጋጃ ሰነዶችን መነሻ በማድረግ በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ ሲሆን የዝግጅትና የሕትመት ወጪው በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስትና በኢፌዲሪ ትምህርት ሚንስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ማረጋገጫ ፕሮግራም-ኢ/ GEQIP-E/ ተሸፍኖአል፡፡

በመሆኑም የመጽሐፉን ዝግጅት በገንዘብ፣ በሰው ሃይልና በማቴሪያል፣ ተፈላጊውን መረጃ በመስጠት፣ ተቋማቸውን በመፍቀድ፣ ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን በማጋራት እንዲሁም ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለደገፉ አካላት፣ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ ትምህርት ቢሮው ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

## © የቅጂ መብት

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የአዲስ አበባ አስተዳደርና የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ናቸው፡፡
© 2014፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የቅጂ መብት ሙሉ የተከበረ ነው፡፡ ያለፈቃድ ማተም፣ ማባዛት፣ ባልተገባ መንገድ ማከማቸትና በሃርድ ኮፒም ሆነ በሶፍት ኮፒ ማሰረጨት እንዲሁም ላልተገባ ዓላማ መጠቀም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብሊክ፤ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 410/2004 ቅጂ መብት እና ጥበቃ ደንብ መሰረት ያስቀጣል፡፡

የመጀምሪያ እትም 2016 ዓ.ም
ሲዳማ/ ሃዋሳ

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


መግቢያ I

ምዕራፍ አንድ 1

የሃገር ፍቅር

ምዕራፍ ሁለት 11

የስራ ባህል

ምዕራፍ ሶስት 30

ኤች አይ ቪና መተላለፊያ መንገዶቹ

ምዕራፍ አራት 44

ወጣትነትና ሱሰኝነት

ምዕራፍ አምስት 60

የስደት አስከፊነት

ምዕራፍ ስድስት 77

የሲዳማ ባህላዊ ቤት አሰራር

ምዕራፍ ሰባት 99

ግብር (ታክስ)

ምዕራፍ ስምንት 117

የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂ

ምዕራፍ ዘጠኝ 131

የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት

ምዕራፍ አስር 140

ስርዓተ ፆታ

ዋቢ ጽሁፎች 151

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት፣ የኢትዮጵያን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል አዲስ የትምህርት ስርዓት ነድፎ በተግባር እንዲውል አድርጓል፡፡ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ላይ ተመስርቶ በክልሉ የመማሪያና የማስተማሪያ መጻህፍት እንዲዘጋጁ አድርጓል፡፡ ይህ መጽሐፍ የዚህ ጥረት ውጤት ነው፡፡

የሃገሪቱ የትምህርት ስርዓት ለውጥ እንዲደረግ ካስገደዱ መሰረታውያን ጉዳዮች አንዱ የኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት መቀነሱ ነው፡፡ ትምህርትን ለማዳረስ ብርቱ ጥረት ቢደረግም በአንጻሩ የጥራት ጉዳይ ግን ችግር እንደሆነ ቀርቷል፡፡ አዲሱ የትምህርት ስርአት ይህን ክፍተት ለመሙላት በጥራት ላይ ያተኩራል፡፡ የጥራቱ አንዱ መገለጫ፣ በተማሩበት የሙያ መስክና ከዚያም በሰፋ መልኩ ውጤታማ የሆነ፣ ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ ያለው ተግባር የሚያከናውነው የሰው ሀይል ነው፡፡ በየመስኩ እንዲህ ያለውን ውጤታማ ሰው ማፍራት የትምህርት ትልቁ አላማ ነው፡፡

በቋንቋ ትምህርት ረገድም በሚገባ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ያለው፣ እንዲሁም ከዕውቀት ዘርፎች አንፃር ለየደረጃው የሚመጥን በቂ የሰዋስውና የስነጽሁፍ ዕውቀት ያለው ሰው /ባለሙያ ማፍራት ይፈለጋል፡፡ ለሰዎች ሀሳቡን በመናገር ሆነ በመጻፍ በቀላሉና በግልጽ ማስረዳት የሚችል፣ የሌሎችንም በወጉ መረዳት የሚችል ሰው ጥሩ የተግባቦት ክሂል ያለው ሰው ነው፡፡ አሁን ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ የተዘጋጀው መጽሐፍ ይህን አላማ ያሳካል የሚል እምነት አለን፡፡

አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋቸው የሚማሩ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የክሂልና የዕውቀት ደረጃ እንዲያሳዩ ይጠበቃል፡፡ በጥሩ ሁኔታ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ፣ እንዲሁም የሰዋስውና የስነጽሁፍ ችሎታንም ለደረጃው በሚመጥን መልኩ እንዲያሳዩ ይፈለጋል፡፡

ይህን ለማስገኘት ትምህርቱ በአብዛኛው በክሂሎች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ አራቱም ክሂሎች እኩል ደረጃ ተሰጥቷቸው በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን ትኩረቱ ስለክሂሎች ማወቅ ሳይሆን ክሂሎቹን ማወቅ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡

ከይዘት አደረጃጀት አንጻር፣ መጽሐፉ አስር ምዕራፎች አሉት፡፡ በሁሉም ምዕራፎች በተለያዩ ጭብጦች ላይ የሚያተኩሩ አስር ለማንበብ ክሂል የሚውሉ ጽሁፎች አሏቸው፡፡

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በክፍል አንድ የአዳምጦ መረዳት፣ በክፍል ሁለት የመናገር፣ በክፍል ሶስት የአንብቦ መረዳት እና በክፍል አራት የመጻፍ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ የቃላት ትምህርት ከአዳምጦ መረዳት ወይም ከአንብቦ መረዳት ጋር ተቀናጅቶ ቀርቧል፡፡ የሰዋስው እና የስነጽሁፍ ይዘቶችን ግን የምዕራፉን ይዘት ለመመጠን ሲባል በተለያዩ ምዕራፎች ቀርበዋል፡፡ የአዳምጦ መረዳትና የአንብቦ መረዳት ተግባራት ወጥ በሆነ መልኩ በሶስት ደረጃዎች እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ ከማዳመጥና ከማንበብ በፊት፣ በማዳመጥና በማንበብ ሂደት፣ እንዲሁም ካዳመጡና ካነበቡ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት በወጉ ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎች በየደረጃዎቹ እንዲያከናውኑ የቀረቡላቸው ተግባራት ዋናውን የትምህርት አላማ ከማሳካት አንጻር የየራሳቸው ድርሻ አላቸው፡፡

ስለዚህ የተዘጋጀውን የመማሪያ መጽሐፍ በወጉ በመጠቀም፣ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በመምራትና በማገዝ የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ የሚል እምነት አለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## የሃገር ፍቅር

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ምንባብ አዳምጠህ/ሽ መረጃዎችን ታወጣለህ/ታወጪያለሽ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

‹‹ሃገሯን ያስጠራች አትሌት›› የሚለውን ምንባብ ከማዳመጥህ/ሽ በፊት ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የጥንድ ውይይት በማድረግ መልስ/ሺ፡፡

ሀ. በኢትዮጵያ ውስጥ በሃገር ደረጃ የሚታወቁ አትሌቶች እነማን ናቸው? በምን ታወቁ?

ለ. ከሴት አትሌቶች መካከል የምታደንቃት/ቂያት ማነች? ለምን?

#### ሂደት ማዳመጥ ተግባር

‹‹ሃገሯን ያስጠራች አትሌት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ እያደመጥህ/ሽ፣ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. መሰረት ደፋር ለመጀመሪያ ጊዜ የሩጫ ውድድር የጀመረችው የት ነው?

ለ. መሰረት ደፋር የመጀመሪያውን የዓለም አቀፍ ውድድር የተወዳደረችው መቼ ነው? በዚህ ውድድር ስንተኛ ወጣች?

ሐ. መሰረት ደፋር በጀርመን ስቱትጋርት ተወዳድራ ሪከርድ ያስመዘገበችው በምን የሩጫ ውድድር ዓይነት ነው?

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ።

   ሀ. ከመሰረት ደፋር የሩጫ ህይወት የተማርከውን/ሽውን በአጭሩ በፅሁፍ አቅርብ/ቢ።

   ለ. መሰረት ደፋር ሃገሯን ያስጠራች አትሌት ለምን ተባለች?

   ሐ. መሰረት ደፋር በጅማሬዋ የውድድር ዘመን አሸናፊ የሆነችባቸው ርቀቶችን ዘርዝር/ሪ።

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጥ/ጪ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ተሰጥኦ | ሐ. አመራች |
| ለ. ተገነዘበች | መ. አኩሪ |

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ስለ ሃገር ፍቅር የቡድን ውይይት ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ።
- በቡድን ውይይት ወቅት የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለክፍሉ በቃል ታቀርባለህ/ታቀርቢያለሽ።

ቡድን በመመስረት ጀግኖች አባቶቻችን የሃገር ፍቅርን ለመግለፅ ያከናወኗቸውን ተግባራት በመለየት ተወያይታችሁ ለክፍሉ አቅርቡ።

# ክፍል ሶስት፣ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ‹‹የሃገር ፍቅር›› የሚለውን ምንባብ ይዘት ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- የሃገር ፍቅር ምንነትን ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡
- የምንባቡን መልዕክት ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- ለቃላት የተለያዩ ፍቺዎችን ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡

## ቅድመ ማንበብ ተግባር

1. የሃገር ፍቅር ምንድነው?
2. የሃገር ፍቅር በምን ይገለፃል?

## የሃገር ፍቅር

የሃገር ፍቅር፣ አንድ ሰው ለሚኖርበት ሃገር ያለው የጀግንነት፣ የብሄራዊ ኩራት፣ ‹‹የኔ ነው›› የማለትና የቤተኝነት ስሜት ነው፡፡ ጀግንነት ለሃገር አንዳች አስተዋፅኦ ከማበርከት ጋር፣ ብሄራዊ ኩራት ከሃገራዊ ማንነት፣ ‹‹የኔነት›› ከወገንተኝነት እንዲሁም ቤተኝነት ከደህንነት ዋስትና ጋር የተያያዘ እሳቤ ነው፡፡

የሃገር ፍቅር የተለያዩ መገለጫዎች አሉት፡፡ በሌላ አባባል፣ አንድ ሰው ሃገሩን ይወዳል ሲባል፣ መውደዱ የሚገለፅባቸው የተለያዩ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንደኛው፣ የሰንደቅ ዓላማ ወይም የባንዲራ ክብር ነው፡፡ ባንዲራ፣ የተለያዩ ሃገራዊ ሃሳቦችን የያዘ የአንድ ሃገር ትዕምርት ነው፡፡ አንድ ሃገር ከሌላው ሃገር ተለይቶ የሚታይበት መታወቂያ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ፣ የአንድ ሃገር ባንዲራ አላግባብ ሲነካ የዚያ ባንዲራ ባለቤት የሆነው ሃገር እንደሚነካ ይቆጠራል፡፡ ባንዲራን መናቅ ሃገርን እንደመናቅ፣ ባንዲራን ማክበርም ሃገርን

እንደማክበር ይታያል፡፡ የሃገራችን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራም የኢትዮጵያ መታወቂያ ነው፡፡ ይህን የሚያከብር ሰው ለሃገሩ ፍቅር እንዳለው ይቆጠራል፡፡

የሃገር ፍቅር ሌላኛው መገለጫ ሰላምና ደህንነትን ማስጠበቅ ነው፡፡ ሰላምና ደህንነት በአንድ በኩል በሃገር ውስጥ ግጭቶች እንዳይነሱና የአብሮ መኖር እሴቶች እንዳይጎዱ መጠበቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሃገርን ዳር ድንበር ከውጪ ወራሪ መከላከል ነው፡፡ በሃገር ውስጥ፣ በገጠር ሆነ በከተማ በፖለቲካ ይሁን በሌላ ምክንያት ግጭት ሊነሳ ይችላል፡፡ ግጭት ከተነሳ ደግሞ ሰው ሊጎዳ፣ ንብረትም ሊወድም ይችላል፡፡ ስለዚህ ቢቻል ግጭቱ እንዳይነሳ ማድረግ፣ ከተነሳም እንዳይስፋፋ የራስን ድርሻ ማበርከት ሃገርን የመውደድ መገለጫ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ የውጪ ጠላት በሚመጣበት ጊዜም ከሃገር መከላከያ ጎን በመሆን የራስን ድርሻ መወጣት ሃገርን የመውደድ መገለጫ ነው፡፡ አንድ ሰው የሚወደው ዘመዱ ወይም ጎረቤቱ እንዳይጎዳ በመጠንቀቅ ፍቅሩን እንደሚገልጥ ሁሉ ለሃገሩም እንደዚያ በማድረግ ይገልጣል፡፡ የቀድሞ አባቶቻችን ከጣሊያን የተቃጣብንን ተደጋጋሚ ወረራ፣ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ሆ ብለው በመትመም ለሃገራቸው ያላቸውን ፍቅር ገልጠዋል፡፡ ሃገራቸውንም በጠላት ከመገዛትና ከማፈር ጠብቀዋል፡፡

የሃገር ፍቅር ተግቶ በመስራትም ይገለጣል፡፡ አንድ ህዝብ ተግቶ ካልሰራ ደሃና ኋላ ቀር ይሆናል፡፡ ሁሉም ሰው በየተሰማራበት የስራ መስክ በሚገባ ከሰራ ፍሬያማ ይሆናል፡፡ ገበሬው በግብርናው፣ ወዝ አደሩ በኢንዱስትሪው፣ ሌላውም እንደየስራ ዘርፉ በትጋት ከሰራ ሃገሩን ያበለፅጋል፡፡

ዜጋን መውደድና ማክበር ሌላው የሃገር ፍቅር መገለጫ ነው፡፡ የአንድ ሃገር ዜጋ ሲቸገር መርዳት፣ ሲበደል መሟገት፣ በጎኑ ቆሞ

መደገፍ የሃገር ፍቅር ነው፡፡ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ብዙዎችን ሊረዳ በሚችል መልኩ የበጎ አድራጎት ስራዎችን በመስራት ሰዎችን መደገፍ ይገባል፡፡

(መነሻ ሃሳቡ፣ ከመምህር ጉጉ. መቻ. ዋልታ የአማርኛ አጋዥ፣ 5ኛ - 8ኛ፣ ገፅ 145 ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተቀንጭቦ የተወሰደ፡፡)

### ድህረ ማንበብ ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

   ሀ. በምንባቡ መሰረት የሃገር ፍቅር ምንድነው?

   ለ. የሃገር ፍቅር መገለጫ ተብለው የቀረቡ ሃሳቦች ስንት ናቸው? ለይተህ/ሽ አውጣ/ጪ፡፡

   ሐ. ሌሎች የሃገር ፍቅር መገለጫዎች ናቸው የምትላቸው/የምትዪአቸው ካሉ ጥቀስ/ሺ፡፡

   መ. የፅሁፉ መልዕክት ምንድነው?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡ ሃሳቡን ያገኘህበትን/ሽበትን ቦታ ከምንባቡ አመልክት/ቺ፡፡

   ሀ. የሃገር ፍቅር ህዝብን በሚጠቅሙ ስራዎች ይገለጣል፡፡

   ለ. የሃገርን ሃብት መንከባከብ እንደ አንድ የሃገር ፍቅር መገለጫ ተጠቅሶአል፡፡

   ሐ. የቀድሞ አባቶች የሃገርን ዳር ድንበር ያስከበሩት ተቀምጠው በመነጋገር ነው፡፡

   መ. ተግቶ መስራት ሃገርን እንደመውደድ የሚቆጠረው፣ ውጤቱ ብዙ ሰዎችን ስለሚጠቅም ነው፡፡

**ማስታወሻ፤ የቃላት አውዳዊ ፍቺ**

የቃላት አውዳዊ ፍቺ የሚባለው አንድ ቃል በማህበራዊ አጠቃቀም ጊዜ በተለያዩ ሁኔታዎች የተለያየ ፍቺ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው፡፡ ቃሉ አንድ ሆኖ በአንድ ቦታ አንድ ፍቺ፣ በሌላ ቦታ ሌላ ፍቺ ይኖረዋል፡፡ ፍቺው እንደዓረፍተ ነገሮቹና ለማለት እንደተፈለገው ጉዳይ አንፃር ይለያያል፡፡ ከዚህ የተነሳ የአንድ ቃል ትክክለኛ ማለትም አጠቃቀማዊ ፍቺ የሚታወቀው በዓረፍተ ነገር ውስጥ ከሌሎች ቃላት በመቀናጀት መልዕክት ሲያስተላልፍ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ሸረከተው›› የሚለውን ቃል ብንወስድ፣ ‹‹ወፍጮው ስለተበላሸ በቆሎውን ሸረከተው››፣ ገረደፈው ለማለት፣ ‹‹ምስማሩ የአልማዝን ቀሚስ ሸረከተው›› ቀደደው ለማለት ይውላል፡፡

3. ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. በጎ አድራጎት
ለ. ሰላም
ሐ. ደህንነት
መ. መትመም

4. ቀጥሎ በቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍቺ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. አማረች በውሃ ጥም ተቃጠለች፡፡
ለ. ፋላሳ በገጠመው ጉዳይ ሃሳቡ ተሰረቀ፡፡
ሐ. ዕቃው ጥሩ ዋጋ አወጣ፡፡
መ. ልጅቱ ከብዙዎች ጋር ተወዳድራ አንደኛ ወጣች፡፡

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- የግል የዕለት ውሎ ፅፈህ/ሽ በክፍል ውስጥ ታነባለህ/ ታነቢያለሽ፡፡

ቀጥሎ ‹‹የዕለት ውሎዬ›› በሚል ርዕስ ከአንድ አንቀፅ ያላነሰ ድርሰት ፅፈህ/ሽ በክፍል ውስጥ አንብብ/ቢ፡፡

**ማስታወሻ፤ የዕለት ውሎ ማስታወሻ**

✍ የዕለት ውሎ ማስታወሻ፣ ሰዎች በየዕለቱ የሚያደርጉትን፣ የሚገጥማቸውን፣ የሚሰማቸውን፣ ወዘተ. ጉዳይ ሁሉ ያሰፈሩበት ደብተራቸው ነው፡፡ ጠዋት ስንነሳ በዕለቱ ለማድረግ ያቀድነውን መፃፍ ይቻላል፡፡ የቀኑን ውሎ ውጣ ውረድ፣ ሰዎች በዕለቱ ያደረጉትንና የገጠማቸውን፣ የተሰማቸውን ሃዘን ይሁን ደስታ መዝግበው ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ ወደ ፊት የግለሰቡ የህይወት ታሪክ አካል ይሆናል፡፡

✍ እኛ በዚህ ትምህርት በአንድ በኩል፣ የዕለት ውሎ መመዝገብን፣ በሌላ በኩልም የአፃፃፍ ስርዓት መጠበቅን ሁለቱንም እናነሳለን፡፡ በዕለት ውሎ ማስታወሻው የተፃፈበት ቀን ይኖራል፡፡ ማስታወሻውን የፃፈው ሰው በውሎው ያገኛቸውን ሰዎችና የነበረበትን ጊዜና ቦታ (መቼት) ሊፅፍ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት፤ ሰዋስው፤ የስም አገባብ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- ከቃል ክፍሎች መካከል የስምን አገባብ ትለያለህ/ ትለዪአለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ ሰዋስው (የስም አገባብ)**

✍ በዚህ ክፍል ስለ ስም አገባብና ቅርፅ እናነሳለን፡፡ ስም በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በመግባት የተለያዩ ሰዋስዋዊ ሙያዎችን ያከናውናል፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ካያሞ ደብተር ገዛ›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ስሞች ይገኛሉ፡፡ እነርሱም ‹‹ካያሞ›› እና ‹‹ደብተር›› ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የመግዛትን ተግባር ያከናወነውን አካል ስለሚያሳይ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የመገዛት ድርጊት የተፈፀመበት አካል ስለሆነ ተሳቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት፣ ከሙያ አንፃር፣ ስም በዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትና ተሳቢ ይሆናል፡፡ ከቅርፅ አንፃር ደግሞ፣ /-ኦች/ የሚለውን አብዢ ምዕላድ ይቀበላል፡፡ /ልጅ - ኦች/ ለዚህ ምሳሌ ይሆናል፡፡

ቀጥሎ በቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በጥንድ በመወያየት ባለቤትንና ተሳቢን ለይተህ/ሽ አውጣ/ጪ፡፡

ሀ. ሀጃሞ ልብስ ሰጠኝ፡፡

ለ. መምህሩ ጠመኔ አመጣ፡፡

ሐ. ዓለሚቱ የቤተሰቧን መሶብ ወሰደች፡፡

መ. ቀበሌው ትምህርት ቤቱን አደሰ፡፡

## ክፍል ስድስት፤ ስነ ፅሁፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

👁 የምሳሌያዊ ንግግሮችን አጠቃቀም ትለያለህ/ዩአለሽ፡፡

ማስታወሻ፣ ምሳሌያዊ ንግግር

✍ ምሳሌያዊ ንግግር፣ እንደስሙ ሃሳብን በምሳሌ እያዋዛ የሚያቀርብ የቃላዊ ስነ ፅሁፍ ዓይነት ነው፡፡ ሰዎች በየዕለት ማህበራዊ ኑሮዋቸው የሚገጥሟቸውን ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለሌሎች ለማስረዳት፣ ከታወቀና ተቀባይነት ካለው አጠቃላይ ገጠመኝ ወይም እውነታ ጋር እያዛመደ በማስረጃነት የሚያቀርብ የአነጋገር ስልት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ውል አያወላውል፤ ሙላት አያሻግር›› ቢባል፣ ‹‹ውል›› ና ‹‹የውሃ ሙላት›› ተነፃፅረው ቀርበዋል፡፡ ውል የተዋዋለ ሰው ውሉን ማክበር ይኖርበታል፤ የውሉ መኖር እንደፈለገው እንዲሆን ወይም እንዲያደርግ አይፈቅድለትም፤ አያወላውለውም፡፡ እንደዚሁም ደግሞ፣ የወንዝ ሙላት ሰውን በቀላሉ አያሻግረውም ማለት ነው፡፡ ‹‹ውሃ እድፍን ያጠራል፤ ትምህርት ልብን ያጠራል›› ቢባልም፣ ውሃና ትምህርት በማጥራት ተግባር ተነፃፅረው ቀርበዋል፡፡

✍ ምሳሌያዊ ንግግር ሁልጊዜ በንፅፅር ላይቀርብ ይችላል፡፡ ምሳሌያዊ ንግግር በምክንያትና ውጤትም ሊገለፅ ይችላል፡፡ ‹‹ውሃ ቢደርቅ፣ ዓሳ ያልቅ››፤ ‹‹አለባብሰው ቢያርሱ፣ በአረም ይመለሱ›› ለዚህ ምሳሌ ይሆናል፡፡

✍ ምሳሌያዊ ንግግርን ከሚያስተላልፈው ትምህርት አንፃርም ማየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ የችኮላን ጉዳት የሚያሳይ ‹‹የነቶሎ ቶሎ ቤት፣ ግድግዳው ሰንበሌጥ››፣ የመተባበርን አስፈላጊነት የሚመክር ‹‹ድር ቢያብር፣ አንበሳ ያስር›› ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

1. ቀጥሎ የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያስተላልፉትን ቁም ነገር ተናገር/ሪ፡፡

   ሀ. ትለብሰው የላት፣ ትከናነበው አማራት፡፡
   ለ. ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም፡፡
   ሐ. እንኳን ዘንቦብሽ፣ እንዲያውም ጤዛ ነሽ፡፡
   መ. በሬ ከአራጁ ይውላል፡፡

2. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡ ጅምር ምሳሌያዊ ንግግሮችን አሟላ/ዪ፡፡

   ሀ. የቆጡን አውርድ ብላ፣ ______________________
   ለ. ሰርገኛ መጣ፣ ______________________
   ሐ. ሞኝ የዕለቱን፣ ______________________
   መ. ሳይቃጠል፣ ______________________
   ሠ. አይጥ ሞቷን ስትሻ፣ ______________________

3. የምታውቃቸውን/ቂያቸውን ሌሎች አምስት ምሳሌያዊ ንግግሮችን አምጥተህ/ሽ፣ ሃሳባቸውን ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡
4. ምሳሌያዊ ንግግር እየተጠቀምህ/ሽ አጭር ንግግር አድርግ/ጊ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የስራ ባህል

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ፅሁፍ ሲነበብልህ/ሽ አዳምጠህ/ሽ መረጃዎችን ታወጣለህ/ ታወጪያለሽ፡፡
- በድምፅ ከፍታና ዝቅታ የተነገሩ ዓረፍተ ነገሮችን አዳምጠህ/ሽ ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡

**ቅድመ ማዳመጥ ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡ ቃላት መምህራችሁ ከሚያቀርቡላችሁ የማዳመጥ ምንባብ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ለቃላቱና ለሃረጋቱ ግምታዊ ፍቺ ስጥ/ጪ፡፡ (ፅሁፉን ካዳመጥህ/ሽ በኋላ ትክክለኛውን መልስ እንደገና ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ)፡፡

ሀ. ደቦ
ለ. መኸር
ሐ. ማረም
መ. ሰብል

**ሂደተ ማዳመጥ ተግባር**

‹ደቦ›› የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ መምህራችሁ የሚያነቡልህን/ሽን የማዳመጥ ምንባብ በአፅንኦት እያዳመጥህ/ሽ ለይ/ዪ፡፡

**ድህረ ማዳመጥ ተግባር**

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት ተገቢ ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ደቦ ምንድነው?

ለ. የደቦን ጥቅም ዘርዝር/ሪ፡፡

ሐ. አርሶ አደሩ የስራ ጫናን ለመቀነስ አዘውትሮ የሚጠቀመው ምንድነው?

መ. ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሲባል ምን ማለት ነው?

2. በቅድመ ማዳመጥ ተግባር የቀረቡ ጥያቄዎችን ፍቺ እንደገና ስጥ/ጪ፡፡ የገመትከውና/ሽውና ከምንባቡ በኋላ የተረዳከው/ሽው ይለያያል?
3. ቀጥሎ መምህርህ/ሽ የተወሰኑ ዓረፍተ ነገሮችን ያነቡልሃል/ሻል፡፡ አነባበባቸውን አዳምጠህ/ሽ፣ አነባበቡ በመልዕክቱ ላይ ያመጣውን ለውጥ ተናገር/ሪ፡፡
4. መምህርህ/ሽ የሚያነቡልህን/ሽን ምልልስ እያዳመጥህ/ሽ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ የፅሁፍን ሃሳብና መልዕክትን በማጉላት ረገድ ያለውን ሚና ተናገር/ሪ፡፡

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

### ምልልስ፣ መደበኛ ንግግር

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- በሚና ጨዋታ በመሳተፍ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡
- ልምድን መነሻ ባደረጉ ርዕሶች ዙሪያ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡
- የመደበኛ ንግግር ስርዓት ጠብቀህ/ሽ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ ሚና ጨዋታ**

✍ ማዳመጥና ማንበብ መረጃን መቀበያ ክሂሎች ሲሆኑ፣ መናገርና መፃፍ ግን መረጃን የማመንጨትና ለሌሎች ማስተላለፊያ ክሂሎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ክሂሎች የሚዳብሩት በተግባራዊ ልምምድ ነው፡፡

✍ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ከሚያገለግሉ መንገዶች አንዱ ሚና ጨዋታ ነው፡፡ ሚና ጨዋታ፣ የአንድን ሰው፣ ለምሳሌ፣ የመካኒክ፣ የገበሬ፣ የሃገር መሪ፣ ወዘተ. ቦታ ይዞ እንደርሱ የመናገርና የማከናወን ተግባር ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ እንደ መምህር፣ እንደ ነጋዴ፣ እንደ ሃኪም፣ ወዘተ. ሆነው መንቀሳቀስ፣ እንደ ወከሉት ሰው መሆን፣ እንደወከሉት ሰው መናገር ነው፡፡

1. ቀጥሎ የቀረበውን የጎበዝና የሰነፍ ተማሪ ምልልስ ሚና ወስደህ/ሽ በመዘጋጀት በክፍል ውስጥ አቅርብ/ቢ፡፡

| |
|---|
| ዱሬሳ፣ ጎበዝ ተማሪን ይወክላል፡፡ |
| ጊዴሳ፣ ሰነፍ ተማሪን ይወክላል፡፡ |

ዱሬሳ፦ እኔ ከሁሉም በላይ የማስቀድመው ትምህርቴን ነው፡፡

ጊዴሳ፦ ትምህርት ለምን ይጠቅማል? በኛ ሰፈር ያሉ አቶ ሃይሉ ምንም አልተማሩም፡፡ ከሁላችንም የተሻለ ኑሮ የሚኖሩት ግን እርሳቸው ናቸው፡፡

ዱሬሳ፦ ዛሬ በሰማይ የሚበረውን፣ በምድር የሚሽከረከረውን የፈጠሩት አቶ ሃይሉ ናቸው? የተማረ ሰውኮ ነው፡፡ አታውቅም እንዴ መማር ሙሉ ሰው ያደርጋል፡፡

ጊዴሳ፦ ፈረንጅ እንጂ ሃበሻ ሲፈጥር እኔ አይቼ አላውቅም፡፡ ተምረን የት እንደርሳለን ብለህ ነው?

ዱሬሳ፦ ካልተማርን ወደ ፊት እርሻን እንኳ በአግባቡ አርሰን ከሌላው በተሻለ ሁኔታ ምርታማ መሆን አንችልም፡፡

ጊዴሳ፤ ገና አሁን እውነት ብለሃል፡፡ ከዚህ አኳያ መማር ጥሩ ሊሆን ይችላል፡፡

ዱሬሳ፤ አንተ መማርን ሃብት ከማግኘት ጋር በማያያዝህ የተሳሳተ አስተሳሰብ እንዲኖርህ አድርጎአል፡፡ ተምሮ ጥሩ መሪ፣ ተምሮ በጣም ጥሩ ሃብታም፣ ተምሮ ጥሩ ነጋዴ፣ ተምሮ የተሻለ ገበሬ መሆን ይቻላል፡፡

ጊዴሳ፤ አሁን ገባኝ፡፡ ተምሮ የተለያዩ ስራዎችን በጥሩ ሁኔታ ለመስራት ከሆነ እኔም ትምህርቴን ከልቤ ለመከታተል እሞክራለሁ፡፡

2. በቡድን ሆናችሁ መሰረት ስለ ስራ ባህል የቀረቡ ስዕሎችን በማየት የንግግርን ስርዓት ጠብቀህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡



ሀ. ስዕሎቹን በትኩረት በመመልከት የሚያስተላልፉትን ሃሳብ ተናገር/ሪ፡፡

ለ. በስዕሎቹ ላይ የሚታዩ ሰዎች ምን እያደረጉ እንደሆነ ግለፅ/ጪ፡፡

ሐ. ስዕሎቹን አስተውለህ/ሽ ተመልከት/ቺ፡፡ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀህ/ሽ የሚያደርጉትን ነገር ተናገር/ሪ፡፡

3. ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች መካከል አንዱን በቡድን በመምረጥ የደረሳችሁበትን ሃሳብ በመደበኛ የንግግር አቀራረብ ለክፍሉ አቅርብ/ቢ፡፡

ሀ. ጎበዙ ተማሪ

ለ. ታታሪው ገበሬ

ሐ. የጨምበላላ በዓል አከባበር

መ. የጎጆ ቤት አሰራር

**ማስታወሻ፤ መደበኛ ንግግር**

- መደበኛ ንግግር፣ በአብዛኛው በስብሰባ አዳራሽ ወይም በመድረክ የሚቀርብ በመሆኑ የመድረክ ንግግርም ይባላል፡፡ አስቀድሞ በመዘጋጀት፣ ለብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ የሚቀርብ ነው፡፡

ሀ. የንግግር አዘገጃጀት

- የንግግርን ርዕሰ ጉዳይ መወሰንና ማጥበብ፣ የንግግሩን ዓላማ በግልፅ ማወቅ፣
- የአድማጮችን አጠቃላይ ደረጃ መገንዘብ (ለማን ምን፣ እንዴት ማቅረብ እንደሚገባ ለማወቅ ይረዳልና)፣
- በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በቂ መረጃ መሰብሰብ፣ መረጃውን ለህዝብ ማቅረብ በሚቻልበት ተገቢ ቅደም ተከተል ማደራጀትያስፈልጋል፡፡

ለ. የንግግር አቀራረብ

- ራስንና የንግግሩን ርዕሰ ጉዳይ ለአድማጮች ማስተዋወቅ፣
- ከአጀማመር አንስቶ እስከ አጨራረስ አድማጮችን በሚያረካ መልኩ መናገር፣
- በንግግር ሂደት የአድማጮችን አጠቃላይ ሁኔታ ማስተዋል (በጥሞና እየተከታተሉ መሆን አለመሆናቸውን) ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

(ከቀድሞው የ12ኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ፣ 1986፣ ለደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ)

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ምንባብ በማንበብ መረጃዎችን ታወጣለህ/ታወጪያለሽ፡፡
- ለቃላትና ሃረጋት አገባባዊ ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡

### ቅድመ ማንበብ ተግባር

‹‹የስራ ባህል›› የሚለውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ምን ዓይነት ተግባር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል?

ለ. ጠንካራ የስራ ባህልን እንዴት ልናዳብር እንችላለን?

### ሂደተ ማንበብ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ የጠንካራ የስራ ባህልን ምንነት እየለየህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

## የስራ ባህል

ጠንካራ የስራ ባህል፣ ሰዎች ለስራ ካላቸው አመለካከት ይመነጫል፡፡ ጠንካራ የስራ ባህል በተሰማሩበት የስራ መስክ ተግቶ በመስራት ውጤታማ መሆንን ያመለክታል፡፡ ሰራተኞች ከሚፈጥሩት የስራ ተነሳሽነትና ፍቅር አንፃር ይወሰናል፡፡ ለግለሰብ፣ ለማህበረሰብና ለሃገር ዕድገት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ጠንካራ የስራ ባህል የግለሰብን የገቢ መጠን በማሳደግ ኑሮን ለማሻሻል ይጠቅማል፡፡ በተሰማሩበት የሙያ መስክ ዕውቀትንና ጉልበትን በአግባቡ በስራ ላይ ማዋል፣ ምርታማነትን በማሳደግ ገቢን ለመጨመር ይረዳል፡፡ ገቢ ባደገ መጠንም የአኗኗር ዘይቤም ይለወጣል፡፡

ጠንካራ የስራ ባህል ማህበራዊ ዕድገትን ያመጣል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት በመረዳዳትና በመተጋገዝ የታቀደን ስራ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳቸው ያላወቁትን ከሌላው በመማር የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮት በመፍታት ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ ጉልበትና ግብዓቶችን በጋራ ከተጠቀሙ ብዙ ጊዜ የሚወስድን ስራ በወቅቱ ለማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡ ውጤታማ ስራ በመስራታቸው በራሳቸው የመተማመንን ስሜት በማዳበር አካባቢያቸውን ለመለወጥና ለሌላ የበለጠ ስራ ለመነሳሳት ይችላሉ፡፡

‹‹ደቦ›› የተሰኘው የስራ ባህል ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳል፡፡ የስራ መሳሪያን፣ ጉልበትንና ጊዜን በጋራ በመጠቀም ብዙ ቀን ይፈጅና ያደክም የነበረን ስራ በአጭር ጊዜ ለመጨረስ ያስችላል፡፡

ጠንካራ የስራ ባህል የሃገር ዕድገትን በማፋጠን ማህበራዊ ለውጥን ያመጣል፡፡ ዜጎች በምጣኔ ሃብታቸው እያደጉ በሄዱ መጠን የሃገሪቱ ልዩ ልዩ ገቢዎች ይጨምራሉ፡፡ የኑሮ ደረጃም ይሻሻላል፡፡

(ጉጉ. መቻ. ዋልታ የአማርኛ አጋዥ፣ 5ኛ - 8ኛ፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

## ድህረ ማንበብ ተግባር

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ምክንያት እየሰጠህ/ሽ እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

   ሀ. ጠንካራ የስራ ባህል ማህበራዊ ዕድገትን ያመጣል፡፡
   
   ለ. በተሰማሩበት የስራ መስክ ጉልበትንና ዕውቀትን በአግባቡ በስራ ላይ ማዋል ተፈላጊነቱ ያነሰ ነው፡፡
   
   ሐ. የስራ ባህል፣ ሰዎች በሚፈጥሩት የስራ ተነሳሽነትና የስራ ፍቅር ይወሰናል፡፡
   
   መ. ጠንካራ የስራ ባህል አስተሳሰብንና ዕውቀትን ያዳብራል፡፡

2. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ መልሶቻቸውን በቃል ተናገሩ፡፡

   ሀ. ጠንካራ የስራ ባህል ማለት ምን ማለት ነው?
   
   ለ. ጠንካራ የስራ ባህል የግለሰብን የገቢ መጠን ያሳድጋል ሲባል ምን ማለት ነው?
   
   ሐ. ጠንካራ የስራ ባህል ማህበራዊ ፋይዳው ምንድነው?

**ማስታወሻ፤ የቃላት አውዳዊ ፍቺ**

✍ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ካላቸው አጠቃቀም የተነሳ የሚያሳዩት የፍቺ ልዩነት አውዳዊ ፍቺ ይባላል፡፡

ለምሳሌ፣ ‹‹አጠረ›› የሚለውን ቃል ብንወስድ

- ግንበኛው ቤቱን በግንብ አጠረ።
- የልጁ ሱሪ አጠረ።

✍ በነዚህ ሁለት ምሳሌዎች አንዱ ቃል ከገባበት አገልግሎት አንፃር ሁለት የተለያየ ፍቺ እንዳለው እንመለከታለን። የመጀመሪያው አጥር መስራትን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ግን የቁመት ማነስን ያሳያል።

ሌላ ምሳሌ፤ ‹‹ቀመሰ›› በሚለው ቃል

- ዳኢቴ ወጥ ቀመሰች። አጣጣመች ለማለት
- ዳኢቴ ዱላ ቀመሰች። ተመታች ለማለት
- ዳኢቴ መከራ ቀመሰች። ተቸገረች ለማለት

✍ ከነዚህ ምሳሌዎች የቃላት አጠቃቀማዊ ፍቺ የተለያየ መሆኑን እንገነዘባለን።

3. ቀጥሎ ከምንባቡ በወጡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሃረጋት አውዳዊ ፍቺ ፈልግላቸው/ጊላቸው።

ሀ. ጠንካራ የስራ ባህል ማህበራዊ ዕድገትን ያመጣል።
ለ. በማህበራዊ አውድ ውስጥ ስራን በወቅቱ ለመጨረስ በደቦ መስራት ይገባል።
ሐ. በራስ ገቢ በመኖር ነፃ የሚወጣው ከሌሎች ጥገኝነት ብቻ ሳይሆን ከህሊና ወቀሳ ጭምር ነው።
መ. ገቢ ባደገ መጠን የአኗኗር ዘይቤ ይለወጣል።

4. ቀጥሎ የተሰመረባቸው ቃላት በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሲገቡ ያላቸውን ፍቺ ስጥ/ጪ።

ሀ. ሬሳው ፈረሰ። ጭንቅላቱ ፈረሰ።

ለ. ቡናው ለለቀማ ደረሰ። ቃባቶ መፅሃፍ ደረሰ።

ሐ. ገበሬው ገመዱን ፈታ፡፡ ሰውዬው እንቆቅልሹን ፈታ፡፡

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- በዓረፍተ ነገሮችና በታሪኮች ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ትጠቀማለህ/ትጠቀሚያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ ስርዓተ ነጥብ**

- ስርዓተ ነጥብ፣ የነጥቦችና የምልክቶች ስርዓት ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ ስርዓተ ነጥብ፣ ምልክቶች በፅሁፍ ውስጥ ገብተው ሃሳብን የሚያጎሉበትን ሁኔታ የሚያመለክት ደንብ ነው፡፡ አንድ ፅሁፍ ከያዘው ሃሳብ አንፃር እንዴት መነበብ እንዳለበት የሚያሳይ የነጥቦች አጠቃቀም ስርዓት ነው፡፡ በመሆኑም ምልክቶች የሚያገለግሉበትን መንገድ ማወቅ የአንድን ፅሁፍ አነባበብና ሃሳቡን መረዳት ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ስራዓተ ነጥቦች በተገቢው መንገድ ካልገቡ እነዚያን በመለየት ለማቃናትም ይረዳል፡፡

- ስራዓተ ነጥቦች የሚባሉት እንደአንድ ነጥብ(.)፣ ሁለት ነጥብ(:)፣ ነጠብጣብ ወይም ሶስት ነጥብ (...)፣ አራት ነጥብ (፡፡) ያሉትን ሲሆን፣ ምልክት ወይም ትዕምርት የምንለው ደግሞ እንደ ትዕምርተ አንክሮ (!)፣ ትዕምርተ ጥያቄ (?) ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››) ያሉትን ነው፡፡ ትዕምርት ማለትም ምልክት ማለት ነው፡፡

## ስራዓተ ነጥቦች ዓይነቶችና አገልግሎታቸው

### 1. አንድ ነጥብ (.)

አንድ ነጥብ፣ ይዘት ተብሎም ይጠራል፡፡ ለተለያዩ ጉዳዮች ያገለግላል፡፡

ሀ. አንድን ቃል አሳጥሮ ለመፃፍ

ምሳሌ፣ ዓ.ም. ዓመተ ምህረት

አ.አ. አዲስ አበባ

ኢ.ዜ.አ. የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት

ለ. ብርን ከሳንቲም ለመለየት

ምሳሌ፣ 2.75 ሁለት ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም

3.00 ሶስት ብር

### 2. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (፡-)

በዝርዝር የሚቀርቡ ነጥቦች መኖራቸውን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፣ የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገዶች ብዙ ናቸው፡፡

እነርሱም፡-

- ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት
- እንደ ምላጭ ያሉ ብረት ነክ ዕቃዎችን በጋራ መጠቀም
- ከበሽተኛው የፈሰሰ ደም መንካትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሁለት ነጥብ ከሰረዝን ስንጠቀም የሚዘረዘሩ ነገሮች በምሳሌው እንደተቀመጠው መሆን አለባቸው፡፡

### 3. አራት ነጥብ (፡፡)

አራት ነጥብ በተሟላ ዓረፍተ ነገር መጨረሻ በመግባት ሃሳብን የማጠቃለል ተግባር ያከናውናል፡፡ የዓረፍተ ነገር መግቻ

ነው። ዓረፍተ ነገር በራሱ የነገር ማረፊያ ማለት ነው። ያን በፅሁፍ ውስጥ ለማመልከት ደግሞ አራት ነጥብ ያገለግላል።

ምሳሌ፣ ዜጎች፣ ሃገራችንን በልማት ለማሳደግ በመረባረብ ላይ ይገኛሉ።

- ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን የእግር ኳስ ቡድን እየደገፉ ናቸው።
- መማር ያስከብራል።

### 4. ትዕምርተ ጥያቄ (?)

የጥያቄ ምልክት፣ የዓረፍተ ነገር ሃሳብ በጥያቄ መልክ መቅረቡን ያመለክታል።

ምሳሌ፣

- መምህራችን ወዴት ሄዱ?
- የአማርኛ መምህራችሁ ማነው?
- አሁን ስንት ሰዓት ነው?

### 5. ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ›› ወይም " ")

የተለያዩ ጉዳዮችን ሊያመለክት ይችላል። አንዱን ብቻ እናንሳ። ትዕምርተ ጥቅስ (የጥቅስ ምልክት) በንግግር ውስጥ፣ የተናጋሪን ሃሳብ ከሌላው የዓረፍተ ነገር ክፍል ለይቶ ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፣ የክፍላችን ተጠሪ እየሮጠ መጥቶ፣ ‹‹ሁላችንም ፈተናውን አልፈናል›› በማለት የምስራች ነገረን። በዚህ ምሳሌ ውስጥ የክፍል ተጠሪው ንግግር በትዕምርተ ጥቅሱ ውስጥ የተቀመጠው ነው። ከርሱ በግራና በቀኝ ያሉት የፀሃፊው ገለፃዎች ናቸው።

## 6. ነጠላ ሰረዝ (፣)

በርካታ አገልግሎቶች አሉት፡፡ ዝርዝር ቃላትንና ሃረጋትን ለመለየት፣ የገፀ ባህርይን ንግግር ከፀሃፊው ገለፃ ለመለየት፣ የሃሳብ ቆምታን ለማሳየት ማገልገሉ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የተወሰኑ አገልግሎቶቹን እናንሳ፡፡

**አንደኛው፣** የሃሳብ ቆምታን ለማሳየት ያገለግላል የሚለው ነው፡፡ የሃሳብ ቆምታ፣ በፅሁፍ ውስጥ ለአንድ ሃሳብ አፅንኦት ለመስጠት ወይም በማንበብ ሂደት ትንፋሽ ለመውሰድ ቆም የሚደረግበት ሁኔታ ነው፡፡

ምሳሌ፣ በዚሁ አንቀፅ ውስጥ ያቀረብነውን ዓረፍተ ነገር እንደ ምሳሌ እንውሰድ፡፡ ‹‹አንደኛው፣ የሃሳብ ቆምታን ለማሳየት ያገለግላል የሚለው ነው››፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ከ‹‹አንደኛው›› ቀጥሎ የገባው ነጠላ ሰረዝ የሃሳብ ቆምታን ያሳያል፡፡

**ሁለተኛው** የነጠላ ሰረዝ አገልግሎት፣ የፀሃፊን ገለፃ ከገፀ ባህርዩ ንግግር ለይቶ ለማመልከት ነው፡፡ (በዚህ ዓረፍተ ነገር የተጠቀምነው ነጠላ ሰረዝ ቆምታን ያሳያል፤ እግረ መንገዳችንን እያስታወስን እንድንሄድ)፡፡

ምሳሌ፣ የክፍላችን ተጠሪ እየሮጠ መጥቶ፣‹‹ሁላችንም ፈተናውን አልፈናል›› በማለት የምስራች ነገረን፡፡

በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹የክፍላችን ተጠሪ እየሮጠ መጥቶ›› ከሚለው ቀጥሎ የገባው ነጠላ ሰረዝ የመጀመሪያውን የፀሃፊ ገለፃ ከገፀ ባህርዩ ወይም ከክፍል ተጠሪው ንግግር ለይቶ ለማመልከት (ቆምታም ነው) ያገለግላል፡፡

**ሌላኛው** የነጠላ ሰረዝ አገልግሎት በተከታታይ እየተዘረዘሩ የሚመጡ ቃላትንና ሃረጋትን ለይቶ ለማመልከት ያገለግላል የሚለው ነው፡፡

ምሳሌ፣

ሀ. አየለች ወደ ገበያ ሄዳ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ቀይ ስር፣ ጎመንና ቲማቲም ገዝታ መጣች።

ለ. የሰፈራችን ገበሬዎች እርሻ ማረስ፣ ዘር መዝራት፣ ከብቶችን ማርባት፣ እንዲሁም ማህበራዊ ጉዳይ መወጣት የዘውትር ስራቸው ነው።

## 7. ድርብ ሰረዝ (፤)

ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ፣ ግን የሃሳብ ተከታታይነት ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮችን ለማያያዝ ያገለግላል።

ምሳሌ፣ ልጅቱ በጠዋት ተነሳች፤ ፊቷን ታጠበች፤ ቁርሷን በላች፤ ቦርሳዋን ያዘች፤ ከዚያም ወደ ትምህርት ቤት ሄደች።

## 8. ትዕምርተ አንክሮ (!)

ሃሳብን የማናር ወይም ከፍ የማድረግ ስሜትን የሚያሳይ ምልክት ነው። ትዕምርተ አጋኖ እየተባለ የሚጠራውም ለዚህ ነው። ትዕምርት ማለትም ምልክት ማለት ነው።

ምሳሌ፣

ሀ. ሰውዬው ጫካውን እያቆራረጠ ሲሄድ ድንገት የደነገጠች ድርጭት ስትበር ‹‹ዘራፍ!›› እያለ እመር አለ።

ለ. ህፃኑ ተናዶ እየጮኸ በእጁ የያዘውን ቆሎ ብትን! አደረገው።

1. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክለኛውን የስርዓተ ነጥብ ዓይነት አስገብተህ/ሽ እንደገና ፃፍ/ፊ።

ሀ. ማሳንቱ አውሮፕላን አብራሪ መሆን ትፈልጋለች

ለ. ደራርቱ የስነ ፅሁፍ ሽልማት አገኘች

ሐ. ዛሬ እዚህ እንዴት መጣህ

መ. ወሮ ዓለሚቱ ዛሬ ወደ በንሳ ሄደች

2. የሚከተሉትን ሃረጎች አሳጥረህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

ሀ. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት
ለ. የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ሐ. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት
መ. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

3. ቀጥሎ በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ያሉ ተራ ቁጥሮችን በተገብ ስርዓተ ነጥቦች ተኩ።

ማርታ በርካታ የዳንስ ቀኖችም ሆኑ ምሽቶች አሳልፋለች። ከሁሉም ይልቅ በዚህ ቀላል የዳንስ ቀን፣ ‹‹ዲስኮ›› በጭንቅላቷ ውስጥ ተቀርፆ [1] የቀረ ምንም ሴት ያልነበረ በሚመስልበት አዳራሽ እሷ፣ [2] ዲስኮ ሌዲ [3] ሆና በወንዶች መሃል እንደ ጣያት ተቀምጣለች።

[4] ዳንስ ትወጂያለሽ [5] [6] አላት እስክንድር ከትዝታ ባህር መስመጧን ሳያጤን። የንግግሩ ክብደት አልተሰማትም [7]

‹‹እስቲ እናንተው ሁኑበት›› ብላ ቀለደችና [8] [9] እውነት ግን ከልብህ ነው እንዲህ ሃገር ወዳድ ሆነህ የምትከራከረው? [10] አለችው።
‹‹እውነቴን ነው›› አላት።

## ክፍል አምስት፤ ሰዋስው

## የግስ ምንነት፣ አገባብና ቅርፅ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የግስን ምንነት ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ።
- የሁኔታና የድርጊት ግስን ትለያለህ/ትለዩአለሽ።
- የባለቤት አመልካች ጥገኛ ምዕላዶችን ትለያለህ/ትለዩአለሽ።

**ማስታወሻ፤ የግስ ምንነትና አገባብ**

- ግስ፣ ድርጊትን ወይም ሁኔታን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ ምን ተደረገ? እና ምን ሆነ? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የምናገኘው ከግስ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ከፈተ›› ብንል የተደረገን ነገር እናውቅበታለን፡፡ የ‹‹መክፈት›› ድርጊት ተፈፅሞአል፡፡ በአንፃሩ፣ ‹‹ወፈረ›› ወይም ‹‹አዘነ›› ብንል ግን የሆነን ጉዳይ እናገኛለን፡፡ መወፈርም ሆነ ማዘን ድርጊቶች አይደሉም፡፡

- በአማርኛ ቋንቋ፣ ግስ በአገባቡ ከሌሎች ቃላት ይለያል፡፡ ግስ የዓረፍተ ነገር ሃሳብ መቋጫ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዓረፍተ ነገሩ መጨረሻ ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ገበሬው በሬውን ሸጠው›› ቢባል፣ ‹‹ሸጠው›› የሚለው ከላይ እንዳልነው ድርጊትን ከማመልከቱም በላይ፣ በዓረፍተ ነገሩ መጨረሻ ገብቶአል፡፡ በዚህ አገባቡ ማሰሪያ አንቀፅ ይባላል፡፡

- ግስ የሚለይበት ሌላኛው ጉዳይ ቅርፁ ነው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የዓረፍተ ነገር ባለቤት አመልካች የሆኑ ቅጥያዎችን በስተመጨረሻ መቀጠሉ ባህርዩ ነው፡፡

ለምሳሌ፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከፈት -ሁ | ከፈት- ህ | ከፈት-ኧ | ከፈት-ኣችሁ |
| ከፈት-ን | ከፈት-ሽ | ከፈት-ኧች | ከፈት-ኡ |

- እነዚህ በግሱ መጨረሻ የመጡ ሁሉ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትን አመልካች ጥገኛ ምዕላዶች ናቸው፡፡

- ከዚህ ጋር ተሳቢ አመልካችንም ከባለቤት አመልካቹ ቀጥሎ ሊወስድ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ሰደብ - ኧ - ኝ (ሰደበኝ) በሚለው ውስጥ ከባለቤት አመልካቹ /-ኧ/ ቀጥሎ ያለው በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ያለው ተሳቢ ነው፡፡ በሚቀጥለው ምሳሌ

እንመልከት፡፡ ‹‹ስዩም እኔን ሰደበኝ›› ቢል፣ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ስዩም የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ሲሆን፣ ‹‹እኔን›› ግን ተሳቢ ነው፡፡ የተሰደበው አካል ማለት ነው፡፡ ከላይ በቀረበው ግስ ውስጥ ያለው /-ኧ/ ስዩምን ሲያመለክት፣ /-ኝ/ ግን ‹‹እኔን›› ያመለክታል፡፡ ይህ ከግስ ቅርፅ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡

1. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤቱንና ማሰሪያ ግሱን ለይተህ/ሽ አውጣ/ጪ፡፡

ሀ. የደጊቱን ዶሮ ሸለምጥማጥ በላት፡፡

ለ. አሊቶ ዛሬ ወደ በንሳ ሄደ፡፡

ሐ. ከወናጎ የተገዛው ሰንጋ ታረደ፡፡

መ. ከአርባ ምንጭ የተገዛው ሙዝ በውድ ዋጋ ተሸጠ፡፡

2. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ባሉ ማሰሪያ ግሶች ላይ ያሉትን ባለቤትና ተሳቢ አመልካች ቅጥያዎችን ለይተህ/ሽ አውጣ/ጪ፡፡

ሀ. ዱካሞ እንጨቱን ፈለጠው፡፡

ለ. ዳምሌ ሽንኩርቱን ሸጠች፡፡

ሐ. ተማሪዎቹ ደብተር ገዙ፡፡

መ. ልጅቱ ዶሮዋን ገደለቻት፡፡

# ክፍል ስድስት፤ ስነ ፅሁፍ

## ግጥም መፃፍና መልዕክቱን መለየት

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤቶች**

- የግጥምን መልዕክት ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡
- የግጥም ስንኝና ሃረግን ለይተህ/ሽ ታሳያለህ/ታሳዩአለሽ፡፡
- አጭር ግጥም ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ የግጥም ምንነት**

- ግጥም በሃረግና በስንኝ የሚዋቀር የስነ ፅሁፍ ዓይነት ነው፡፡ ግጥም እኩል ከተመጠኑ ስንኞች ወይም ሃረጎች የተነሳ ሙዚቃዊ ቃና ይፈጥራል፡፡ ሃረግ የአንድ ስንኝ እኩሌታ ነው፡፡ ስንኝ ግን እንደ ሁኔታው የሁለትም ከዚያ በላይም ሃረጋትን ሊይዝ ይችላል፡፡ በአንድ ሃረግ ብቻ ሊዋቀርም ይችላል፡፡

- ምሳሌ፣

  ክፉና ደጉን እያደባለቀ፣
  መንፈሱ ለይቶ ፍርድ ካላወቀ፡፡
  ድካሙ ከሆነ ለጌጡ ለልብሱ፣
  ልፋቱ ከሆነ እስኪሞላ ከርሱ፡፡
  ካላቀረበለት ህሊናው ወቀሳ፣
  በምን ይበልጣል የሰው ልጅ ከእንስሳ፡፡

- ‹‹ክፉና ደጉን እያደባለቀ›› የሚለው ስንኝ ሲሆን፣‹‹ክፉና ደጉን››ና ‹‹እያደባለቀ›› ሃረጎች ይሆናሉ፡፡ ግጥሙ በአጠቃላይ ስድስት ስንኞች ሲኖሩት፣ አስራ ሁለት ሃረጎች አሉት፡፡

1. ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹን መልስ/ሺ፡፡

ቆንጆ ጎበዝ ሃብታም አዋቂ ተብሎ፣
የአዳም ልጅ በመሬት እንደ አበባ በቅሎ፣
አንድ እንኳን ሳይታይ ከመካከል በቅሎ፣
ሁሉም ወዳቂ ነው እንደ አበባ ረግፎ፡፡

ሀ. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?
ለ. የግጥሙ ሃረጎች ስንት ናቸው?
ሐ. የግጥሙ መልዕክት ምንድነው?
መ. ግጥሙን ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

2. አንድ ርዕስ መርጠህ/ሽ ከአምስት ስንኞች ያላነሰ አንድ ግጥም ፃፍ/ፊ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## ኤች አይ ቪ እና መተላለፊያ መንገዶቹ

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የምንባብን ሃሳብ ርዕሱን አይተህ/ሽ ትገምታለህ/ ትገምቺያለሽ፡፡
- ምንባብን መምህርህ/ሽ ሲያነቡልህ/ሽ አዳምጠህ/ሽ የይዘት መረጃዎችን በቃል ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

ቀጥሎ ለቀረበው ጥያቄ የሚደመጠው ምንባብ ከመነበቡ በፊት ግምታዊ ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

ኤች አይ ቪ (ኤድስን) በሚመለከት መድልዎ (ማድላት) እና ማግለል ምንን ያመለክታል? ከምን ጋር የተያያዘ ነው?

#### ሂደተ ማዳመጥ ተግባር

የሚደመጠውን ምንባብ መምህርህ/ሽ ሲያነቡላችሁ እያዳመጥህ/ሽ መድልዎና ማግለል በምን ምክንያትና ሁኔታ እንደሚከሰት ለይተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በቃል መልስ/ሺ።

   ሀ. በህዝብ ዘንድ ተደማጭነትና ተአማኒነት ያላቸውን ሰዎች ዘርዝር/ሪ።

   ለ. ኤች አይ ቪ (ኤድስ) በደማቸው ውስጥ ካለባቸው ሰዎች ጋር አብሮ በመቆየት፣ በመብላትና በመጠጣት ቫይረሱ የማይተላለፈው ለምንድነው?

   ሐ. ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ መድልዎንና ማግለልን ለመከላከል ከተጠቀሱት ነጥቦች መካከል አንዱ ‹‹በደማቸው ኤች አይ ቪ ያለባቸው ሰዎች አዎንታዊ የአኗኗር ዘዴ እንዲከተሉ ማድረግ ነው›› ሲባል ምን ለማለት ነው? አስረዳ/ጂ።

2. የሚነበብልህን/ሽን ፅሁፍ እያዳመጥህ/ሽ የለየሃቸውን/ሻቸውን ፍሬ ነገሮችን ፅፈህ/ሽ ለክፍሉ በቃል ተናገር/ሪ።

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤት**

- በውይይት የደረስክበትን/ሽበትን ሃሳብ በበቂ ምክንያትና ማስረጃ አስደግፈህ/ሽ ለክፍሉ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ።

ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጠህ/ሽ ከሌሎች ጋር የቡድን ውይይት በማድረግ የደረስክበትን/ሽበትን ለክፍሉ ተናገር/ሪ።

   ሀ. የትምህርት ቤታችን ተማሪዎች በኤች አይ ቪ እንዳይያዙ ማድረግ ያለብን ተግባራት ምንድናቸው?

   ለ. በኤች አይ ቪ የተያዙ ወገኖቻችንን ላለማግለል ማድረግ ያለብን ምንድነው?

**ማስታወሻ፤ የውይይት መመሪያ**

✍ ውይይት፣ ዓላማ ያለው፣ በሰዎች መካከል የሚካሄድ የሃሳብ ልውውጥ ነው። ሰዎች ጊዜና ቦታ ወስነው በመገናኘት በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ የሚለዋወጡበትና በተቻለ መጠን ከስምምነት ላይ የሚደርሱበት ተግባር ነው።

1. የውይይት ዝግጅት

✍ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ ማግኘት፣ ለዚህም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ የፅሁፍና የቃል መረጃዎችን መመርመር

✍ በማንበብና ሰዎችን በማናገር የተገኙ ማስታወሻዎችን በወጉ ማደራጀት፤ ለተወያዮቹ ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም መረጃዎቹ የርዕሰ ጉዳዩን የተለያዩ ገፅታዎች የሚያሳዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ

2. የውይይት አቀራረብ

✍ በቡድን ውይይት የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለክፍሉ ስታቀርቡ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

- ርዕስና ዓላማን በግልፅና በአጭሩ ማስተዋወቅ
- በልበ ሙሉነትና በድፍረት፣ ለአወዱ በተመጠነ ድምፅ መናገር፣ የአድማጭን ፊት ወይም ዓይን እየቃኙ መከታተል
- የሌሎችን ሃሳብ ማክበር፣ እንዲሁም ተራ ጠብቆ መናገር
- ንግግራችሁ ተቀባይነትና ተአማኒነት እንዲኖረው በቂ ምክንያትና ማስረጃ ማቅረብ

✍ ከታዳሚዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መዝግቦ በመጨረሻ ተጨባጭና ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ መስጠት

# ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍል ሶስት የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ምንባብ አንብበህ/ሽ ይዘቱን ትለያለህ/ትለዪአለሽ።
- የምንባቡን ይዘት ትተነትናለህ/ትተነትኚያለሽ።

## ቅድመ ማንበብ ተግባር

የሚከተለውን ጥያቄ ‹‹ኤች አይ ቪ እና መተላለፊያ መንገዶቹ›› ምንባብን ከማንበብህ/ሽ በፊት መልስ/ሺ።

ኤች አይ ቪ የሚተላለፍባቸውንና የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ዘርዝር/ሪ።

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ስታነብ/ቢ የኤች አይ ቪ የሚተላለፍባቸውንና የማይተላለፍባቸውን መንገዶች እየለየህ/ሽ በዝምታ አንብብ/ቢ።

### ኤች አይ ቪ እና የመተላለፊያ መንገዶቹ

ኤች አይ ቪ የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅም በማዳከም ለሌሎች በሽታዎች የሚያጋልጥ ረቂቅ ተህዋስ (ቫይረስ) ነው። ቫይረሱ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው በ1978 ዓ.ም ነው። በኢትዮጵያ የኤድስ ህመምተኛ የታወቀው ደግሞ በቫይረሱ ከተያዘ ከሁለት ዓመት በኋላ ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በሽታው በከፍተኛ ፍጥነት እየተሰራጨ ይገኛል።

ቫይረሱ በተለያዩ መንገዶች ይተላለፋል። መተላለፊያ መንገዶቹን ማወቅ ራስን ለመጠበቅና የበሽታውን ስርጭት ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው።

ቫይረሱ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው፡፡ ቫይረሱ ካለባቸው ሰዎች ጋር በሚደረግ ጥንቃቄ የጎደለው የወሲብ ግንኙነት ቫይረሱ ወደ ጤነኞች ይተላለፋል፡፡ በዓለም ላይ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆኑት የቫይረሱ ተጠቂዎች የተያዙት በዚሁ መንገድ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ቫይረሱ ከነፍሰ ጡር እናትም ወደ ልጅ ይተላለፋል፡፡ ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኝ እናቶች ተገቢውን የህክምና ክትትል ካላደረጉ ቫይረሱ ወደ ልጅ እንደሚተላለፍ ተረጋግጧል፡፡ በእርግዝና ጊዜ ተገቢ የህክምና ክትትል ካልተደረገ በሶስት መንገዶች ከእናት ወደ ልጅ ይተላለፋል፡፡ በእርግዝና ወቅት ከእናት ወደ ልጅ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ሁለተኛ፣ በወሊድ ጊዜ በሚኖር የደም ንክኪ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ሶስተኛም፣ ህፃናት የእናት ጡትን በሚጠቡበት ጊዜም ሊተላለፍ ይችላል፡፡

ሌላው፣ የተበከለን ደም ለሌሎች በመለገስም ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በተለያዩ የህክምና ተቋማት ውስጥ የሚታከሙ ሰዎች ተጨማሪ ደም ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት የሚሰጣቸው ደም በኤች አይ ቪ የተበከለ ከሆነ ይተላለፍባቸዋል፡፡ ይህ እንዳይሆን የለጋሾቹን ደም አስቀድሞ በመመርመር ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

ቫይረሱ በደም ንክኪ ሊበከሉ በሚችሉ ሌሎች መሳሪያዎች አማካይነትም ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ቫይረሱ ያለባቸው ሰዎች የተጠቀሙባቸውን ምላጮች፣ መርፌዎች፣ ወረንጦችና የመሳሰሉ ስለታም ነገሮችን ጤነኛ የሆኑ ሰዎች ከተጠቀሙባቸው ሊተላለፍባቸው ይችላል፡፡ አደንዛዥ ዕፅ በመርፌ የሚወስዱ ሰዎች መርፌ የሚጋሩ ከሆነ ቫይረሱ በቀላሉ ይተላለፍባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገዶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በግርዛት፣ በንቅሳት፣ እንጥል

በማስቀረጥ፣ ግግ በማስወጣት ወዘተ. አማካኝነት በሚፈጠር የደም ንክኪ ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

በአንፃሩ፣ ቫይረሱ የማይተላለፍባቸውን መንገዶች ማወቁም ከአጉል ፍርሃትና ጭንቀት ይገላግላል፡፡ ለምሳሌ ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝ ሰዎች ጋር እጅ ለእጅ በመጨባበጥ፣ ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም፣ መታጠቢያ ቤት በጋራ በመጠቀም፣ አብሮ በመብላት፣ በአንድ ቤት ውስጥ አብሮ በመኖር አይተላለፍም፡፡ በትንፋሽ፣ በሳልና በእንጥሻም አይተላለፍም፡፡ በትንኞችና ሌሎች ደም መጣጭ ነገሮች አይዛመትም፡፡ እርሳስ፣ እስክሪብቶ፣ ደብተርና መፅሃፍ በመዋዋስም ቫይረሱ ከሰው ወደ ሰው አይተላለፍም፡፡

(ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፡፡ 2011፡፡ ኤች አይ ቪ. ፕሪቬንሽን ፓኬጅ ከሚል ፅሁፍ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

## ድህረ ማንበብ ተግባር

1. ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ/ሺ፡፡

   ሀ. ኤች አይ ቪ. ምን ዓይነት በሽታ ነው?

   ለ. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኤድስ ህመምተኛ የታወቀው መቼ ነው?

   ሐ. ኤች አይ ቪ. በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዴት ሊተላለፍ ይችላል?

   መ. የኤች አይ ቪ. ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ እንዴት ይተላለፋል?

2. በምንባቡ መሰረት ቫይረሱ የሚተላለፍባቸውንና የማይተላለፍባቸውን መንገዶች የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተርህ/ሽ በመገልበጥ ፃፍ/ፊ፡፡

| ተ.ቁ. | ኤች አይ ቪ የሚተላለፍባቸው መንገዶች | ኤች አይ ቪ የማይተላለፍባቸው መንገዶች |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

3. ምንባቡ የሚያስተላልፈውን ይዘት በአጭሩ ተንትነህ/ሽ በቃል አቅርብ/ቢ፡፡

አሁን ደግሞ ከቃላት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ትሰራለህ/ትሰሪያለሽ፡፡ የቃላት ጥያቄዎችን ከመመለስህ/ሽ በፊት ምንባቡን እንደገና አንብብ/ቢ፡፡

4. ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› አምድ ስር ለቀረቡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በ‹‹ለ›› አምድ ስር ከቀረቡት አማራጮች መርጠህ/ሽ አዛምድ/ጂ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. ስርጭት | ሀ. ተላላፊ በሽታ |
| 2. መነመነ | ለ. ማስወገድ፣ ማቆም |
| 3. ወረርሽኝ | ሐ. ፍርሃት |
| 4. መግታት | መ. ግንዛቤ |
| 5. ስጋት | ሠ. ከሳ |
| | ረ. መስፋፋት |

5. በ‹‹ሀ›› ስር ለተሰጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በ‹‹ለ›› አምድ ከቀረቡት መካከል መርጠህ/ሽ አዛምድ/ጂ።

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
| --- | --- |
| 1. በሽተኛ | ሀ. ግድ የለሽ |
| 2. ከሳ | ለ. ማሳጠሪያ |
| 3. ጠንቃቃ | ሐ. ጨመረ |
| 4. ማርዘሚያ | መ. ነሳ፣ ነፈገ |
| 5. ቀነሰ | ሠ. ተጎዳ |
| 6. ለገሰ | ረ. ጤነኛ |
| | ሰ. ወፈረ |

6. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሃረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ፃፍ/ፊ።

ሀ. አደንዛዥ ዕፅ በመርፌ የሚወስዱ ሰዎች ቫይረሱ ይተላለፍባቸዋል።

ለ. በእርግዝና ጊዜ ተገቢ የህክምና ክትትል ካልተደረገ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ ይተላለፋል።

ሐ. በትንፋሽ፣ በሳልና በእንጥሻ በሽታው አይተላለፍም።

መ. ቫይረሱ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ማወቅ ከአጉል ፍርሃትና ጭንቀት ይገላግላል።

# ክፍል አራት፤ መፃፍ

## አንቀፅ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- አያያዦችን ተጠቅመህ/ሽ ዓረፍተ ነገሮችን ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡
- የተለያዩ ርዕሶች መርጠህ/ሽ በምክንያትና ውጤት የአፃፃፍ ስልት አንቀፅ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

## አያያዦችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መፃፍ

**ማስታወሻ፤ የአያያዦች ምንነትና አጠቃቀም**

- አያያዦች፣ በንግግር ሆነ በፅሁፍ ውስጥ ቃልን ከቃል፣ ሃረግን ከሃረግ፣ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር በሃሳብ ያያይዛሉ፡፡ የአሁን የኛ ትኩረት አያያዦችን በፅሁፍ ውስጥ መጠቀም ነው፡፡ አያያዦች ለተመረጡለት ዓላማ እንዲያገለግሉ በጥንቃቄ መጠቀም ይገባል፡፡

- በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ አያያዦች የሚባሉት ና፣ ወይም፣ ሆኖም፣ ቢሆንም፣ ስለዚህ፣ በመሆኑም፣ የሆነ ሆኖ፣ ምንም እንኳ፣ ነገር ግን፣ ዳሩ ግን፣ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ የተነሳ፣ በዚህ መሰረት፣ ወዘተርፈ ናቸው፡፡

ምሳሌ፣

- አየለ እና ተሰማ መጡ፡፡ (አያያዡ ‹‹እና›› ቃልን ከቃል አያይዟል)
- ገልሜሳ ኳስ መጫወት ወይም መፅሃፍ ማንበብ ይፈልጋል፡፡ (አያያዡ ‹‹ወይም›› ሃረግን ከሃረግ አያይዟል)

- ዳኢቴ በጣም ታጠናለች፤ በመሆኑም ጎበዝ ተማሪ ሆነች። (አያያዡ ‹‹በመሆኑም›› ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር አያያይዟል። ያያያዘው አዎንታዊና ተደጋጋፊ ሃሳብ ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ነው)። ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር ጋር የሚያያይዙት ነጠላ ዓረፍተ ነገርን ወደ ድርብ ዓረፍተ ነገር ያሳድጋሉ።

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች በሃሳብ ሊያቀናጃቸው በሚችል አያያዥ በማያያዝ ፃፍ/ፊ።

ሀ. ወንድሙ ንቁ አዕምሮ አለው። ነገሮችን ቶሎ ይገነዘባል።
ለ. ታታሪነቴ ያኮራኛል። እንደ ስራዬ ውጤታማ አይደለሁም።
ሐ. አባቴንና እናቴን እወዳቸዋለሁ። በየጊዜው ባያቸው ደስ ይለኛል።
መ. ቁርስ አልበላሁም። አልራበኝም።

2. የሚከተሉትን አያያዦች በተገቢ ቦታቸው በመጠቀም አንቀፁን አሟላ/ዪ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሆኖም | ነገር ግን | ወይም | አለበለዚያ |
| በመሆኑም | እና | ምክንያቱም | |

ለአባቷ ሁለተኛም የመጨረሻም ልጅ ናት። አባቷ እርሷ ጥሩ ደረጃ ላይ ደርሳ ማየት ይመኛል። ‹‹ተስፋዬ አንቺው ነሽ›› የሚለውን የአባቷን ንግግር ሰንቃ፣ ትምህርቷን መማር ጀመረች። ሌሊት ተነስታ ስታጠና ቅዝቃዜው ይቀረጥማታል፤ ----1------ ጥናቷን ሳታቋርጥ እስኪነጋ ድረስ ታጠናለች። ጓደኞቿ አዲስ ልብስ፣ ዘመናዊ ቦርሳና ልዩ ልዩ ጌጣ ጌጥ ሲኖሯቸው እርሷ ግን ተመኝታ አታውቅም። -----2-------የእርሷ ራዕይ ጥሩ ውጤት አምጥታ ያለ እናት ያሳደጓትን የአባቷን ህልም እውን ማድረግ ነው። በርካታ ችግሮች ደርሰውባታል፤ -------3------ አንዳቸውም ከጥናቷ ወደ

ኋላ አላስቀሯትም፡፡ ሁሉንም በድል ተወጥታቸዋለች፡፡ ከስምንተኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ በትምህርቷ የሚወዳደራት አልነበረም፡፡ የምታገኛቸው ሽልማቶች ---4---- ምስጋናዎች ኃይል ሆነዋታል፡፡ ሳይንቲስት ---5--- መሃንዲስ የመሆን ፍላጎት ነበራት፡፡ ጥረቷ ሁሉ ፍሬ አፍርቶ አሁን የዩኒቨርሲቲ የምህንድስና ተማሪ ሆናለች፡፡ ዛሬም ከመቼውም በላይ ጠንክራ ታጠናለች፡፡ ቤተ መፃህፍት ታዘወትራለች፡፡ ---6---- የእስካሁን ልፋቷና የአባቷ ቃል መና እንደማይቀርባት ታምናለች፡፡ ----7---- ሙሉ ጊዜዋንና ትኩረቷን በትምህርቷ ላይ ብቻ አድርጋ ወደ ስኬት እየገሰገሰች ትገኛለች፡፡

## አንቀፅ መፃፍ

**ማስታወሻ፤ አንቀፅ**

- በአንቀፅ ውስጥ ያሉ አንድን ሃሳብ የሚያብራሩ ዓረፍተ ነገሮች በአያያዦች የተያያዙና **የሃሳብ ተከታታይነት** ያላቸው ናቸው፡፡
- በአንቀፅ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ሃሳብን ከመሸከም አንፃር የተለያዩ ናቸው፡፡ አንደኛው የአንቀፁን ሃሳብ ሰብስቦ የያዘው ጠቅላይ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር መንደርደሪያ እየተባለም ይጠራል፡፡
- መንደርደሪያ የተባለው ከሚገባበት ቦታ አንፃር ሳይሆን ሃሳቡን የሚጀምረው ስለሆነ ነው፡፡ ሆኖም መንደርደሪያ የተባለው ዓረፍተ ነገር በአንቀፁ መጀመሪያ፣ መሃከል ወይም መጨረሻ ሊገባ ይችላል፡፡ ሌሎቹ ዓረፍተ ነገሮች ዋናው ዓረፍተ ነገር የያዘውን ሃሳብ የሚያብራሩ ወይም የሚዘረዝሩ በመሆናቸው ዘርዛሪ ዓረፍተ ነገሮች ይባላሉ፡፡

እነዚህ ዘርዛሪ ዓረፍተ ነገሮች ከመንደርደሪያ ዓረፍተ ነገሩ በሃሳብ የተለዩ መሆን የለባቸውም፡፡

✍ ለምሳሌ፣

‹‹የቤተሰብ መፍረስ›› በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት ስልት የተፃፈን አንቀፅ ምሳሌ እንመልከት፡፡

✍ ባልና ሚስት በተለያዩ ምክንያቶች በሃሳብ ሳይስማሙ ሲቀሩ ችግሩ ሄዶ ሄዶ የሚያስከትለው ጉዳት ብዙ ነው፡፡ በመጀመሪያ ቤተሰብ የሚባለው ማህበራዊ ተቋም ይፈርሳል፡፡ ልጆችም በባልና ሚስት መለያየት ምክንያት እንደ ዕቃ ለሁለት ተከፍለው ሁለት ቤት ሆነው ያድጋሉ፡፡ ባልና ሚስቱ፣ ‹‹እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ›› በሚል አጉል ፉክክር ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን ስለሚያደርጉ ልጆች ከስነ ምግባርና ከቁጥጥር ውጪ ይሆናሉ፡፡ በመጨረሻም አልባሌ ቦታዎችን በማዘውተር ለተለያዩ ሱሶች ስለሚጋለጡና ስለሚጠቁ ለራሳቸውም ለቤተሰቦቻቸውም ሳይሆኑ ይቀራሉ፡፡

1. ቀጥሎ በቀረበው የቢጋር ሰንጠረዥ ውስጥ በሰፈረው የሃሳብ መነሻነት፣ ‹‹ኤች አይ ቪ ና መዘዙ›› በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአፃፃፍ ስልት ሁለት አንቀፆችን በመፃፍ ለመምህርህ/ሽ አሳይ/ዪ፡፡ አንቀፁ ከላይ የቀረበውን ማብራሪያ የሚያሟላ መሆን እንዳለበት ልብ አድርግ/ጊ፡፡

**ምክንያት**

- የደም ንክኪ
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት
- ስለታም የሆኑ ነገሮችን በጋራ መጠቀም
- ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች




**ውጤት**

- የጤና መታወክ
- የቤተሰብ መበተን
- በኤኮኖሚ መዳከም
- የሰው ህይወት መቅጠፍ

2. በመረጥከው/ሽው ርዕስ ቢያንስ ሁለት አንቀፆች ያሉት አንድ ድርሰት ፅፈህ/ሽ ለክፍሉ ተማሪዎች አንብብ/ቢ።

## ክፍል አምስት፤ ሰዋስው

### የቅፅል ምንነትና አገባብ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- ቅፅል የስም ገላጭ መሆኑን ትለያለህ/ትለዩአለሽ።

**ማስታወሻ፤ የቅፅል ምንነትና አገባብ**

- ቅፅል፣ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ካለው ቦታ አንፃር ስምን ቀድሞ የሚገባ፣ ቀድሞት የገባው ስም ከተለያዩ ጉዳዮች (መልክ፣ መጠን፣ ባህርይ...) አንፃር የሚያሳይ የቃል ዓይነት ነው። ለምሳሌ፣
    - ትልቅ ደብተር በሚለው ውስጥ፣ ‹‹ትልቅ›› ስምን ቀድሞ የገባ፣ መጠንን ገላጭ ቅፅል ነው።

- <u>ቀይ</u> ደብተር በሚለው ደግሞ ‹‹ቀይ›› የደብተርን መልክ ገላጭ የሆነ ቅፅል ነው፡፡
- <u>ጠንካራ</u> ደብተር በሚለው ውስጥ ‹‹ጠንካራ›› የደብተርን ባህርይ ይገልፃል፡፡
- ነገር ግን ከስም ቀድሞ የሚገባ ሁሉ የስም ገላጭ ወይም ቅፅል ላይሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ያ ቤት›› በሚለው ሃረግ ውስጥ ‹‹ያ›› ከስም ቀድሞ የገባ ቢሆንም ቅፅል አይደለም፡፡

ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅፅሉን ለይተህ/ሽ ለመምህርህ/ሽ አሳይ/ዪ፡፡

ሀ. ነጭ ልብስ ለብሷል፡፡
ለ. ሰባራ ስኒ ለቡና መጠጫ አያገለግልም፡፡
ሐ. ሰፊ ሜዳ ኳስ ለመጫወት ይመቻል፡፡
መ. ህፃናት በጠባብ ስፍራ መጫወት የለባቸውም፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ወጣትነትና ሱሰኝነት

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ከፅሁፍ ርዕስ ተነስተህ/ሽ ለቃላት ግምታዊ ፍቺ ትሰጣለህ/ ትሰጪያለሽ፡፡
- መምህርህ/ሽ ምንባብ ሲያነቡ አዳምጠህ/ሽ ጭብጡን ታወጣለህ/ታወጪያለሽ፡፡
- በፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ ገፀ ባህርያትን ስብዕና ትለያለህ/ ትለዪአለሽ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡ ቃላት ከምታዳምጠው/ጪው ምንባብ የተወሰዱ ናቸው፡፡ ለቃላቱ ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ግምታዊ ፍቺ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ፍንጃል ለ. ባልቴቶች

#### ሂደተ ማዳመጥ ተግባር

የሚደመጠውን ፅሁፍ መምህርህ/ሽ ሲያነቡልህ/ሽ እያዳመጥህ/ሽ የገፀ ባህርዩን ስብዕና ወይም ባህርይ ለይ/ዪ፡፡

**ማስታወሻ፤ የገፀ ባህርይ ስብዕና**

- የገፀ ባህርይ ስብዕና ያልነው የገፀ ባህርዩ ባህርይ ለማለት ነው፡፡ መልካም፣ ክፉ፣ ስራ ወዳድ፣ ቸልተኛ፣ ፈጣን፣ ጎታታ፣ ቶሎ ተግባቢ፣ በቶሎ የማይግባባ፣ ደግ፣ ንፉግ፣ ንፁህ መልበስ የሚወድ፣ ለአለባበሱ ግድ የሌለው ወዘተ. ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡ ከዚህም ጋር መልኩና ቁመናው ሊገባ ይችላል፡፡

## ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በፅሁፍ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

   ሀ. ከገፀ ባህርዩ ህይወት የተረዳከው/ሽው ምንድነው?

   ለ. ‹‹በጎውን ስራ ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አልብሰዋል›› በሚለው ውስጥ አፈር አልባሹ ማነው?

   ሐ. ተበጆ ሰካራሙ ከሚያሰክር ሁሉ ለመታረም ብዙ ጊዜ አስቦ ያልቻለው ለምን ይመስልሃል/ሻል?

   መ. ‹‹የጉሌለው ሰካራም›› የሚለው ፅሁፍ ጭብጥ ምንድነው?

2. ቀጥሎ መምህርህ/ሽ ከሚያነቡልህ/ሽ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጥበቅና በመላላት የፍቺ ልዩነት የሚያመጡ ቃላት አሉ፡፡ እያዳመጥህ/ሽ ቃላቱን ለይተህ/ሽ የፍቻቸውን ልዩነት ተናገር/ሪ፡፡

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍል ሁለት የሚጠበቅ ውጤቶች**

- በምልከታ ያገኘሃቸውን/ሻቸውን መረጃዎችን በንግግር ታቀርባለህ/ ታቀርቢያለሽ፡፡
- ተረት አንብበህ/ሽ መልሰህ/ሽ ትናገራለህ/ሪያለሽ፡፡

1. የትምህርት ቤትህ/ሽ አጠቃላይ ገፅታ ምን እንደሚመስል ለማያውቅ ሰው ለማስተዋወቅ እንደምታቀርብ/ቢ አድርገህ/ሽ በማሰብ ተናገር/ሪ፡፡

**ማስታወሻ፤ የንግግሩ አቀራረብ**

✍ ንግግር ስታደርግ/ጊ የሚከተሉትን ነጥቦች ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

- የትምህርት ቤቱ የምስረታ ታሪክ (መቼ፣ በማን፣ እንዴት እንደተሰራ)
- ባለህበት/ሽበት አካባቢ ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት አቅጣጫ
- የትምህርት ቤቱ አቀማመጥ፣ የሸፈነው ቦታ መጠን (ስፋት)
- በትምህርት ቤቱ ግቢ የሚገኙ ህንፃዎች (መማሪያ፣ ቢሮ፣ ቤተ መፃህፍት፣ ቤተ ሙከራ፣ መፀዳጃ፣ የኳስ ሜዳ፣ እርሻ ...) አቀማመጥ (አቅጣጫ) እና የህንፃዎቹ መጠንና ቀለም
- የመምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ብዛትን ማካተት ይቻላል፡፡

✍ እነዚህንና የመሳሰሉ ሌሎች መካተት ያለባቸውን ጉዳዮች በቅደም ተከተልና ለሌሎች በሚገባ መልኩ በዝርዝር ማቅረብ ይገባል፡፡ በዚህ ጊዜ የሃሳብ አቀራረብ ልዩ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ከዚህም ጋር ከዚህ በፊት እንደተማርከው/ሽው በድፍረት፣ ጎላ ባለ ድምፅ፣ ቀና ብሎ አድማጭን እያዩ፣ በጥሩ ሰዋስው መናገር ወዘተ ያሉ የጥሩ ንግግር ባህርያትን በስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

2. ቀጥሎ አንድ ተረት ቀርቦአል፡፡ መምህርህ/ሽ በሚሰጡህ/ሽ መመሪያ መሰረት ተረቱን በግል በማንበብ ከተለማመድህ/ሽ በኋላ ለክፍሉ በትረካ መልክ በቃል አቅርብ/ቢ፡፡

## ተረት

በድሮ ጊዜ ሁለት ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ሁለቱ ባልና ሚስት ዶሮ አረዱ፡፡ ያረዱትን ዶሮ በደንብ ከሰሩ በኋላ ከመብላታቸው በፊት ለጥርሳቸው መጎርጎሪያ ለማምጣት ወደ ጫካ ይሄዳሉ፡፡ በመንገድ ላይ ወታደሮች ለስራ (ለግዳጅ) ታዘው ሲሄዱ አገኟቸው፡፡ ወደ ወታደሮቹ ይጠጉና እቤት ዶሮ አርደን፣ ጠላ ጠምቀን ልንበላ ስንል የጥርስ መጎርጎሪያ ለማማጣት ወደ ጫካ እየሄድን ነን፡፡ ስለዚህ በኛ ቤት በኩል ስታልፉ እንዳትገቡ ብለዋቸው ሄዱ፡፡ ባልና ሚስቱም ወታደሮቹ እንደሄዱ፣ ‹‹በጣም ደግ ናቸው፤ አደራ የተባሉትን እንኳ የሚነኩ አይመስሉም›› እያሉ ተሳስቀው ወደ ጫካ ገቡ፡፡

ወታደሮቹ የሩቅ መንገደኞች ስለነበሩ፣ እነዚህ ቂሎች ብለው ወደ ተጠቆሙበት ቤት ሄዱ፡፡ እዚያም ባልና ሚስት ያዘጋጁትን ዶሮ በልተው ጠጥተው ሁሉን ክፍትፍት አድርገው በሩን ብቻ ዘግተው ሄዱ፡፡

ባልና ሚስቱ የጥርስ መጎርጎሪያ ይዘው ሲመለሱ ቤቱ ዝንብ በዝንብ ሆኖ አገኙት፡፡ ያዘጋጁት ምግብ ተበልቶ ትርፍራፊውን ዝንብ ወርሮት ነበር፡፡ ከዚያ ዶሮ ወጣቸውን ዝንብ ነው የበላው ብለው ስላሰቡ በቤቱ ውስጥ ውር ውር የሚሉትን ዝንቦች አንድ በአንድ መግደል ጀመሩ፡፡ ዝንቦቹ በእንስራው፣ በምጣዱ፣ በማሰሮው ላይ ሲያርፉ እነሱን አገኘን ብለው ሲመቱ የቤቱን ዕቃ ሁሉ ሰባበሩት፡፡ ከዝንቦቹ አንዷ በሚስቱ አፍንጫ ላይ አረፈች፡፡

ባልም ‹‹ቀስ በይ፣ እንዳትንቀሳቀሺ›› ብሎ ተጠጋትና ዝንቧን እገድላለሁ ብሎ በያዘው ዱላ የሚስቱን አፍንጫ ነርቶ ገደላት ይባላል፡፡

(ሀይሌ ገ/የሱስ፣ ‹‹የስነ ቃል ማስተማሪያ›› ያልታተመ ገጽ፣ 22)

3. በተረቱ አቅርቦት ጊዜ በመናገር ያልተሳተፍህ/ሽ ከሆነ፣ የምታውቀውን/ቂውን ተረት ለክፍሉ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ምንባብ አንብበህሽ ይዘቱን ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- የምንባብን ሃሳብ ከርዕሱ በመነሳት ትገምታለህ/ትገምቺያለሽ፡፡
- የምንባብን ሃሳብ እየተረዳህ/ሽ ታነባለህ/ታነቢያለሽ

### ቅድመ ማንበብ ተግባር

‹‹ወጣትነትና ሱሰኝነት›› በሚለው ርዕስ ስር የቀረበውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት ከዚህ በፊት ያለህን/ሽን ዕውቀት መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተርህ/ሽ ላይ ፅፈህ/ሽ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ረድፎች ሙላ/ዪ፡፡

| ወጣትነትና ሱሰኝነት | | |
|---|---|---|
| ስለ ወጣትነትና ሱሰኝነት የማውቀው | ስለ ወጣትነትና ሱሰኝነት ማወቅ የምፈልገው | ስለ ወጣትነትና ሱሰኝነት ያወቅሁት |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

‹‹ወጣትነትና ሱሰኝነት›› የሚለውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰማ/ሚ በቅድመ ንባብ ላይ ‹‹ማወቅ የምፈልገው›› ብለህ/ሽ የዘረዘርካቸው/ሻቸው ነጥቦች በምንባቡ ውስጥ መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን እያስተዋልክ/ሽ በዝግታ አንብብ/ቢ፡፡

### ወጣትነትና ሱሰኝነት

ወጣትነት፣ በማወቅና በመፈተሽ ጉጉት የተሞላ፣ ብርቱ ምኞት፣ ያልተብላላ ውስጣዊ ሃይልና አይበገሬ እልህ በአንድነት የሚገኝበት ዓለም ነው፡፡ ይህን የወጣትነት ዓለም ያላግባብ ከሚያበላሹት ነገሮች መካከል አንዱ ሱሰኝነት ነው፡፡

አንድ ሰው ሱሰኛ ሆነ የሚባለው አንድን ነገር ደጋግሞ በመጠቀሙ ከወሰደው ነገር ጋር ሲላመድና ከመላመድም የተነሳ ብርቱ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ቁርኝት ሲፈጥር ነው፡፡ አንድ ሰው ሱሰኛ ሲሆን የሰውነቱ የመቋቋም ሃይል ይቀንሳል፡፡ ያን ያስለመደውን ነገር አምጣ አምጣ የሚል ስሜት ይሰማዋል፡፡

በሃገራችን የተለመዱት ሱስ አምጪ የሚባሉት ዕፀ ፋሪስ (ካናቢስ)፣ ጫት፣ ትንባሆና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ በኢንዱስትሪ የሚፈበረክ አለ፡፡ እንደ ጤና ባለሙያዎች አስተያየት ሄሮይን የተባለው ዕፅ በህጋዊ መንገድ ይፈበረካል፡፡ በአግባቡ ስንጠቀምበትም ለህክምና አገልግሎት ይውላል፡፡ ለምሳሌ፣ የማደንዘዣ መድሃኒቶች የሚመረቱት ከዚህ ንጥረ ነገር ነው፡፡

ለእነዚህ ሱስ አምጪ ዕፆችና ንጥረ ነገሮች በይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህረሰብ ክፍሎችን ስንመለከት ወጣቶች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ የተጠና ጥናት እንደሚያመለክተው ጫት፣ የአልኮል መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ሃሺሽና በአፍንጫ የሚሸተቱ ንጥረ

ነገሮች ይዘወተራሉ። ዋናዎቹ ተጠቃሚዎች ደግሞ ከ19-24 ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች መሆናቸው በጥናቱ ተመልክቷል።

ወጣቶች በሱስ እንዳይጠመዱ፣ ምን መደረግ አለበት የሚለው አሳሳቢ ጥያቄ ነው። መፍትሄው እንዲህ ቀላል አይደለም። ለመፍትሄው ቅድሚያውን ድርሻ የሚወስዱት ወጣቶች ራሳቸው ናቸው።

ሌላው የመፍትሄ አካል ቤተሰብ ነው። በአሁኑ ጊዜ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሰጡት ጊዜ እያነሰ ነው። ለኑሮ ስኬት፣ በትምህርት፣ በማህበራዊ ጉዳዮች ተሳትፎ በብዛት ስለሚጠመዱ ለልጆቻቸው የሚሰጡት ጊዜ አጭር ነው። የልጆቻቸውን ዕለታዊ ህይወት በጥንቃቄ መከታተል ስለማይችሉ የልጆቻቸውን መበላሸት የሚያውቁት ከመሸ በኋላ ነው። ይህ እንዳይሆን ወላጆች ለልጆቻቸው ሰፊ ጊዜ በመስጠት ዕለት በዕለት የልጆቻቸውን መውጫና መግቢያ መከታተል ይኖርባቸዋል።

(የሃዋሳ ከተማ አስ.ፋ.ኢ.ል. መምሪያ፣ የስነ ህዝብ ጉዳዮች ማስተባሪያና መተግበር ዋና የስራ ሂደት፣ ቅፅ 1፣ ቁጥር 2፣ በየዓመቱ የሚታተም፣ ለዚህ ስራ እንዲሆን ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

### ድህረ ማንበብ ተግባር

1. በቅድመ ማንበብ በደብተርህ/ሽ የገለበጥከውን/ሽውን ሰንጠረዥ በሶስተኛው አምድ ላይ፣ ‹‹ስለ ወጣትነትና ሱሰኝነት ያወቅሁት›› የሚለውን በመሙላት ለክፍሉ አቅርብ/ቢ።
2. ቀጥሎ ምንባቡን በፍጥነት በድጋሚ በማንበብ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ከተሰጧቸው አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።

   1. ሱስ ምንድነው?

      ሀ. አንድን ዕቃ ደጋግሞ ከመጠቀም ጋር የተያያዘ ነው።

ለ. ዕፆችን አዘውትሮ ከመጠቀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡
ሐ. አልኮል ነክ መጠጥ ማዘውተር ነው፡፡
መ. ለ ና ሐ መልሶች ናቸው

2. በሃገራችን የተለመዱ ሱስ አምጪ (የሚያስይዙ) የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

ሀ. ካናቢስ ለ. ጫት ሐ. ትንባሆ መ. ሁሉም

3. ወጣቶች በሱስ እንዳይጠመዱ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. እንዳይጎዱ ለ. እንዳይያዙ
ሐ. እንዳይታሰሩ መ. ለ ና ሐ መልሶች ናቸው

4. በምንባቡ መሰረት ይበልጥ ለሱስ ተጋላጭ የሆኑ የማህረሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ጎልማሶች ለ. አዛውንት
ሐ. ወጣቶች መ. ሀ ና ለ

3. ቀጥሎ ለተሰመረባቸው ቃላት በምንባቡ መሰረት ፍቺ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ወላጆች የልጆቻቸውን መበላሸት የሚያውቁት ከመሸ በኋላ ነው፡፡
ለ. ወጣትነት ውስጣዊ ሃይልና አይበገሬ እልህ የሚገኝበት ዓለም ነው፡፡

# ክፍል አራት፤ መፃፍ

## የግል ደብዳቤና ማመልከቻ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- የግል ደብዳቤና ማመልከቻዎችን መመሪያዎችን ተከትለህ/ሽ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

### ማስታወሻ፤ የግል ደብዳቤ

- የግል ደብዳቤ፣ የግለሰብ ደብዳቤ ሲሆን በቅርብ ከምናገኛቸው ወዳጆቻችን ወይም ዘመዶቻችን ጋር መልዕክት የምንለዋወጥበት፣ የደብዳቤ ዓይነት ነው፡፡
- የደብዳቤ አፃፃፍ ሁኔታ በላኪውና በተቀባዩ መካከል ባለው ግንኙነት ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ፣ አንዳንድ ሰዎች ያላቸው ግንኙነት የጓደኝነትና የዚያን ያህል ቅርበት ያለው ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ የወላጅና የልጅ ግንኙነት አላቸው፡፡ በተወሰነ ምክንያት ገና በደብዳቤ የሚተዋወቁም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
- ስለዚህ የሃሳብ አገላለፁ በሚፃፍበት ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን መልዕክት በሚያስተላልፈውና መልዕክቱን በሚቀበለው ሰው መካከል እንዳለው ግንኙነት ይወሰናል ማለት ነው፡፡
- ያም ብቻ አይደለም፡፡ የደብዳቤው አካሄድ የሚፃፈውን ጉዳይ በሚመለከት ሁለቱም አካላት ባላቸው ዕውቀት ላይም ይመሰረታል፡፡ ላኪውና ተቀባዩ ስለሚፃፈው ጉዳይ በጋራ የሚያውቁት ካልሆነ (ላኪው/ፀሃፊው ብቻ የሚያውቀው ከሆነ) የሚፃፍበት መንገድ ለየት ይላል፡፡ አንባቢውን ለማሳወቅ በማብራራትና በማስረዳት ላይ የተመሰረተ

አቀራረብ ይከተላል፡፡ ሁለቱም ስለሚያውቁት ጉዳይ የሚፃፍ ከሆነ ግን አያስረዳም፡፡ ‹‹ያ ጉዳይ…፣ ነገሩ፣ ወዘተ.›› እያለ ያልፈዋል፡፡

- በደብዳቤ ውስጥ የአድራሻ አፃፃፍም የተወሰነ ስርዓት አለው፡፡ ደብዳቤው በሚፃፍበት ወቅት ከበስተቀኝ ጫፍ ላይ ደብዳቤው የተፃፈበት ቀን፣ ከቀኑ ስር የላው ሙሉ ስም፣ በላኪው ስም ስር አድራሻው (የመልዕክት ሳጥን ቁጥር፣ የሚገኝበት ቦታ) ይቀርባል፡፡

- የላኪው አድራሻ ባለቀበት መስመር (ከስሩ) በስተግራ የወረቀቱ ጫፍ የተቀባዩ ስምና አድራሻ ይፃፋል፡፡ ከስሩ ወረድ ብሎ ሰላምታ ይቀርባል፡፡ ሰላምታ፣ የደብዳቤ መግቢያ አካል ነው፡፡ ከሰላምታ ቀጥሎ ደብዳቤው የተፃፈበት ምክንያት፣ ማለትም የደብዳቤው ይዘት ይቀርባል፡፡ ሃሳቡ በሚገባ ተብራርቶ ይቀርባል፡፡

- በመጨረሻም የመገናኘት ተስፋ፣ የመሰነባበቻ ቃላትና ፊርማ በመደምደሚያው ክፍል ይቀርባል፡፡

የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከት/ቺ።

## የደብዳቤ የውስጥ ይዘት

29/9/2013
ከተማሪ ጳውሎስ ደስታ
የመ.ሳ.ቁ. 189
ሃዋሳ

ለተማሪ ማሳንቱ አርጎ
የመ.ሳ.ቁ. 41
አርባ ምንጭ

ውድ እህቴ ማሳንቱ እንደምን ከርመሻል? እኔ ፈጣሪ ይመስገን ደህና ነኝ። ባለፈው ጊዜ ከአንቺ ዘንድ ስመለስ ካጋጠመኝ የመጓጓዣ ችግር ውጪ ሃዋሳ በሰላም ገብቻለሁ። ማሳንቱዬ፣ የአርባ ምንጭ ሙቀት እንዴት ይዞሻል?

እንግዲህ ትኩረትሽን በስራ ላይ አድርጊ። በተሰማራሽበት መስክ ውጤታማ ለመሆን ጥረት ማድረግ ይኖርብሻል። ጥሩ ስራ ጥሩ ፍሬ ይኖረዋል፤ ፍሬው ለራስም ለሌላውም ነው። በይ፣ ጥሩ ጓደኛ በጥንቃቄ ምረጪ።

ስለ ሃዋሳ መቼም አትጠይቂኝም፤ ታውቂዋለሽና። አሁን አየሩ ትንሽ ቀዝቀዝ እያለ ነው። ለማንኛውም ደብዳቤ መፃፍ እንዳትረሺ።

በተረፈ አምላክ በሰላም ለመገናኘት ያብቃን። ደህና ሁኚ።

ያንቺው
ፊርማ
ጳውሎስ ደስታ

ይህ ደብዳቤ በዚህ መልኩ ከተፃፈ በኋላ በፖስታ (በኤንቨሎፕ) ታሽጎ በሁለት ዓይነት መንገድ አድራሻ ተፅፎ ይላካል፡፡ አድራሻው ሲፃፍ ከፖስታው ጀርባ የተቀባዩ አድራሻ፣ ከፊት ለፊት በማሸጊያው በኩል የላኪው አድራሻ ይፃፋል፡፡ ይህ አቀራረብ ግን እየቀረ መጥቷል፡፡ ሁለተኛውና አሁን በስፋት የሚዘወተረው የአፃፃፍ ስልት አድራሻዎቹ (የላኪውና የተቀባዩ) በፖስታው ጀርባ ይፃፋሉ፡፡ ይህም ለፖስታ ቤት ስራ ቅልጥፍና የሚመች በመሆኑ ዛሬ ግለሰቦችና መስሪያ ቤቶች በዚህ ስልት ይጠቀማሉ፡፡

በፖስታው ጀርባ የላኪው አድራሻ በግራ ጫፍ፣ የተቀባዩ ደግሞ የላኪው በሚያልቅበት ትይዩ በቀኝ በኩል ይፃፋል፡፡ በቀኝ ጫፍ ላይ ቴምብር ይለጠፋል፡፡

ቴምብር

የላኪው አድራሻ

________________

________________

የተቀባይ አድራሻ

________________

________________

1. ከላይ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ አንድ የግል ደብዳቤ ለጓደኛህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

**ማስታወሻ፤ ማመልከቻ አፃፃፍ**

- የማመልከቻ ደብዳቤ ሲፃፍ፣ በስተቀኝ ጫፍ ላይ ቀን ይፃፋል፡፡ ዝቅ ብሎ፣ በርሱ ትይዩ፣ በስተግራ ጫፍ የምናመለክትበት አካል አድራሻ ይፃፋል፡፡
- ከዚያ ስር የአመልካቹ ስም ይፃፋል (ይህ ግን ሁል ጊዜ ላይኖር ይችላል)፡፡ ቀጥሎ፣ ማመልከቻው የሚቀርብበት

ምክንያት ይፃፋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ፣ ‹‹ጉዳዩ፣ …›› በማለት ይጀምራል፡፡ ‹‹ርዕሰ ጉዳዩ …›› የሚሉም አሉ፡፡ ሁለቱም ያስኬዳሉ፡፡ በዚህ ክፍል የምናመለክትበት ዋና ጉዳይ በአጭሩ እንደ ርዕስ ይቀርባል፡፡

✍ በአዲስ መስመር፣ እንደ አንቀፅ፣ የማመልከቻውን ዝርዝር ሃሳብ እናቀርባለን፡፡ ጉዳዩን ለሚያነበው ሰው ካለፈ ወይም ቀድሞ ከሚታወቅ ሁኔታ ጋር አያይዞ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በጣም በአጭሩ፡፡ ማብራሪያ የሚያስፈልግ ከሆነ በጥቂት ዓረፍተ ነገሮች ብቻ ይቀርባል፡፡ ማመልከቻ በባህርዩ አጭር ነው፡፡ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን ለማግኘት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

✍ ዋና ሃሳቡ ከቀረበ በኋላ በመጨረሻ፣ የፃፈው ሰው ሙሉ ስሙንና ፊርማውን ያኖራል፡፡ በግርጌ በስተቀኝ ይፃፋል፡፡ ፊርማ ይቀድማል፤ ስም በፊርማው ስር ይፃፋል፡፡

2. የሚከተለውን ፅሁፍ በማስተዋል ተመልክተህ/ሽ ከግል ደብዳቤ ጋር ያለውን ልዩነት በፅሁፍ አቅርብ/ቢ፡፡

ቀን ____________

ለ ________________ ትምህርት ቤት

ሀዋሳ

ከተማሪ ________________

**ጉዳዩ፣ በትምህርት ቤታችሁ ገብቼ እንድማር ስለመጠየቅ**

ቤተሰቦቼ በስራ ምክንያት ወደዚህ ከተማ ተዛውረው መጥተዋል፡፡ እኔም ከቤተሰቦቼ ጋር ከነበርኩበት ትምህርት ቤት መሸኛ ይዤ ስለመጣሁ፣ በትምህርት ቤታችሁ በሰባተኛ ክፍል ገብቼ እንድማር እንድትፈቅዱልኝ በትህትና አመለክታለሁ፡፡

ፊርማ ________

ተማሪ ____________

3. አንድ የማመልከቻ ደብዳቤ ፅፈህ/ሽ ለክፍሉ አቅርብ/ቢ፡፡

## ክፍል አምስት፣ ስነ ቃል

### ቃላዊ ግጥሞች

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የቃላዊ ግጥሞችን ምንነት ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- የቃላዊ ግጥሞችን ጭብጥ ታስረዳለህ/ታስረጂያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ የስነ ቃል ምንነትና ዓይነት**

ስነ ቃል ምንድነው? ስነ ቃል፣ በመነገር ወይም በመዜም ስለ ተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የሚያወሳ ቃላዊ ፈጠራ ነው፡፡ የአንድን ማህረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ጥበብ ነው፡፡

- የስነ ቃል ምንጭ የማህረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞችና አካባቢው ወይም ተፈጥሮ ነው፡፡ ከስነ ቃል መካከል ቃላዊ ግጥሞች የሚባሉት ይገኛሉ፡፡ ‹‹ቃላዊ›› የተባለው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይፃፍ በአፍ እየተነገረ መተላለፉን ያሳያል፡፡ ‹‹ግጥሞች›› የሚለው ደግሞ የሚቀርብበትን ቅርፅ ያሳያል፡፡
- በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ በሌሎቹም ስራዎች ላይ የሚዜሙና በግጥም የሚነገሩ ስነ ቃሎች፣ በክብት ስምሪት ጊዜ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች፣ በሰርግ፣ በልጆች ጨዋታ የሚዘፈኑ ዘፈኖች፣ ወዘተ. ሁሉ በስነ ቃል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ለተወሰኑት ምሳሌ ማንሳት እንችላለን፡፡
- የስራ ግጥሞች ከሚባሉት መካከል የበሬ ውዳሴ ግጥም

  በሬ ካላንተማ አያ ካላንተማ፣  
  ዓይንም አያይልኝ ጆሮዬም አይሰማ፡፡
- ስነ ቃል ከሚቀርብበት መንገድ የተነሳ የተለያዩ ዓይነቶችም አሉት፡፡ ከነዚህ መካከል ተረት፣ አፈ ታሪክ፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ እንቆቅልሽ፣ የስራ ዘፈን፣ የሰርግ ዘፈን፣ የለቅሶ ግጥም፣ የልጆች ጨዋታና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

1. የሚከተሉትን በአጭሩ መልስ/ሺ፡፡

   ሀ. ስነ ቃል ምንድነው?

   ለ. የስነ ቃል ዓይነቶችን ዘርዝር/ሪ፡፡

   ሐ. ቃላዊ ግጥም ምንድነው? ምሳሌ እየሰጠህ/ሽ አስረዳ/ጂ፡፡

2. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች የያዙትን ሃሳብ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት አስረዳ/ጂ።

ምሳሌ፣ ኧረ ደግ ሚዜ ደግ ባልንጀራ፣
እርሻ እረስ እያለ ያበላል እንጀራ።
ከሁሉም ከሁሉም እርሻ ደግ ብላት፣
አፈር መስሎ ሰርቶ ጌታ መስሎ መብላት።

ይህ ግጥም የስራ ግጥም ነው። በቃል ግጥሙ ውስጥ የተገለፀው ሃሳብ ለእርሻ ስራ የተሰጠን ክብር ያሳያል። የእርሻ ስራ ከባድና የሰሪውን መውጣትና መውረድ የሚጠይቅ ቢሆንም በመጨረሻ ግን ከችግር ነፃ ሆኖ ወይም እንደ ጌታ ሆኖ ሳይቸገሩ እንጀራ ለመብላት ያስችላል የሚል ነው።

ሀ. የኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት፣
አንድ ዓመት ሞላኝ እርሱን ሳነክት።

ለ. ሙሽሪት ለምዳለች ሙሽሪት ለምዳለች፣
እንዝርቷን ደጋኗን ላኩልኝ እያለች።

ሐ. እንኳን ጥሬውን ያብላው ዱቄቱን፣
በሬ አይደለም ወይ ያቃናው ቤቱን።

# ምዕራፍ አምስት

## የስደት አስከፊነት

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ያዳመጥከውን/ሽውን ግጥም መልዕክት አስፋፍተህ/ሽ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡
- እያዳመጥህ/ሽ ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን በማስታወሻ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ስደት ምንድ ነው?
ለ. ከአካባቢህ/ሽ የተሰደደ ሰው ታውቃለህ/ታውቂያለሽ?

#### ሂደተ ማዳመጥ ተግባር

መምህሩ የሚያነብልህን/ሽን እያዳመጥህ/ሽ ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. የግጥሙን ርዕስ ተናገር/ሪ፡፡
ለ. በግጥሙ ውስጥ ያለው/ችው ገፀ ባህርይ የሚገኘው/ምትገኘው የት ነው?

## ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. ባዳመጥከው/ሽው ግጥም መሰረት የቡድን ውይይት በማድረግ ለሚከተሉት ሃረጋት ፍቺ ስጥ/ጪ።

   ሀ. የትዝታ ሻማ ሲበራ በላዬ
   ለ. ሆዴን ባር ባር አለው

2. ያዳመጥከውን/ሽውን ግጥም መልዕክት አስፋፍተህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

3. ቀጥሎ የቀረቡትን ጅምር ዓረፍተ ነገሮች አዳምጠህ/ሽ ቀሪውን ሃሳብ አሟላ/ዪ።

   ሀ. ዓለሚቱ የጓደኛዋን የአሚናን ወደ አረብ ሃገር መሄድ ተመልክታ ______________________________።
   ለ. ሴሳ በፈተና ሰሞን ከምታደርጋቸው ድንቅ ተግባራት ውስጥ __________________________________።

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- በሚና ጨዋታ በሚኖር ምልልስ ውስጥ ያለን ረዥም የንግግር ሚና በአግባቡ ትወጣለህ/ትወጪያለሽ።

ቀጥሎ የቀረበውን የትጉህ ሰዓት አክባሪ ተማሪና የአርፋጅ (የግድ የለሽ) ተማሪ ምልልስ ሚና ወስደህ/ሽ ዝግጅት በማድረግ በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርብ/ቢ።

- የትጉህ ሰዓት አክባሪ ተማሪን ሚና ሴሳ ትወክላለች።
- የአርፋጅ (ግድ የለሽ) ተማሪን ሚና ጋቢሶ ይወክላል።

**ሴሳ፣** ሁልጊዜ የሚያረፍዱ ተማሪዎች ይገርሙኛል፡፡ እኛ ሴቶች አንዳንድ ጊዜ ብናረፍድ እንኳን በቤታችን ውስጥ ሃላፊነቶች ስላሉብን ነው፡፡ አንተ ከኛ ክፍል ሁልጊዜ አርፍደህ ትመጣለህ፡፡ ለምንድነው የምታረፍደው? ወላጅም አምጥተህ ነበር፡፡

**ጋቢሶ፣** እኔ ከመኝታዬ የምነሳው ፀሃይ ሞቅ ሲል ነው፡፡ በጠዋት ተነሳሁ ከተባለ በ1፡30 ላይ ነው የምነሳው፡፡ በጠዋት መነሳት በራሱ ችግር ነው፡፡ ብርዱ ያስፈራል፡፡ የጠዋት እንቅልፍ ደግሞ ደስ ይላል፡፡ አንቺ ቶዩ በጠዋት መተኛት አትወጂም?

**ሴሳ፣** ከመተኛትና ከመማር የቱ ይበልጣል? ሌሊቱን ሙሉ ተኝተህ አድረህ ቀኑን እንዴት በመተኛት ታሳልፋለህ? እኛ ቤት ሁላችንም ከአንድ ሰዓት በፊት ተነስተን ማከናወን ያሉብንን ተግባራት እናከናውናለን፡፡ ልክ 1፡30 ሲሆን ደብተሮቻችንን ይዘን ወደ ትምህርት ቤታችን እንሄዳለን፡፡ አንድ ልጅ እንኳን ካረፈደ ወላጆቻችን ይቆጣሉ፡፡ እኔ የሚመስለኝ አንተ የምታረፍደው ትምህርት ስለማትወድ ነው፡፡

**ጋቢሶ፣** እንዲያው አንቺ ስታስቢው ትምህርት ምኑ ይወደዳል? በክፍል ውስጥ መምህራን ጥያቄ ሲጠይቁ ያለው ጭንቀት፣ ሳረፍድ ከፈረቃ መሪው ጋር ያለው ግብግብ ፣ ከአለቃችን ጋር ያለው ጭቅጭቅ … ስንቱን ልንገርሽ? እንዲያው ጓደኞቼ በልጠውኝ ሲሄዱ እንዳይቆጨኝ ብዬ ነው እንጂ ወደ ትምህርት ቤት የምመላለሰው፡፡ ከስምንተኛ ክፍል በኋላ እኔ አልማርም፡፡ የምን ጭንቀት ነው!

**ሴሳ፣** ያንተኮ ትልቁ ችግር በጥረትህ ማሸነፍ የምትችለውን ተግባር ሁሉ እንደ ችግር መቁጠርህ ነው፡፡ እስቲ ለአንድ ሳምንት

ብቻ በጠዋት ለመነሳት ሞክር፡፡ በየዕለቱ የተማርከውን ደግሞ ወዲያው በየዕለቱ አጥና፡፡ የቤት ስራህንም በወቅቱ ስራ፡፡ ከዚያ በኋላ በመማር የሚገኘውን ደስታ ታያለህ፡፡

ጋቢሶ፣ እሺ! አንቺ ካልሽ ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡ የሚከብደኝን ነገር ግን እንደምታስረጂኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ከምንባቡ የወጡ አዳዲስ ቃላት ፍቻቸውን በምንባቡ አውድ መሰረት ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- ምንባብ ለደረጃው በሚመጥን ፍጥነት፣ ትክክለኝነትና ተገቢ አገላለፅ ታነባለህ/ታነቢያለሽ፡፡

### ቅድመ ማንበብ ተግባር

‹‹የስደት አስከፊነት›› የሚለውን የምንባብ ርዕስ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ሰው ከሃገሩ ወደ ሌላ ሃገር የሚሰደደው ለምንድን ነው?

ለ. የስደት አስከፊነትን በሚመለከት ያለህ/ሽ አጠቃላይ ግንዛቤና ስሜት ምንድነው?

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተርህ/ሽ ላይ በማስፈር በውስጡ ላሉ ቃላት፣ ምንባቡን እያነበብህ/ሽ በምንባቡ መሰረት ፍቺ ስጥ/ጪ።

| ተ.ቁ. | ቃል | ቃላቱ በምንባቡ አገባብ ያላቸው ፍቺ |
|---|---|---|
| 1. | እርም | |
| 2. | የትየለሌ | |
| 3. | የዜና አውታር | |

## የስደት አስከፊነት

አራት መቶ ሺህ ያህል ኢትዮጵያውያን ይገኙባታል የምትባለው ሳውዲ አረቢያ የዓለማችን ዜጎች በብዛት ከሚሰደዱባቸው አሜሪካ፣ ሩሲያ፣ ጀርመን፣ ካናዳ፣ እንግሊዝ ተርታ ተሰልፋለች፡፡

ሃገሪቱ ለስደተኛ አያያዝ የከፋች ብትሆን እንኳን ኢትዮጵያውያን ሴቶች በተለይም የኮሌጅ ትምህርት ያልተማሩት አሁንም ቢሆን ለመሰደድ ይመርጧታል፡፡ ምርጫቸው ግን ከድህነት ለማምለጫ እንጂ እንደ ምኞታቸው ለነርሱ አንጊ ሆና ስለተገኘች አይደለም፡፡ ስደታቸው በበቂ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በሃገሪቱ፣ እንኳን በህገ ወጥነት የሄዱ ቀርቶ ህጋዊ ሰነድ ያላቸውም የአካልና የስነ ልቦና፣ ወዘተ. ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ ብዙዎች የወሲብ ጥቃትና ሌሎች የአካል መጉደል ጥቃት ይደርስባቸዋል፡፡ በአሰሪዋ ከከፍተኛ ፎቅ ተገፍትራ ተጥላ ሞተች፤ አሰሪዋ አስገድዶ ደፈራት፤ ነፍሰ ጡር ስትሆን ተባረረች፤ የፈላ ውሃ ተደፋባት፤ ባልሞት ባይ

ተጋዳይነት አሰሪዋን ገድላ በስቅላት ተቀጣች፣ ወዘተ. የሚሉ ዓይነት ዜናዎችን መስማት የተለመደ ነው፡፡ ድህነትን ለማምለጥ፣ ለቤተሰብ ቀን ለማሳለፍ ብሎ እንዲህ በቀላሉ ህይወት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡

ወላጆች ከብትና ሌላም ንብረት ሸጠው ገንዘቡን ለደላላ በመክፈል ልጆቻቸውን ይሰዳሉ፡፡ አንዳንዱም መኪናውን ሸጦ የተሻለ ለማግኘት በሚልም የሚሰደድም አለ፡፡ እዚህ ላይ ስደተኞች ምን ያህል ተሳካላቸው ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው፡፡ በሃገር ውስጥ ሰርቶ መለወጥን ቢያስቡ ደግሞ የላቀ ብልህነት ይሆናል፡፡

የስደት አስከፊነትን ከቀመሱ ወጣቶች አንዷ ሶፊያ ሃሰን ናት፡፡ ሶፊያ ለዜና አውታር በሰጠችው አስተያየት ‹‹እርም! ስደት አልመለስበትም›› ብላለች፡፡ ምክንያቷን ተጠይቃም፣ ‹‹ማደግና መለወጥ የምፈልገው በሃገሬ ነው፤ ሰው አለ ሃገሩ የሚቆጠረው እንደ ዕቃ ነው፡፡ በሳውዲ ማጎሪያ ሲያስገቡን ለአፍታም ያህል እንደ ሰው የተመለከተን የለም›› በማለት ገልፃለች፡፡ ለዚህ መፍትሄው ህጋዊ ሆኖ መሄድ ሊመስል ይችላል፡፡ ይሁንና ህጋዊ ሆነው ሄደውም መከራና እንግልት የሚደርስባቸው የትየለሌ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ፣ ዜጎች ዓይናቸውን ወደ ስደት እንዳያዞሩ ማህበራዊና የስነ ልቦናዊ ድጋፎችን ማድረግ ግድ ይላል፡፡ ይህ ሲሆን ዜጎቻችን የስደት ኑሮ ለምኔ ማለት ይጀምራሉ፡፡ በሃገር ላይ ሰርተው መክበርና መከበርንም ይለምዳሉ፡፡


(ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ቁጥር 176፣ የካቲት 27/ 2012 እትም፣ ለስራው በሚስማማ መልኩ ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ)

## ድህረ ማንበብ ተግባር

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሃረጋት በምንባቡ መሰረት ፍቻቸውን ስጥ/ጪ።

ሀ. የትየለሌ
ለ. እርም
ሐ. የዜና አውታር
መ. ህገ ወጥነት
ሠ. አልሞት ባይ ተጋዳይ

2. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሰንጠረዥ በምሳሌው መሰረት በተገቢ የምክንያትና ውጤት ሃሳብ ከሌሎች ጋር በመሆን አሟላ/ዪ። ከዚያም በአንድ አንቀፅ በራስህ/ሽ አገላለፅ ፃፍ/ፊ።



3. ‹‹የስደት አስከፊነት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንቀፅ ሁለትንና ሶስትን በቡድን በመሆን አንብበህ/ሽ ድምፅህን/ሽን ከፍ አድርገህ/ሽ አንብብ/ቢ።
4. መምህርህ/ሽ በሚሰጥህ/ሽ መመሪያ መሰረት አንቀፅ ሁለት፣ ሶስትና አራትን ድምፅህን/ሽን ከፍ በማድረግ ለክፍሉ በትክክል በተገቢ አገላለፅና ፍጥነት አንብብ/ቢ።

**ማስታወሻ፤ ስቀላጥፎ ማንበብ (ትክክለኛነት፣ ፍጥነት፣ አገላለፅ)**

- አንድ ተማሪ አንድን ፅሁፍ ለደረጃው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለፅ ሊያነበው ይገባል። ፍጥነት የሚባለው፣ አንድ ተማሪ በአንድ ፅሁፍ ውስጥ በአንድ ደቂቃ ሊያነበው የሚገባ የቃላት መጠን ነው። ተማሪዎች በአንድ ደቂቃ ሊያነቡት የሚገባ የቃላት መጠን በየደረጃው የተለያየ ነው። በሰባተኛ ክፍል፣ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችም በግምት ከሰባ ያላነሰ ቃላትን ማንበብ እንዳለባቸው ይታሰባል።

- ትክክለኛነት ደግሞ ቢቻል ያለ ስህተት፣ ካልሆነም በአነስተኛ የስህተት መጠን ማንበብ ማለት ነው። በማንበብ ሂደት ስህተት የሚባለው ቃላትን ደግሞ መጥራት፣ የፊደልን ድምፅ ሳይጠብቁ ማንበብ፣ መንተባተብ፣ ከቃሉ ውስጥ ፊደል ማጉደል፣ በቃሉ የሌለ ፊደል መጨመርና የመሳሰሉ ናቸው።

- ተገቢ አገላለፅ የሚባለው ደግሞ የፅሁፉን ሃሳብና በቃላቱ ውስጥ ያለን ስሜት ማሳየት ወይም መግለፅ በሚችል መልኩ ማንበብ ማለት ነው።

5. ‹‹የስደት አስከፊነት›› ከሚለው ምንባብ የተረዳከውን/ሽውን የአንቀፅ አፃፃፍን ደንብ በጠበቀ መልኩ በአንድ አንቀፅ ፃፍ/ፊ፡፡

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

### የሌላን ሰው ታሪክ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤት**

- ስለ ታዋቂ ሰዎችና አርበኞች መረጃን በመሰብሰብና በማደራጀት ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ የሰዎችን ታሪክ መፃፍ**

- ስለ ሰዎች የህይወት ታሪክ ለመፃፍ ስንነሳ በመጀመሪያ የምንፅፍበትን ምክንያት እንወስናለን፡፡ ዓላማ ወይም ምክንያት፣ ያን ታሪክ በመፃፍ ማሳየት የምንፈልገው ጉዳይ ነው፡፡

- ከዚህ በኋላ ስለ ሰውዬው ከቤተሰቡ ጀምሮ፣ ስለ ልደቱና አስተዳደጉ፣ ስለትምህርት ቤቱና ስለሚኖርበት አካባቢ፣ ስለቤተሰቡ የኑሮና የእምነት ሁኔታ፣ ስለ ባህርዩና ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ መረጃ መሰብሰብ ይገባል፡፡ እነዚህን መረጃዎች መሰብሰብ ወይም አለመሰብሰብ ለመፃፍ በፈለግንበት ዓላማ ይወሰናል፡፡ ማሳየት የምንፈልገው ጥቂት ጉዳይ ከሆነ ለዚያ በሚመጥን መልኩ ብቻ መረጃ እንሰበስባለን፡፡

#### አብዲሳ አጋ

አብዲሳ አጋ በ1929 ዓ.ም በምዕራብ ኢትዮጵያ በወለጋ ተወለደ፡፡ አብዲሳ የኢትዮጵያን ጦር የተቀላቀለው በአስራ አራት ዓመቱ ሲሆን፣ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሲወርር ሃገሩን ለመከላከል በሚደረግ ውጊያ ላይ መሳተፍ ጀመረ፡፡ እጅግ ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎችን ከታጠቀው

የኢጣሊያ ጦር ጋር በሚደረገው ውጊያ ላይ ባጋጠመው የመቁሰል አደጋ በህክምና ላይ ከቆየ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ አንድ ቤት ውስጥ በቁም እስር እንዲቆይ ተደረገ፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ በአብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በጣሊያኑ ግራዚያኒ ላይ የመግደል ሙከራ ከተደረገ በኋላ አብዲሳና ሌሎች ሰላሳ ሰባት የሚሆኑ የቁም እስረኞች ተጠርጣሪዎች ተብለው በከባድ ስቃይ በእስር ቤት ከቆዩ በኋላ በወቅቱ የጣሊያን ግዛት በነበረችው በሶማሊያ በኩል ወደ ሲሲሊ ተወሰደ፡፡ በጣሊያን አገር የጦር እስረኛ ተደረገ፡፡

በጠባቂዎች ጥብቅ ቁጥጥር በሚደረግበትና አብዲሳ አጋ ታስሮ በሚገኝበት እስር ቤት አብሮት ከነበረ ሁሊዮ ከሚባል ዩጎዝላቪያዊ ምርኮኛ ጋር ከእስር ቤት ለማምለጥ የሚያስችል ዕቅድ ያወጣ ጀመር፡፡ እንዲለብሰው የተሰጠውን ብርድ ልብስ ቀድዶ በመቀጣጠል በመስኮት በኩል ከሌሎች ስድስት እስረኞች ጋር ለማምለጥ ቻለ፡፡ ከእስር ካመለጠ በኋላ ከጣሊያን ወታደሮች በመሸሽ ፈንታ በርሱ እቅድ አውጪነትና መሪነት ወደ እስር ቤት ተመልሶ በጠባቂዎቹ ላይ ጥቃት በመፈፀም የታሰሩትን እስረኞች በሙሉ ነፃ አወጣቸው፡፡ የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት በጣሊያን ላይ አስመሰከረ፡፡

ያመለጡት እስረኞች፣ ከእስር ቤቱ ጠባቂዎች በወሰዱት መሳሪያ በመታገዝ፣ የአማፅያንን ጦር ያደራጁ ሲሆን፣ ጦሩን እንዲመራ የተመረጠውም አብዲሳ አጋ ነበር፡፡ ከዚያም በተለያዩ የጣሊያን ወታደራዊ ሰፈሮች ላይ ጥቃት በመፈፀም ወራሪዎቹ ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ያጋጥማቸው ከነበረው የአርበኞች እንቅስቃሴ ባልተናነሰ በሃገራቸው ያጋጥማቸው ጀመር፡፡
አብዲሳ በሌሎችም ግንባሮች ከጠላት ጋር እየገጠመ ድል ሲቀዳጅ ቆየ፡፡ መሪዎቹ በጀግንነቱ ስላመኑበት የአንድ ጦር ዋና አዛዥ

አድርገው ሾመውትም ነበር፡፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ መለያ ምልክት በማድረግ ይጠቀምበትም ነበር፡፡

በዚህን ወቅት የጀርመን ናዚ ስርዓት እየተጋጋለ መጥቶ ነበር፡፡ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመርም ፋሺስት ሞሶሎኒ ከነዚህ ጀርመኖች ጋር አበረ፡፡ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና አሜሪካን ጨምሮ በርካታ የምዕራብ ሃገሮች ደግሞ የህብረት ጦር መስርተው የሞሶሎኒን ጦር መውጋት ጀምረው ነበር፡፡

በወቅቱ ይህ የህብረት ጦር የአብዲሳን ዝና በመስማቱ ጣሊያንን ለማዳከም ሲል ለአብዲሳ ጦር የቁሳቁስ ድጋፍ ያደርግ ነበር፡፡ የጣሊያን ጦር ተሸንፎ ዋና ከተማዋ ሮም በአሜሪካና በእንግሊዝ በሚመራው ጦር እጅ በመውደቋ አብዲሳ አጋም የሚመራውን ጦር ይዞ ወደ ሮም ከተማ ገባ፡፡ በዚያን ጊዜ በዓለም ዓቀፉ የህብረት ጦር አቀባበል ተደርጎለት ነበር፡፡ ከጦርነቱ መገባደድ በኋላም የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግስታት አብዲሳ ጦራቸውን ተቀላቅሎ እንዲቀጥል ለማድረግ በርካታ ጥቅማ ጥቅሞችን አቅርበውለት ነበር፡፡ አብዲሳ ግን ኢትዮጵያ ምንም ያህል ደሃ ብትሆን ህዝቡንና መንግስቱን ጥሎ እንደማይሄድ አስረግጦ በመናገር ጥያቄውን ሳይቀበል ቀረ፡፡ «ተቀላቀለን» የሚለውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ያልተዋጠላቸው አንዳንድ የህብረቱ ጦር አባላት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካበቃ በኋላ በወንጀል ከሰሰውት ወደ እስር ቤት አስገብተውት ነበር፡፡ በኋላም እስሩ ወደ ገንዘብ ቅጣት ተቀይሮ ገንዘቡም ተከፍሎ አብዲሳ ለዓመታት ወደ ተለያት ሃገሩ በክብር ተመለሰ፡፡ ከዚያም በወታደርነት ሙያው ሃገሩን ሲያገለግል ቆይቶ ሌተና ኮሎኔል ማዕረግ ከተቀዳጀ በኋላ በ1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡

(ሺ.በሺ. ለማ፣ አርአያዎች፣ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ፣ 2003፣ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

### ማስታወሻ፤ የምንባቡ ይዘት

✍ በዚህ የአብዲሳ አጋ ታሪክ ለማሳየት የተፈለገው የጀግንነት ውሎው ብቻ ነው። ለሃገሩ ኢትዮጵያ ያደረገውን አስተዋፅኦ ተተኳሪ ነጥብ አድርጎ የቀረበ የህይወት ታሪክ ፅሁፍ ነው። የአብዲሳን የአስተዳደግና የቤተሰብ ሁኔታን፣ የትምህርት ደረጃም ሆነ ሌሎች ከባለ ታሪኩ ህይወት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ፅሁፉ አላነሳም። ስለዚህም አንተ/አንቺ በአካባቢህ/ሽ ስላሉ ታዋቂ ሰዎች ወይም አርበኞች ስትፅፍ/ፊ በዚሁ መሰረት ማሳየት በፈለግከው/ሽው አንድ ጉዳይ ላይ ማተኮር ይኖርብሃ/ሻል። አስቀድሞ ግን ስለ ባለታሪኩ ማሳየት ወይም መፃፍ የፈለግከው/ሽውን ጉዳይ መወሰን ያስፈልጋል።

ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት በአካባቢህ/ሽ ታዋቂ የተባሉ ሰዎችን በመለየትና ስለነርሱ መረጃ በመሰብሰብ በአካባቢያቸው የታወቁበትን ጉዳይ በመግለፅ ከሁለት አንቀፅ ባላነሰ አንድ ታሪክ ፃፍ/ፊ። ጽሁፍህን/ሽን ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አንብብ/ቢ።

## ክፍል አምስት፤ ሰዋስው

### ተውሳከ ግስና መስተዋድድ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የመስተዋድድና የተውሳከ ግስን ምንነት ትናገራለህ/ ትናገሪያለሽ።
- የመስተዋድድና የተውሳከ ግስን አገባብ ትለያለህ/ ትለዪአለሽ።

**ማስታወሻ፤ የተውሳከ ግስ ምንነትና አገባብ**

✍ ተውሳከ ግስ፣ ከቃል ክፍሎች አንዱ ነው። በቃሉ ውስጥ ያለው ‹‹ተውሳክ›› ጭማሪ ማለት ሲሆን፣ ተውሳከ ግስ ማለት ደግሞ በግስ ላይ የተጨመረ ማለት ነው። በሌላ አባባል በግስ ላይ እየተጨመረ ግስን የሚያጎለምስ ወይም የሚገልፅ ማለት ነው። ግስን የሚያጎለምሰውም ከጊዜ፣ ከቦታና ከሁኔታ አንፃር ነው።

✍ አንድ ድርጊት ተፈፀመ ብንል በጊዜ፣ በቦታና፣ በሁኔታ ይከናወናል። ጊዜው መቼ እንደሆነ፣ ቦታው የት እንደሆነ፣ የተከናወነው እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሆነ የሚገልፅ ቃል አብሮት ሲመጣ ተውሳከ ግስ ይሆናል።

✍ ለምሳሌ፤

- አንቻሞ ዛሬ ሄደ።
- አንቻሞ ገና አልመጣም።
- አንቻሞ ልጁን ክፉኛ ጎዳው።

✍ በነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ማሰሪያ ግሱ የያዘውን ሃሳብ በመግለፅ ስለሚያገለግሉ ተውሳከ ግሶች ናቸው።

✍ ጥቂት ተውሳከ ግሶችን በምሳሌነት እንውሰድ።

- ገና፣ ድንገት፣ አሁን፣ ድሮ፣ ቶሎ፣ ክፉኛ፣ ምንኛ

1. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተውሳከ ግሶችንና የተውሳከ ግስ ሚና ያላቸውን ከስራቸው በማስመር ለይ/ዪ።

ሀ. የገበሬው ምርት ዘንድሮ ጨመረ።

ለ. የሰፈራችን ዝነኛ ሌባ ዛሬ ክፉኛ ተደበደበ።

ሐ. ከውጪ የሚመጣውን ወንድማችንን እየጠበቅነው ብንሆንም ገና አልመጣም፡፡

መ. የተላከችው ልጅ ቶሎ መጣች፡፡

ሠ. ሾፌሩ መኪናውን በፍጥነት ነዳ፡፡

## ማስታወሻ፤ የመስተዋድድ ምንነትና አገባብ

- መስተዋድድ እንደ ስሙ በቃላት መካከል የሃሳብ ዝምድና እንዲኖር የሚያደርግ ቃል ነው፡፡ አንዱ ቃል ለብቻው የቆመ ሳይሆን በሃሳብ ከሌላው ጋር እንዲቆራኝ ያደርጋል፡፡ መስተዋድድ በስም ወይም በግስ ላይ እየተቀጠለ ንፅፅርን፣ ምክንያትን፣ መነሻን፣ አቅጣጫን፣ ወዘተ. ሊያመለክት ይችላል፡፡

- ምሳሌ፣
  - ስዩም <u>እንደ</u> ወንድሙ ጎበዝ ነው፡፡
  - ስዩም <u>ስለ</u> ታመመ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ፡፡
  - ዓለሚቱ ደብተሩን <u>ለ</u>ልጅዋ ሰጠች፡፡

- መስተዋድድ ከቅርፅ አንፃር በራሱ ላይ ቅጥያዎችን መውሰድ አይችልም፡፡
  - ግጥም ብለን ግጥም -ኦች፤ ግጥም -ኡ፣ ወዘተ እንላለን፡፡
  - ጥቁር ብለን ጥቁር -ኦቹ፤ ጥቅር -ኡ፣ ወዘተ. እንላለን፡፡

- ለመስተዋድድ ግን በተመሳሳይ መልኩ ማድረግ አንችልም፡፡

2. ቀጥሎ በቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ መስተዋድዶችን ከግርጌያቸው በማስመር አሳይ/ዪ፡፡

ሀ. አሊቶ ከሃዋሳ መጣ፡፡
ለ. ገበሬው ስለ ደከመ ማረፍ ፈለገ፡፡
ሐ. ዳርሳሞ ወደ ከተማ ሄደ፡፡
መ. ስጋውን በቢላዋ ቆረጠ፡፡
ሠ. ለጋስ ለሰጠ ንፉግ ይመቀኛል፡፡

## ክፍል ስድስት፤ ስነ ፅሁፍ

### ግጥም ማንበብና መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የግጥምን ምትና ዜማ ጠብቀህ/ሽ ታነባለህ/ታነቢያለሽ፡፡
- የግጥምን መልዕክት አብራርተህ/ሽ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡

**ማስታወሻ፤ የግጥም አፃፃፍ**

✍ ግጥም የአፃፃፍና የአነባበብ ስርዓት አለው፡፡ ግጥም ሲፃፍ በመጀመሪያ በሃረግና በስንኝ እንደሚፃፍ ይታወቃል፡፡ ሃረጉ ወይም ስንኙ በውስጡ ጎልተው የሚነበቡ ቀለም የሚባሉ ድምፆች አሉት፡፡ እነዚህ ጎልተው የሚነበቡ ቀለሞች በተወሰነ ቁጥር ይገባሉ፡፡ አምስትም ስድስትም ሰባትም፣ እንደ ሁኔታው ከዚያም በላይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቀለሞቹ ቁጥር ምጣኔ ይባላል፡፡ ሃረጉ ወይም ስንኙ የተፃፈበት የቀለም መጠን ለማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ምጣኔው አራት አራት፣ አምስት አምስት፣ ስድስት ስድስት፣ ወዘተ. ሊሆን ይችላል፡፡ እኩል የሆኑ ቀለሞች ተደጋግመው ሲመጡ እንደ መዚቃ ያለ ምት ይፈጥራሉ፡፡ ምት ተመሳሳይ ምጣኔ ወይም ቀለም ተደጋግሞ መምጣት

ነው። ተደጋግሞ ሲመጣ ደግሞ ዜማ ይሆናል።

✍ ስለዚህ ግጥም ሲፃፍ እነዚህ ጠብቆ መፃፍ እንደሚገባ ሁሉ ሲነበብም እነዚህን ጠብቆ ማንበብ ይገባል።

✍ ለምሳሌ፣

እዚያ ማዶ ጪስ ይጨሳል፣

አጋፋሪ ይደግሳል።

የሚለውና

ተመስገን አምላኬ የእንስሳት ፈጣሪ፣

እኔን ያደረግሽኝ የሰማይ በራሪ።

የሚለው አነባበባቸው አንድ ዓይነት አይደለም። የቀለማቸውን ምጣኔ ስንት እንደሆነ ባናውቅ እንኳ በአነባበብ እንደሚለዩ መረዳት እንችላለን።

በአጠቃላይ ግጥም ስናነብ የሚከተሉትን መገንዘብ አለብን።

- የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶች ከመምህራንና ከሌሎች ቦታዎች እየሰሙ መለማመድ፣
- በሃረግ የተከፈለ ግጥም ከሆነ በሃረጎች መካከል ቆምታ ማድረግ፣
- ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ፣
- ግጥሙ የያዘውን ስሜት በሚያንፀባርቅ መልኩ ማንበብ። ለምሳሌ፣ የግጥሙ ስሜት የሃዘን፣ የጀግንነት፣ የፍቅር፣ ወዘተ. ከሆነ ያን ስሜት ማሳየት በሚችል መልኩ ድምፅን ከፍና ዝቅ፣ ጠንከርና ላላ፣ ፈጠንና ጎተት እያደረጉ ማንበብ ይገባል። የቀረርቶና የሃዘን ግጥም በተመሳሳይ ቃና አይነበብም።
- ድምፅ ለሌሎች በሚሰማ መልኩ ማንበብ፣

1. የሚከተለውን ግጥም ምቱን ጠብቀህ/ሽ በዜማ አንብብ/ቢ።

## ፅጌረዳና ደመና

አንዲት ፅጌረዳ ቃልዋን አስተዛዝና፣
እንዲህ ተናገረች ለሰማይ ደመና።
ድርቀት በጣም ጎድቶኝ እዩኝ ስንገላታ፣
እባክህ ጣልልኝ የዝናብ ጠብታ።
ቶሎ ካላራስከኝ ጉልበቴ እንዲጠና፣
ምንም ተስፋ የለኝ መሞቴ ነውና።
አሁን መሄዴ ነው ለትልቅ ጉዳይ፣
ስመለስ መጥቼ ሳልፍ በአንቺ ላይ።
አዘንብልሻለሁ ጠብቂኝ እያለ፣
ምንም ሳይጥልላት መንገዱን ቀጠለ።
ሰውም እንደዚሁ ጭንቁን እያዋየ፣
በችግሩ ብዛት እየተሰቃየ።
ብዙ ጊዜ ኖሮ ቆይቶ ሲጉላላ፣
የሚረዳው አጥቶ ከሞተ በኋላ።
ዘመድ ወዳጆቹ እንባ እያፈሰሱ፣
ሙሾ ቢያወርዱለት በህብረት ቢያለቅሱ፣
ይህ ሁሉ ከንቱ ነው አይጠቅመውም ለሱ።
እውነት ከወደደው ሲቸገር ሲጎዳ፣
በህይወቱ ሳለ ሰው ወዳጁን ይርዳ።

(ከበደ ሚካኤል፣ ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መፅሃፍ፣ ሁለተኛ እትም፣ ገፅ 33)

2. የግጥሙን ሃሳብ (መልዕክት) አብራርተህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

# ምዕራፍ ስድስት

## የሲዳማ ባህላዊ ቤት አሰራር

## ክፍል አንድ፤ አድምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- ፅሁፍ ሲነበብልህ/ሽ አዳምጠህ/ሽ ፍሬ ነገሩን ትለያለህ/ ትለዪአለሽ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች በጥንድ ውይይት በማድረግ ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. የሲዳማ ባህላዊ ቤት ምን ምን ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል?

ለ. ‹‹ጉረኖ፣ ጋጥ እና በረት›› በሚሉት ቃላት መካከል ያሉትን ልዩነቶች ተናገሩ?

### ሂደተ ማዳመጥ ተግባር

መምህርህ/ሽ አንድ ፅሁፍ ያነቡልሃል/ሻል፡፡ ፅሁፉን እያዳመጥህ/ሽ የጽሁፉን ዋና ዋና ሀሳቦች በማስታወሻህ/ሻሽ ላይ ፃፍ/ፊ፡፡

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ፅሁፍ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሽ፡፡

ሀ. በሲዳማ ባህላዊ ቤት ውስጥ የሚሰራው ቆጥ ጠቀሜታው ምንድነው?

ለ. የሲዳማ ባህላዊ ቤት ምን ምን ክፍሎች አሉት?

# ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- በስዕል የቀረበን መረጃ ተመልክተህ/ሽ ሃሳብ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡
- አንድን ይዘት ከተለያየ አቅጣጫ በማየትና በመተርጎም ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡
- ታሪክን አሳጥረህ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡

1. ቀጥሎ የቀረበውን ስዕል በመመልከት የተረዳከውን/ሽውን ሃሳብ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡









2. መምህርህ/ሽ በሚሰጡት መመሪያ መሰረት ኮቪድ 19 በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በሃገር ደረጃ ሊያስከትል የሚችላቸውን ተግዳሮቶች በቡድን ውይይት በዝርዝር በማቅረብ የደረስክበትን/ሽበትን ነጥብ ለክፍሉ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡
3. ቀጥሎ የቀረበውን ታሪክ በዝግታ (በማስተዋል) በማንበብ አሳጥረህ/ሽ በቃል አቅርብ/ቢ፡፡

ማስታወሻ፤ የፅሁፍን ሃሳብ አሳጥሮ መናገር

‹‹ደግ ስራ›› የሚለውን ፅሁፍ አሳጥሮ በንግግር ለማቅረብ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገቡን ነጥቦች አሉ፡፡ ይኸውም፡-

- የሚያጥረውን ፅሁፍ በጥንቃቄ ማንበብ
    - በጥንቃቄ ማንበብ አሳጥረን በንግግር ለምናቀርበው ሃሳብ መሰረት ነው፡፡
    - ሃሳቡን በትክክል ለመጨበጥ እንዲቻል ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡
- ዋናውን ሃሳብ ለይቶ በራስ አገላለፅ ማቅረብ
    - የፅሁፉን ዋና ሃሳብ አሳጥረን በራሳችን ቋንቋና አገላለፅ ማቅረብ ይኖርብናል፡፡
    - ያሳጠርነው ሃሳብ ግልፅ መሆኑንና የፀሃፊው ሃሳብ አለመዛነፉን (አለመቀየሩን) የግድ ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡

## ደግ ስራ

ዕድሜው ገፋ ያለ አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ ሰብስቦ፣ ሃብት አካብቶ ይኖር ነበር፡፡ ይህ ሰው መሞቻው ጊዜ እንደ ተቃረበ አውቆ ሃብቱን ለሶስቱ ልጆቹ አካፈላቸው፡፡ ርስቱንና ገንዘቡን አካፍሎ ሲጨርስ አንድ ዕንቁ አስቀረ፡፡ በሚቀጥሉት ሶስት ወራት በጣም መልካም ወይም ደግ የሆነ ስራ ለሰራ እንደሚሰጥ ነገራቸው፡፡ ጊዜው ሲደርስ ልጆቹ ተሰበሰቡ፡፡

ታላቁ ልጁ ቀረበና፣ ‹‹አባቴ ሆይ፣ አንድ ሰው ከዚህ ቀደም፣ ገና ምንም ሳንተዋወቅ፣ አምኖኝ ብዙ ገንዘብ በአደራ እንዳስቀምጥለት፡፡ ሰጠ ሳስቀምጥለት የደረሰኝ ፊርማዬን አልሰጠሁትም፡፡ መተማመኛ

አልፈረምኩለትም፡፡ ይሁን እንጂ፣ እኔም ከገንዘቡ ምንም ሳልነካበት በጥንቃቄ ጠብቄ አስቀመጥኩለት፡፡ እርሱም በፈለገው ጊዜ ለመውሰድ መጥቶ ሲጠይቀኝ ገንዘቡን እንዳለ መልሼ ሰጠሁት፡፡ ስላስቀመጥኩለት የእምነቴን ዋጋ ቢሰጠኝም አልቀበልም ብዬ መለስሁለት፡፡ አባቴ፣ ይህ ደግ ስራ አይደለምን?›› አለ፡፡ አባትየው፣ ‹‹ይህ የታማኝነት ስራ እንጂ ደግ ስራ ሊባል አይችልም›› አለው፡፡

ሁለተኛው ታናሹ ልጁ ተነሳና፣ ‹‹አባቴ ሆይ፣ አንድ በኩሬ አጠገብ ስሄድ አንድ ህፃን በኩሬው ውስጥ ወድቆ ነፍሱን ለማዳን ሲፍጨረጨር አገኘሁ፡፡ እኔም ለነፍሴ ሳልሳሳ ዘልዬ እኩሬው ውስጥ ገብቼ አዳንኩት፡፡ ለተጨነቀችው እናቱም በደህና ሰጠሁት፡፡ አባቴ፣ ይህ መልካም ስራ አይባልምን?›› አለ፡፡ አባትየውም፣ ‹‹ልጄ፣ በርግጥ ያደረግከው ጥሩ ነው፡፡ ሆኖም ይህ የዘውትር የርህራሄ እንጂ ደግ ስራ ሊባል አይበቃም›› ሲል መለሰለት፡፡

ሶስተኛው ልጅ በተራው ቀረበና እንዲህ አለ፡፡ ‹‹አባቴ ሆይ፣ አንድ ጊዜ ሌሊት በጨለማ በጣም ደመኛ የሆነኝ ጠላቴን በገደል አፋፍ ተኝቶ አገኘሁት፡፡ ተኝቶ ስለነበረ እኔን አላየኝም፡፡ ድንገት ድምፄን ባሰማ ደንግጦ (ባንኖ) ወደ ገደል እንዳይወድቅ ቀስ ብዬ እየተንፏቀቅኩ ተጠጋሁት፡፡ በጠላትነት መንገድ ሳይሆን በወዳጅነት ስሜት ቀስቅሼው ከገደሉ አፋፍ አንስቼ በደህና ስፍራ አስተኛሁት፡፡ ነገር ግን እኔ በጠላትነት መንገድ ቀርቤው ደንግጦ ቢባንን በገደሉ ወድቆ ይሞት ነበር፡፡ እኔ ግን ያ እንዲሆን አልፈለግኩም፡፡ ለደመኛዬ መልካም ለማድረግ ስል ይህን አደረግኩ፡፡ ይህስ አባቴ ደግ ስራ አይባልምን?››

አባትየው በዚህ በትንሹ ልጅ ስራ ደስ ብሎት፣ ‹‹ውድ ልጄ፣ ለጠላትህ መልካም ከማድረግ የበለጠ ምን ደግ ስራ አለ? ልትገድለው ስትችል ከመተው፣ ወደ ገደል ልትከተው ስትችል አቅፈህ ደህና

ቦታ ከማስተኛት የሚበልጥ ደግ ስራ የለም›› ብሎ አቅፎ ሳመው፡፡ ዕንቁውንም ሰጠው፡፡

እንግዲህ ጠላትን መውደድ ከሁሉ የበለጠ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡

(ከበደ ሚካኤል፤ ታሪክና ምሳሌ ሁለተኛ መፅሃፍ፣ ገፅ 9-10፣ ለዚህ ዘመን አገላለፅ እንዲመች መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

4. ቀጥሎ በቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተገለፀውን ሃሳብ በማብራራት በቃል አቅርብ/ቢ፡፡

ሀ. ጥንቃቄዎችን በማድረግ በኮቪድ 19 በሽታ መጋለጥንም ሆነ ስርጭቱን ለመቀነስ ይቻላል፡፡

ለ. በኮቪድ 19 በሽታ የመያዝ ተጋላጭነት ሰዎች እንደሚገኙበት ቦታ የሚለያይ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

### ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የምንባብን ይዘት ታብራራለህ/ታብራሪያለሽ፡፡
- ልዩ ልዩ የማንበብ ስልቶችን ተጠቅመህ በትክክልና በተገቢ ፍጥነት ታነባለህ/ታነቢያለሽ፡፡
- ከምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡

### ቅድመ ማንበብ ተግባር

‹‹የሲዳማ ባህላዊ ቤት አሰራር›› የሚለውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች የጥንድ ውይይት በማድረግ በቃል ተናገር/ሪ፡፡

ሀ. በሲዳማ ማህበረሰብ ቤት ከመጠለያነት ባሻገር ለአንድ ሰው ያለውን ፋይዳ(ጥቅም) ተናገሪ/ር፡፡

ለ. በሲዳማ ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደትን አስረዳ/ጂ፡፡

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

‹‹በሲዳማ ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ›› የሚለውን ምንባብ በአምስት ደቂቃ በአሰሳ የማንበብ ስልት እያነበብህ/ሽ ቀጥሎ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

የሲዳማ ማህበረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር አጀማመር ስርአት ምን ይመስላል?

ማስታወሻ፤ የማንበብ ስልት

የማንበብ ስልቶች የሚባሉት የአሰሳ፣ የገረፍታና የዝግታ (የማስተዋል) ማንበብ ናቸው፡፡

- **የአሰሳ ማንበብ** የሚከተሉት ባህርያት አሉት፡፡
  - የፍጥነት ንባብ ነው፡፡ ደግሞም ከፊል መረጃ በአዕምሮ ይዞ ቀሪውን መረጃ ለማሟላት የሚደረግ የማንበብ ስልት ነው፡፡
  - በዚህ ስልት በማንበብ ሂደት አዕምሮዋችን የሚያተኩረው ለማወቅ ወይም ለማግኘት በምንፈልገው መረጃ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

- **የገረፍታ ማንበብ** እንደ ስሙ ገረፍ ገረፍ ተደርጎ የሚነበብበት ስልት ነው፡፡ ይህም የፍጥነት ንባብ ነው፡፡
  - የተፃፈ ነገር ለሰው የሚጠቅም ቁም ነገር ሊኖረው ስለሚችል ‹‹አንዳች ነገር አገኝ ይሆን?›› በሚል ጉጉት የሚደረግ የማንበብ ስልት ነው፡፡
  - ማስታወቂያዎችን፣ ጋዜጦችን፣ የመፅሄፍ ማውጫዎችን፣ ስዕሎችን፣ ወዘተ. ገረፍ ገረፍ አድርጎ ማንበብ የተለመደ ነው፡፡

- በአጠቃላይ ዓላማው በእይታ ‹‹ትኩረት የሚስብ ነገር አለ ወይ?›› ብሎ ማንበብ ይመለከታል፡፡

**የዝግታ ማንባብ፣** ሌላኛው ስያሜው የማስተዋል ንባብ ነው፡፡

- ጥልቅ ንባብ ወይም በጥልቀት ማንበብ ተብሎም ይታወቃል፡፡ ይህኛው መረጃን ወይም ሃሳብን አብላልቶ እያሰላሰሉ ማንበብን ይመለከታል፡፡
- የሚነበበው ጉዳይ ቢበዛም የአነባበቡ ስልት በዝግታ ነው፡፡ ማስታወሻ መያዝ፣ ደጋግሞ ማንበብ፣ ማሰላሰልን ያካትታል፡፡
- ከትምህርት ጋር በተያያዘ ተማሪዎች ለፈተና ለመዘጋጀት የሚያነቡበት የማንበብ ስልት ነው፡፡

## የሲዳማ ባህላዊ ቤት አሰራር

በሲዳማ ማህበረሰብ ቤት ከመጠለያነት ባሻገር ለአንድ ሰው ገበና፣ ክብር፣ ዝና፣ መታወቂያ፣ የይዞታ ማረጋገጫ፣ መጠሪያ፣ ወዘተ፣ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በደጋማ አካባቢዎች ባሕላዊ የሲዳማ ቤት ከቀርከሀና ከእንጨት የሚሰራ ሲሆን በወይና ደጋና ቆላ አካባቢዎች ግን በእንጨትና በሳር “buuyyo” ይሰራል፡፡ ባሕላዊ የቤት አሰራር እንደ አዲስ ተወጥኖ የሚሰራና ቀደም ተብሎ የተሰራ ቤት ሲያረጅ የሚደረግ ጥገናንም ያካትታል፡፡

በሲዳማ ባሕላዊ ቤት አሰራር የማህበረሰቡ የረቀቀ የአካባቢ በቀል እውቀትና ጥበብ ከሚገለጹባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ቤት ለመስራት የሚያስብ ሰው በመጀመሪያ ለቤቱ ስራ በሱ በኩል የሚጠበቅበትን የመስሪያ ቁሳቁስ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ አዲስ ቤት ለመስራት ያሰበ ሰው አስቀድሞ ለቤቱ ስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማሰባሰብ፣ ማከማቸትና ማደራጀት ይጀምራል፡፡ እነዚህን ዋና ዋና ቁሳቁሶች ቤት ሰሪው የሚያሰባስበው ከራሱና ከቅርብ

ቤተ ዘመድና ከወዳጅ ይሆናል፡፡ ----ከዚህም በተጨማሪ የቤት ስራ መረዳጃ “Seera” አባላት እንደ ውስጠ ደንባቸው የቤት መስሪያ ቁሳቁሶች ሊያቀርቡ ወይም ቤቱ ወደሚሰራበት ስፍራ ሊያጓጉዙ ይችላሉ፡፡

ቤት ሰሪው ለቤቱ ስራ አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶች ካመቻቸ በኋላ ቤቱ የሚቆምበትን ስፍራ በመምረጥ መሰረት እንዲጥልለት ወላጅ አባቱን ይጠይቃል፤ አባት ከሌለው ለአጎቱ ወይም ለሰፈር ሽማግሌ ያማክራል፡፡ ሽማግሌዎቹ የቤቱን አቋቋም፣ ፊት ለፊት የሚኖረው ቦታ ለከብት መውጫና መቆሚያ፣ ለእንቦሳ ጥጃ መቦረቂያ፣ በደስታና በሀዘን ጊዜ ለጥላ ሰፊ ቦታ የሚሆን፣ መውጫና መግቢያ መንገድ መኖሩን፣ እንዲሁም የንፋስን አቅጣጫ በግንዛቤ ውስጥ በማድረግ መሰረት ይጥላሉ፡፡

የሲዳማ ባሕላዊ ቤት መሰረት ሲጣል ፍጹም ክብ እንዲሆን ስለሚፈለግ ምሰሶ ከሚቆምበት የቤቱ መሐል ላይ ባላ ተተክሎና በሚፈለገው ስፋት ልክ በጫማ ተለክቶ በባላው ላይ ገመድ በማሰር ዙሪያውን በማሽከርከር ምልክት ይደረጋል፡፡ ይህም የቅየሳ ስራ ‹gaata dara› ይባላል፡፡ የቤቱን ስፋትም የሚወሰነው የቤቱ ባለቤት ባለው የቤተሰብና የቤት እንስሳት ብዛት ይሆናል፡፡ ሽማግሌዎች ቤቱ ከመጠን በላይ ሰፊ እንዳይሆንና በጣም እንዳይጠብ ያማክራሉ፡፡

(አምባሳደር ማርቆስ ተክሌ እና ሌሎች፣2003፣ የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባህል፣ገጽ 369-370 ለተማሪዎች ደረጃ እንዲመጥን ተደርጎ የተቀነጨበ)

## ድህረ ማንበብ ተግባር

1. አንቀፅ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስትና አራትን በዝግታ (በማስተዋል) በማንበብ የየአንቀፆቹን ዋና ዋና ሃሳብ በፅሁፍ ግለፅ/ጪ።
2. በሲዳማ ባህላዊ ቤት አሰራር የሽማግሌዎች ሚና ምንድነው?
3. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በሶስት ደቂቃ ውስጥ ምንባቡን በአሰሳ የማንበብ ስልት እንደገና በማንበብ መልስ/ሽ።

ሀ. በደጋማ አካባቢዎች ባህላዊ የሲዳማ ቤት ከምን ይሰራል?

ለ. በምንባቡ መሰረት የማህበረሰቡ የረቀቀ የአካባቢ በቀል እውቀትና ጥበብ ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ምንድነው?

ሐ. የመረዳጃ አባላት ሲባል ምን ማለት ነው?

4. አንቀፅ ሶስትና አራት ድምፃዊ (ድምፅን ከፍ አድርጎ) የማንበብ ዓይነትን በመጠቀም አቀላጥፈህ/ሽ ለክፍሉ አንብብ/ቢ።

ማስታወሻ፤ የማንበብ አይነቶች

የማንበብ አይነቶች ሁለት ናቸው።

1. ድምፃዊ ማንበብ
2. የዝምታ (ድምፅ አልባ) ማንበብ ይባላሉ።

**ድምፃዊ ማንበብ** ድምፅን ከፍ አድርጎ፣ ሌሎች እየሰሙ የማንበብ አይነት ነው።

- ይህ አነባበብ የምንባቡን ወይም የፅሁፉን ይዘትና ምስጢር ከአንባቢው ይልቅ አድማጭ እንዲገነዘብ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው።

**የዝምታ (ድምፅ አልባ) ማንባብ** ድምፅ ሳያሰሙ የማንበብ አይነት ነው፡፡

- ይህ የማንበብ አይነት የፀሃፊውን መልዕክት በምናብ እየቀረፁ ወይም በወጉ እየተረዱ ለማንበብ ዓይነተኛ ዘዴ ነው፡፡
- በዝምታ በማንበብ ጊዜ ከንፈራችንን ባናነቃንቅ ይመረጣል፡፡

5. ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላትና ሃረጋት በምንባቡ መሰረት ያላቸውን ፍቺ በፅሁፍ ግለፅ/ጪ፡፡

ሀ. ሃገር በቀል

ለ. ቀርከሀ

ሐ. መቦረቂያ

መ. ገመና

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የህይወት መርህን መሰረት በማድረግ የተቀናጀ አንቀፅ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡
- የአመዛዛኝ ድርሰትን ምንነት ታስረዳለህ/ታስረጂያለሽ፡፡
- በተሰጠህ/ሽ ርዕስ አመዛዛኝ ድርሰት ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

**ማስታወሻ**

- የህይወት መርህ የሚባለው፣ ሰዎች ህይወታቸውን የሚመሩበት እምነት ወይም አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህ አንዳንድ ጊዜ የህይወት ክሂል ይባላል፡፡ ህይወትን የምንኖርበት ስልት ወይም ህይወትን በወጉ የመምራትና የመኖር ችሎታ ነው፡፡
- የህይወት መመሪያ ወይም ክሂል ከሚያካትታቸው መካከል የተወሰኑትን መጥቀስ እንችላለን፡፡

- የራስን ማንነት በወጉ መረዳት፣ ለራስ ተገቢ እሴት (ክብር) መስጠት፣
- በራስ መተማመን (አደርገዋለሁ፤ እችላለሁ ማለት)፣
- ባለን ነገር መርካት (ለመጨመር አለማሰብ ሳይሆን፣ ራስን ከሌሎች ጋር እያነፃፀሩ ምንም እንደሌለን አለማሰብ)፣
- ባለን ነገር (ወረት) ላይ ተመስርቶ ለመጨመርና ለማደግ መጣር፣
- ሌሎችን መውደድና ማክበር፣
- ለጥሩ ምክሮች ጆሮ መስጠት፣ ለመተግበር መሞከር፣
- በአሉታዊ አስተያየቶች አለመደናገጥ፣
- ከሌሎች ጋር በተገቢ መንገድ መግባባት (ጥሩ የተግባቦት ክሂል ማዳበር)፣
- ሌሎች እንደ ትህትና፣ ታማኝነትና መቻቻል የመሳሰሉ ማህበራዊ እሴቶችን ማዳበርና መጠቀም፣

✍ እነዚህ እስካሁን የጠቀስናቸውና መሰል የህይወት መርሆች ወይም ክህሎቶች አዎንታዊ ናቸው፡፡ ለራስም ለሌሎችም የሚጠቅሙ መልካም የህይወት መርሆች ናቸው፡፡

✍ በአንፃሩ ግን አሉታዊ የህይወት መርሆችም አሉ፡፡ እነዚህ እንደ መስረቅ፣ መዋሸት፣ እምነት ማጉደልና የመሳሰሉ ጉዳዮችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ በማህበረሰብ ዘንድ ከሞራል አንፃር ተቀባይነት የሌላቸው፣ ለራስም ለሌሎችም የማይጠቅሙ የአኗኗር ዘይቤዎች ናቸው፡፡

✍ ስለዚህ በዚህ የትምህርት ክፍል አዎንታዊ ወይም መልካም የሆኑ የህይወት መርሆችን መሰረት በማድረግ፣ ለምሳሌ ወደ ፊት መሆን የምትፈልገውን/ጊውን ርዕሰ ጉዳይ በማድረግ የተቀናጀ ጥሩ አንቀፅ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

ሃሪቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ ሴሳ ሁልጊዜ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ግፊት ታደርግባታለች፡፡ ሃሪቱ የጓደኛዋን የሴሳን ግፊት ለመቋቋም ጥረት ታደርጋለች፡፡ አንዳንድ ነገሮቿን ባትፈልገውም ግን ሴሳን ላለማስቀየም ሃሳቧን በግልፅ አውጥታ ለመናገር አወላውላለች፡፡ ነገር ግን ሁኔታዎች እየገፉ ሲመጡ የሚከተለውን ማስታወሻ ፅፋ ለሴሳ ሰጠቻት፡፡

**የሃሪቱ ማስታወሻ**

ሴሳ ሰላም ላንቺ ይሁን፡፡ ብዙ ጊዜ የውስጤን አውጥቼ በድፍረት ለመናገር እፈልግና ወዲያው ልቤ ተዪ ይለኛል፡፡ ዛሬ ግን ውስጤ የሚለኝን ደፍሬ በዚህ ማስታወሻ ለመግለፅ ወድጃለሁ፡፡ እኔ ለራሴ ከፍተኛ ግምት እሰጣለሁ፡፡ በመሆኑም ትምህርቴን ስጨርስ ምን መሆን እንደምፈልግ አቅጄ እየተማርሁ እገኛለሁ፡፡ በአቻ ግፊትም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች በቀላሉ መታለል አልፈልግም፡፡ የምጥረው ለራሴ ብቻ ሳይሆን ወልደው ላሳደጉኝ ወላጆቼ ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ዓላማዬን ከግብ ሳላደርስ ማለትም እንደ ጎረቤታችን ልጅ ዓለሚቱ በህክምና ሳይንስ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪዬን ሳላገኝ አስቸጋሪ ውጣ ውረዶች ቢኖሩ እንኳ ከዓላማዬ ፈቀቅ አልልም፡፡ አንቺም ሃሳቤን እንደምትደግፊ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ከዚህ በፊት በተነጋገርነው መሰረት ከነ ጠጅቱ ጋር ያለሽን ግንኙነት እንደምታቆሚ ፅኑ እምነት አለኝ፡፡

ያንቺው ሃሪቱ ዱሬሳ

1. ከላይ ከቀረበው የሃሪቱ ማስታወሻ ውስጥ አዎንታዊና አሉታዊ የህይወት መርሆችን ለይ/ዪ።

| አዎንታዊ የህይወት መርሆች | አሉታዊ የህይወት መርሆች |
|---|---|
| ለራስ ከፍተኛ ግምት መስጠት | ማወላወል |
| | |
| | |

2. ቀጥሎ ከቀረቡ አዎንታዊ የህይወት መርሆች መካከል አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀፅ ፅፈህ/ሽ ለክፍሉ አንብብ/ቢ።
   - ሃላፊነት የሚሰማኝ ተማሪ ነኝ
   - መሆን የምፈልገው
   - በራሴ እተማመናለሁ
   - የጥናት ጊዜዬን አከብራለሁ
   - በፈተና ወቅት አልኮርጅም
   - በዕቅድ የምመራ ነኝ

3. ቀጥሎ ከቀረቡ ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ አመዛዛኝ ድርሰት ፃፍ/ፊ። ድርሰቱን ስትፅፍ/ፊ በምዕራፍ ሶስት ስለ አንቀፅ የተማርከውን/ሽውን ማስታወስ ያስፈልጋል።
   - ወንዶች ሴቶችን ስራ ማገዝ አለባቸው።
   - መማር ከሁሉ ይቀድማል።
   - መምህርነት ከሌሎች ሙያዎች ይበልጣል።

ማስታወሻ፤ አመዛዛኝ ድርሰት

✍ የተለመዱት የድርሰት አይነቶች ተራኪ፣ አመዛዛኝ፣ ገላጭና ስእላዊ በመባል ይታወቃሉ። በዚህ የክፍል ደረጃ አመዛዛኝና ተራኪ ድርሰትን እንማራለን።

- አመዛዛኝ ድርሰት የሚባለው ሁለት ሃሳቦችን እያስተያየ የሚያቀርብ ስልት ነው፡፡ ሀሳቦችን ተቃራኒ የሆኑ ወይም ተቃራኒ ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመመዛዘን የሚቀርቡት ተቃራኒ ሃሳቦች ከሆኑ አነፃፃሪ ድርሰት ይባላል፡፡ በመመዛዘን የሚቀርቡት ሃሳቦች ግን ተቃራኒ ሳይሆኑ ተደጋጋፊ ከሆኑ፣ አወዳዳሪ ድርሰት ይባላል:: ስለዚህ አነፃፃሪና አወዳዳሪ ሁለቱም አመዛዛኝ ድርሰቶች ናቸው፡፡

- አመዛዛኝ ድርሰት አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችንም ያቀርባል፡፡ አከራካሪ ፅሁፍ ዓላማው አንደኛው ወገን የሚቀበለውንና የሚያምንበትን ሃሳብ ሌሎች እንዲቀበሉትና እንዲደግፉት ማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማድረግም አሳማኝ ማስረጃዎችን እያቀረበ መገፋፋት ይገባል፡፡

## ገበሬና ነጋዴ

ገበሬና ነጋዴ የሃገራችን ሞተሮች ቢሆኑም የገበሬን ያህል ለሃገር ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ የሚያደርግ አካል የለም፡፡ በእርግጥ ነጋዴው በሚከፍለው ግብር የሃገር ልማት ስራ ይሰራል፡፡ የመንግስት ሰራተኛው ደመወዝ ከሞላ ጎደል በዚሁ ይሸፈናል፡፡

ይሁን እንጂ፣ የምንበላውን፣ የምንጠጣውን፣ የምንለብሰውን፣ ወዘተ. ስንመለከት የሃገራችን ገበሬ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ገበሬ ለህይወታችን መሰረት ነው፡፡ እንደ ገበሬው አምርቶ፣ የሃገሬውን ህዝብ መግቦ ለሃገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ከቶ የለም፡፡ ለምሳሌ፣ የገበሬን የዕለት ተዕለት ውሎ ብንመለከት እንኳን፣ በእርሻ ወቅት ማለዳ ወፍ ሲንጫጫ ተነስቶ በሬዎቹን አውጥቶ ያበላል፡፡ ወዲያው፣ አፉን ሳያሟሽ (ቁርሱን ሳይበላ) በሬዎቹን ጠምዶ ሲያርስ ይውላል፡፡ በአጨዳም ሆነ በውቂያ ለአፍታ ያህል መቀመጫው መሬት ሳይነካ እንደ ዋተተ ያድራል፡፡ ሁላችንም

እንዲህ እንደ ገበሬው ብንሰራ ሃገራችን ዛሬ የት በደረሰች ያሰኛል፡፡

## ክፍል አምስት፤ ሰዋስው

### የዓረፍተ ነገር መዋቅር

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሃረግንና ግሳዊ ሃረግን ትለያለህ/ትለዩአለሽ፡፡
- ውስብስብና ነጠላ ዓረፍተ ነገርን ትለያለህ/ ትለዩአለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ ስማዊና ግሳዊ ሃረጋት**

ዓረፍተ ነገር የስማዊና የግሳዊ ሃረጋት ቅንጅት ውጤት ነው፡፡ ዓረፍተ ነገሩን እንደሚመሰርቱት ሃረጎች ተራነትና ውስብስብነት ዓረፍተ ነገሩ ተራ ወይም ውስብስብ ሊሆን ይችላል፡፡

በስማዊ ሃረጉ ወይም በግሳዊ ሃረጉ ውስጥ ሌላ ዓረፍተ ነገር ከሌለ፣ ተራ ዓረፍተ ነገር ይባላል፡፡ በሌላ አባባል፣ ተራ ዓረፍተ ነገር ከተራ ስማዊና ከተራ ግሳዊ ሃረጎች ይመሰረታል፡፡

- ለምሳሌ፣ ‹‹ገልሜሳ ትልቅ ቤት ሰራ›› የሚል ዓረፍተ ነገር እንውሰድ፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሃረጉ ‹‹ገልሜሳ›› ሲሆን፣ ግሳዊ ሃረጉ ደግሞ፣ ‹‹ትልቅ ቤት ሰራ›› ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዓረፍተ ነገሩን በሚመሰርቱት ሁለቱ ሃረጋት ውስጥ ሌላ ዓረፍተ ነገር ካለ ዓረፍተ ነገሩ ውስብስብ ይሆናል፡፡ በመሰረቱ ‹‹ሌላ ዓረፍተ ነገር›› የተባለው በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኝ ከማሰሪያ ግሱ ውጪ የሆነ ሌላ ግስ ነው፡፡ ይህን ዓይነት ሃሳብ በውስጡ የያዘው ዋናው ዓረፍተ ነገርም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ይባላል፡፡

ለምሳሌ፣ ‹‹ትናንት ከአዲስ አበባ የመጣችው ልጅ እህቴ ናት›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ፣ ስማዊ ሃረጉ ‹‹ትናንት ከአዲስ አበባ የመጣችው ልጅ›› ሲሆን፣ ግሳዊ ሃረጉ ደግሞ ‹‹እህቴ ናት›› የሚለው ነው። ሆኖም በስማዊ ሃረጉ ውስጥ ‹‹የመጣችው›› የሚል ሌላ የማያስር ወይም ያልተቋጨ ግስ እናገኛለን።

1. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ስማዊና ግሳዊ ሃረጎች ለይተህ/ሽ አሳይ/ዪ።
   ሀ. ወይኒቱ የጓሮ አትክልት ተከለች።
   ለ. አንድ በጣም ትልቅ እንግዳ ዛሬ ወደ ቤታችን መጣ።
   ሐ. ትምህርቱን ያጠና ተማሪ ይሸለማል።
   መ. የሃገራችን ጀግኖች ድንበራችንን ያስከብራሉ።

2. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ምክንያት እየሰጠህ/ሽ ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች በማለት ለይ/ዪ። ለአሰራሩ ከላይ በማስታወሻው ስር የሰጠነውን ማብራሪያ መከተል ይቻላል።
   ሀ. የብሄራዊ ቡድን አባላት ዛሬ የእግር ኳስ ይጫወታሉ።
   ለ. በትምህርት ሰዓት ስለረበሸ ተባረረ።
   ሐ. ዘውዲቱ ውድድሩን በአሸናፊነት አጠናቀቀች።
   መ. የአጥፊ ተማሪዎች ቁጥር ከቀነሰ ጥሩ የመማር ማስተማር አውድ ይፈጠራል።

# ክፍል ስድስት፤ ስነ ፅሁፍ

## አጭር ልቦለድ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- አጭር ልቦለድ አንብበህ/ሽ አላባውያንን ታወጣለህ/ታወጪያለሽ።
- በታሪኩ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርያትን ስብዕና ታስረዳለህ/ታስረጂያለሽ።

**ማስታወሻ፤ አጭር ልቦለድ**

- ልቦለድ ረጅምና አጭር ልቦለድ በሚል በሁለት ይከፈላል። በዚህ ደረጃ የምንማረው ግን ስለአጭር ልቦለድ ነው።
- አጭር ልቦለድ የገሃዱን ዓለም ማህበረሰባዊና እውነታንና ተፈጥሮዋዊ ሁኔታዎችን መሰረት አድርጎ ከደራሲ ምናባዊ ሃይል የሚመነጭ የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ነው።
- የሰውን ልጅ ሃዘንና ደስታ፣ ጥላቻና ፍቅር፣ ምኞትና ፍላጎት፣ ብልፅግናና ውድቀት፣ ወዘተ. በሚያማልል ቋንቋ ያቀርባል።
- በባህርዩ ቁጥብ ነው። በቃላት መጠን፣ በሚሸፍነው መቼት፣ በገፀ ባህርያት ቁጥር፣ በገለፃ ሁሉ የተቆጠበ ነው። ለምሳሌ፣ የአንድን ገፀ ባህርይ ህይወት እንደ ረዥም ልቦለድ ከልደት እስከ ሞት ማሳየት አይችልም። እንደ ስሙ አጭር ስለሆነ ብዙ ለማለት በቂ የድርሰት ጊዜና የታሪክ ቦታ አይኖረውም።
- የገፀ ባህርዩ ታሪክ ከሰዓታት፣ ከቀናት፣ ከሳምንታት ጊዜ አይዘልም።

## የአጭር ልቦለድ አላባውያን

### ታሪክ

- መጀመሪያ እንዲህ ሆነ፤ ከዚያም በኋላ ደግሞ እንደዚህ ሆነ፣ በመጨረሻም እንዲህ ሆነ የምንለው በተወሰነ ጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጀ ድርጊቶችና ሁነቶች ትረካ ነው።

### ገፀ ባህርያት

- በአንድ ልቦለድ ውስጥ ታሪኩ የሚተረክላቸው በልቦለዱ ዓለም ስጋ ለብሰው፣ ባህርይ ተሰጥቷቸው የሚንቀሳቀሱ የገሃዱን ዓለም የሚወክሉ፣ ግን የደራሲው ምናባዊ ዓለም ሰዎች ናቸው።
- ደራሲው ስለ ህይወት ያለውን እይታ ወይም አመለካከት የሚገልፅባቸው መሳሪያዎች ናቸው። ህይወት ምን እንደሆነ በነርሱ አማካይነት ይናገራል። ህይወት እንዴት እንደሚኖር ወይም የአኗኗር ዘይቤን በነርሱ አማካይነት ያሳያል።

### መቼት

- ታሪኩ የሚፈፀምበትን ቦታን፣ ጊዜንና ሁኔታን ይመለከታል።

### ግጭት

- በልቦለድ ዓለም የሚኖሩ ገፀ ባህርያትም በታሪኩ ውስጥ በተፈጠረላቸው እርስ በርስ ግንኙነት የተነሳ በተለያዩ ምክንያቶች በቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ውስጥ ይገባሉ። በነዚህ ቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ሳቢያ የሚፈጠረው ፍጭት ወይም ፍልሚያ ግጭት ይባላል።

### ጭብጥ

- ጭብጥ በልቦለዱ አማካኝነት ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክቱ ነው። የልቦለዱ ማዕከላዊ ጉዳይም ነው። ደራሲው ድርሰቱን

የፃፈበት ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ ደራሲው የሚፅፈው አንድ ዓይነት ማህበራዊ ቁም ነገር ለአንባቢ ለማስተላለፍ ነው፡፡ ስለዚህ ጭብጥ የልቦለድ ድርሰቱን አንብበን ጨምቀን የምናወጣው ቁም ነገር (ፍሬ ነገር) ነው፡፡

(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን፣ ለስራችን እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)

3. ቀጥሎ ተረት ተረት የሚለውን አጭር ልቦለድ እያነበብህ/ሽ ገፀ ባህርያቱን፣ መቼቱንና ግጭቱን ለይ/ዪ፡:

## ተረት ተረት

‹‹እመቤት! ... እየመሸ ነው፤ ቶሎ በዪ›› አሉ በር በሩን እያዩ፡፡ የሚሚ እናት እመቤት፣ ቀኑን ሙሉ የለፉበትን ገንዘብ ልታመጣላቸው ወደ መኝታ ቤቷ ገብታ ዘገየች፡፡

ሽማግሌው እሳሎን ቁጭ ብለው ነበር፡፡ የቆረፈደው ሰፊ የሰሌን ባርኔጣቸው ከጎበጠው ከሲታ ሰውነታቸው ጋር ተባብሮ አናጢ ያጣመመው ባለ ቆብ ምስማር አስመስሏቸዋል፡፡

በእርግጥ ደክሟቸዋል፡፡ ቀኑን በሞላ ነፋስ ያፈረሰውን የግቢውን አጥር ሲያጥሩ ነው የዋሉት፡፡ አሁን ከድካማቸው ለማረፍ ፈልገዋል፡፡ የደረቀ ጉሮሮዋቸውን የሚያረጥብ ጠጅ ብጤ ናፍቀዋል፡፡

‹‹እንዳይመሽብኝ ቶሎ በዪ!›› አሉ፣ ደገሙና፡፡

‹‹መጣሁ አባቴ ... ዝርዝር ብር እየፈለግሁልዎት ነኝ›› እመቤት እመኝታ ቤትዋ ሆና ድምፅዋን ወደ ሳሎን ላከችላቸው፡፡ ‹‹እስከዚያ ከሚሚ ጋር ይጫወቱ!››

በዚህ ጊዜ ነበር ሚሚ ከመኝታ ቤቱ ክፍል የወጣችው፡፡ ሰባት ዓመት በቅጡ ባትደፍንም አንደኛ ክፍል ደርሳለች አሉ፡፡ ነገ ፈተና

ቢኖርባትም በጨዋታ ተጠምዳ ነበር፡፡ ከቀን ሰራተኛው ሽማግሌ ጋር እንድትጫወት ስትጋበዝ የነተበ ደብተሯን ከድና ወደ ሳሎን መጣች፡፡

‹‹አባባ ሽማግሌው!›› አለች፣ እንደደረሰች፡፡

‹‹ደህና ነዎት?››

‹‹ዝሃር መስገን! … ደህና ነሽ የኔ ልጅ?››

ሽማግሌው ከልብ ባልሆነ ድምፅ መለሱላት፡፡ እጇን ዘርግታ ደረቅ መዳፋቸውን ጨበጠች፡፡

‹‹አባባ ሽማግሌው!››

‹‹አቤት የኔ ልጅ!››

‹‹አጥሩን በደንብ አጠሩልን?››

‹‹እንዴታ የኔ ልጅ! እኔ ያንቺ አባት የዋዛ ነኝ?! … አሳምሬ አጥሬዋለሁ!›› ዓይኖቻቸው ወደ መኝታ ቤቱ ያማትራሉ፡፡

‹‹አባባ ሽማግሌው! …››

‹‹አ… ቤ … ት›› ድምፃቸው ውስጥ ድካም አለ፡፡

‹‹እስቲ ተለት ተለት ያውሉኝ››

‹‹ተረት? … ተረት አውቃለሁ ብለሽ ነው፣ ሚሚዋ?››

‹‹እንዴ! እርስዎ ሽማግሌ ስለሆኑ ያውቃሉ፤ በናትዎ ይንገሩኝ››

የአሮጌ ካፖርታቸውን ጫፍ ይዛ ጎተጎተቻቸው፡፡ ሽማግሌው ተናደዱ፡፡ አሁን የሚፈልጉት የሰሩበትን ገንዘብ ተቀብለው ወደሚዝናኑበት ጠጅ ቤት ማዝገም ነው፡፡ ተረት የሚያወሩበት ጊዜ የላቸውም፡፡

ሚሚ ግን የምትለቃቸው አልሆነም፡፡ ከአገጫቸው ስር ሆና ቀና ብላ በዓይኖቿ ጭምር ተማፀነቻቸው፡፡ እናም ለመገላገል ፈለጉ፡፡

‹‹እሺ እንግዲህ ተረት ተረት››

‹‹የላም በለት›› ሚሚ ፍንድቅድቅ ብላ ከቦት ጫማቸው ስር ተቀመጠች፡፡

‹‹በድሮ ጊዜ በአንድ ከተማ አንዲት ማተቤ የምትባል በጣም ቆንጆና ትንሽ ልጅ ትኖር ነበር ...››
‹‹እሺ!›› አለች ሚሚ፡፡

‹‹ ... ማተቤ አንቺን የምታህል በጣም አስቸጋሪ ልጅ ነበረች፡፡ በዚህ ምክንያት እናቷ ሁል ጊዜ ትገርፋት ነበር፡፡ ማተቤ ግን ሰፈሯን ጥላ መዞር መጫወትና መቦረቅ ትልቅ ደስታ ይሰጣት ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን ከእናቷ ተለይታ ወደ አንድ ጫካ ትሄዳለች፡፡ ማተቤ ብዙ ጊዜ ወላጆቿ የሚመክሯትን ምክር አትቀበልም ነበር፡፡ ማተቤ በዚያ ጫካ ብቻዋን ስትሄድ ... ስትሄድ ... መንገዱ ተደናገራትና ጠፋች፡፡ በመደናገጧ ማልቀስና መጮህ ጀመረች፡፡

ጩኸቷን የሰሙ ብዙ ጅቦች ከየጎሬያቸው ወጥተው በመምጣት ማተቤን ከበቧት፡፡ ጅቦቹ ጥቋቁር ከመሆናቸው በላይ ዓይኖቻቸው እንደ እሳት ስለሚያበሩ እጅግ በጣም አስፈሪ ነበሩ፡፡ ጥርሳቸውም እንደ ጦር የሾለና የሚያብለጨልጭ ነበር፡፡ ጅቦቹ ህፃኗን ማተቤን ቦጫጭቀው ለመብላት ስለ ፈለጉ ይጮኹ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ብቻዋን ወደ ጫካ በመምጣቷ ተፀፅታ፣‹‹አስቸጋሪ ልጅ መሆን አልነበረብኝም!›› እያለች ስቅ ስቅ ብላ አለቀሰች ይባላል፡፡

ሽማግሌው እመቤት በመዘግየቷ ትዕግስታቸው አልቋል፡፡ ወዲያው፣ ‹‹ይህቺ ሴትዮ እኔን ጎልታ ተኛች እንዴ!?›› አሉ፣ በልባቸው፡፡

‹‹... ሚሚዬ እናትሽ አስመሸችብኝ›› ከማለታቸው እመቤት ከመኝታ ቤት ብቅ አለች። የሚያስፈልጋቸውንም ገንዘብ ሰጠቻቸው። የቁም መቆፈሪያቸውንም ይዘው ወጡ።

(በዕውቀቱ ስዩም፡፡ ተረቶቻችን፡፡ 2010፤ አዲስ አበባ፤ ዜድ ኤ ማተሚያ ቤት፣ ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ተቀንጭቦ የተወሰደ)

4. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በፅሁፍ ምላሽ ስጥ/ጪ።

ሀ. ሽማግሌው እንዴት ያሉ ሰው ናቸው?

ለ. በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህርያት ዘርዝር/ሪ።

ሐ. ማተቤ ምን ዓይነት ባህርይ አላት?

መ. የልቦለዱ ዋነኛ ጭብጥ ምንድነው?

5. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።

ሀ. የልቦለዱን ታሪክ በቃልህ/ሽ ለክፍሉ ተርክ/ኪ።

ለ. ‹‹ተረት ተረት›› የሚለውን አጭር ልቦለድ የገፀ ባህርያትን ድምፀት በመጠበቅ ለክፍሉ አንብብ/ቢ።

# ምዕራፍ ሰባት

## ግብር (ታክስ)

### ክፍል አንድ፤ አድምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- እያዳመጥህ/ሽ ማስታወሻ ትይዛለህ/ትዪዢያለሽ፡፡
- ለቃላት ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡

**ቅድመ ማዳመጥ ተግባር**

‹‹የንግድ ህጎች›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ሲነበብልህ/ሽ ከማዳመጥህ/ሽ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ከለላ
ለ. ስጋት
ሐ. ድርሻ
መ. የጀርባ አጥንት

**የማዳመጥ ሂደት ተግባር**

‹‹የንግድ ህጎች›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህርህ/ሽ ሲያነቡልህ/ሽ እያዳመጥህ/ሽ፣ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ በመያዝ፣ መጀመሪያ ለጓደኛህ/ሽ፣ ቀጥሎም ለክፍሉ በፅሁፍ አቅርብ/ቢ፡፡

ሀ. የንግድ ህግን ማክበር ለነጋዴው የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድነው?

ለ. ግብር መክፈል ለመንግስትና ለማህበረሰብ የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድነው?

### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

ያዳመጥከውን/ሽውን ፅሁፍ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ከቀረቡ ንዑሳን ርዕሶች አንዱን በመምረጥ የቡድን ውይይት በማድረግ ለክፍሉ በቃል ተናገር/ሪ፡፡

ሀ. የንግድ ፈቃድ ማውጣት ለሃገር ያለው ፋይዳ

ለ. የንግድ ህግን ማክበር ለሃገርና ለተጠቃሚው ያለው ፋይዳ

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

### ክርክር

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- መመሪያ ተከትለህ/ሽ ኢመደበኛ ክርክር ታደርጋለህ/ ታደርጊያለሽ፡፡

ቀጥሎ በቀረበው አከራካሪ ዓረፍተ ነገር ዙሪያ ጎራ በመለየት ኢመደበኛ ክርክር አድርግ/ጊ፡፡

➡ ገንዘብ ከዕውቀት ይበልጣል፡፡ ዕውቀት ከገንዘብ ይበልጣል፡፡

**ማስታወሻ፤ የኢመደበኛ ክርክር ምንነትና አቀራረብ**

ኢመደበኛ ክርክር በአንድ አከራካሪ ሃሳብ ዙሪያ ተማሪዎች ጎራ ለይተው የየጎራቸውን አቋም ለመግለፅ ተራ በተራ ሃሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት የንግግር አቀራረብ ነው፡፡

አከራካሪውን ዓረፍተ ነገር በተመለከተ በመቃወም ወይም በመደገፍ ከውሳኔ መስመር ግራና ቀኝ ጎራ ይለያሉ፡፡ በየትኛው ወገን መሆን እንዳለባቸው እርግጠኛ ያልሆኑ ባሉበት ይቆያሉ፡፡

✍ በየጎራችሁ (በየቡድናችሁ) በመወያየት የማጠናከሪያ ሃሳብ አቅርቡ፡፡

- ከየጎራው አንዳንድ ተናጋሪዎች እርግጠኞች ያልሆኑትን ወደ ራሳቸው ጎራ ለማቀላቀል ሃሳብ አቅርቡ፡፡ (እርግጠኛ ያልሆኑ ተማሪዎች በክርክሩ ሂደት ከሁለቱ ጎራዎች ወደ አንዱ ወገን መምጣት ይችላሉ፡፡ ይህን ለማድረግ ከተቃዋሚዎችና ከደጋፊዎች አንዳንድ ጥሩ የማሳመን ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ምክንያታዊ ሃሳብና ማስረጃ እያቀረቡ እንዲሳምኗቸው ማድረግ ይገባል፡፡
- ከየጎራው ከቀረበው ሃሳብ የተነሳ እርግጠኞች ያልሆኑት ወዳሳመናቸው ጎራ መቀላቀል ሲችሉ አሁንም ግልፅ ያልሆነላቸው ባሉበት ሊቆዩ ይችላሉ፡፡

- ጎራ ለይተው የቆሙ በሚከተለው ስልት ይከራከራሉ፡፡
  - ከየጎራው የተወከሉ ተናጋሪዎች ፊት ለፊት እየተያዩ ከውሳኔው መስመር በግራና በቀኝ በወንበር ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ሌሎች ከነርሱ በስተጊላ በየጎራቸው በሰልፍ ይቆማሉ፡፡
  - ደጋፊው ሃሳቡን ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ሲያቀርብ/ስታቀርብ ተቃዋሚው/ዋ ደግሞ እንደዚሁ ቀጥሎ የተቃውሞ ሃሳቡ/ቧን ያቀርባል/ታቀርባለች፡፡
  - የተናጋሪው/ዋ ደጋፊ በመሃል ማጠናከሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ቢፈልግ/ብትፈልግ ከፊት ያለውን/ችውን የአቅራቢውን/ዋን ትከሻ ነካ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡ ተራውንና ቦታውን ልቀቅኝ/ቂልኝ እንደ ማለት ነው፡፡ ሲለቅለት/ላት ቦታውንና ተራውን ተረክቦ/ባ የማጠናከሪያ ሃሳቡን/ቧን ማቅረብ ይቀጥላል/ትቀጥላለች፡፡ በሌላውም ወገን እንደዚሁ ነው፡፡
  - ሁለቱም ተናጋሪዎች የመከራከሪያ ሃሳባቸው አልቆ ዝም ካሉ መሪው (መምህሩ) የጭብጨባ ድምፅ ሲያሰማ

ሁለቱም ተከራካሪዎች ይነሳሉ፡፡ ከየጎራው ሌሎች ሁለት ተከራካሪዎች ቀርበው ክርክሩን በሌሎች ማስረጃዎች ላይ ተመስርተው ይቀጥላሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መልክ የሚካሄድ ክርክር የመናገር ችሎታችሁ እንዲሻሻል ከመርዳቱ ውጪ አሸናፊንና ተሸናፊን የመለየት ጉዳይ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም ሌላ እንዲህ ዓይነቱ የክርክር ዘዴ ከክፍሉ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ በክርክሩ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

### ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- አቀላጥፈህ/ሽ ታነባለህ/ታነቢያለሽ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡
- ለፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቺ ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ፡፡

### ቅድመ ማንበብ ተግባር

‹‹ግብር ወይም ታክስ›› የሚለውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች የጥንድ ውይይት በማድረግ ለክፍሉ ተናገር/ሪ፡፡

ሀ. ግብር (ታክስ) ለአንድ ሃገር የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድነው?

ለ. ከግብር (ከታክስ) የሚገኝ ገቢ ምን ምን ጉዳዮችን ለማከናወን የሚውል ይመስልሃል/ሻል?

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

‹‹ግብር ወይም ታክስ›› የሚለውን ምንባብ መምህርህ/ሽ በሚሰጡህ/ሽ መመሪያ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተራ በተራ አንቀፆቹን በመከፋፈል አቀላጥፈህ/ሽ በማንበብ የተረዳከውን/ሽውን ለጓደኛህ/ሽ ግለፅ/ጪ፡፡

### ግብር (ታክስ)

በዓለም ላይ ያሉ መንግስታት የትኛውንም አስተዳደራዊ ተግባር ሆነ ሌሎች የህዝብ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ያላቸው ብቸኛ የገንዘብ አማራጭ ከዜጎች የሚሰበስቡት ታክስ ነው፡፡ ታክስ ቢቀር ይህን ክፍተት ሊሞላ የሚችል፣ እንዲሁም መንግስታት በተገቢው መንገድ ሃላፊነታቸውንና ተልዕኮዋቸውን እንዲወጡ የሚያስችል አማራጭ የገቢ ምንጭ አይኖርም፡፡

በዚህም ምክንያት ታክስ ከሃገር መልማትና አለመልማት፣ ከኋላ ቀርነትና ከዕድገት፣ ከድህነትና ከብልፅግና ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማነትን ለማጎልበት የታክስ ድርሻ የማይተካ ነው፡፡

በዓለም ዙሪያ የተጠናከረ የታክስ ስርዓት፣ ብሎም ከፍተኛ የታክስ ገቢና ለዚህ ስርዓት የሚመች የሰለጠነ ማህበረሰብ ያላቸው ሃገራት ኤኮኖሚያዊ አቅማቸው እጅጉን የጎለበተ ሆኖ ይታያል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ደካማ የታክስ ስርዓት፣ ዝቅተኛ ገቢ የመሰብሰብ አቅም፣ አነስተኛ የሰለጠነ የሰው ሃይል እንዲሁም የታክሱን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ በአግባቡ ያልተረዳና የሚጠበቅበትን ለማበርከት የሚያቅማማ ህዝብ ያላቸው አዳጊ ሃገራት በሁሉም ዘርፍ ወደ ኋላ ቀርተው ሲያዘግሙ ይታያሉ፡፡

በሃገራችን የተደራጀና በአግባቡ የሚተገበር የገቢ ስርዓት

ለጠንካራ፣ ዘላቂነት ላለውና አካታች ለሆነ ኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ቢሆንም የሚታዩት ተግዳሮቶች ዘርፉ በአግባቡ እንዳያድግ አድርገውታል፡፡ ከነዚህ ተግዳሮቶች መካከል የገቢ አሰባሰብ ውስንነት፣ የታክስ ክለሳ አለመኖር፣ በቆዩና አመቺ ባልሆኑ የታክስ ስርዓቶች ላይ መንጠልጠል፣ እንዲሁም የአስተዳደራዊ አቅም ውስንነቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በነዚህ ምክንያቶች ማህበራዊና አስተዳደራዊ መሰረተ ልማቶችን፣ እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ የህዝብ ፍላጎቶችን ወጪ ለማሟላት ከባድ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ ትራንስፖርት፣ መገናኛና የሃይል አቅርቦት ያሉ መሰረተ ልማቶች ከዘመናዊ ስልጣኔ ጋር የማይሄዱና ብቃት የሌላቸው ይሆናሉ፡፡ የፈጠራ ስራዎች፣ የጤናና የትምህርት ተደራሽነት፣ እንዲሁም የዜጎች ማህበራዊ ዋስትና በአጠቃላይ የመንግስት ሃላፊነት የሆነው የህዝብ መሰረታዊ ፍጆታዎች የፍላጎት አቅርቦትና አስተማማኝነት አይረጋገጥም፡፡ ኤኮኖሚውም በራሱ በሃገር ውስጥ አቅም ላይ ከመመስረት ይልቅ በውጪ ርዳታ ላይ የሚንጠለጠል እንዲሆን ያስገድዳል፡፡

ከዚህ አኳያ፣ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና ቀጣይነት ያለውን ሰላምና ልማት ለማረጋገጥ የሚውለው ገንዘብ ዋነኛ ምንጭ የሆነው ግብር (ታክስ) ህግና ስርዓት ተበጅቶለት የሚሰበሰብ ከመሆኑም ባሻገር ለስልጣኔና ለሃገር ፍቅር የሚከፈል ዋጋ ነው፡፡ ለዚህም ዜጎች በፍላጎትና በፈቃደኝነት የሚጠበቅባቸውን ግብር (ታክስ) በታማኝነት ወቅቱን ጠብቀው መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡

*(የደ.ብ.ብ.ህ.ክልል መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን ዓመታዊ መፅሄት፣ 2012፣ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)*

## ድህረ ማንበብ ተግባራት

1. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሃሳብ ቆምታ መኖር ያለበት በየትኛው ቦታ ነው? ረገጥ ተደርጎ መነበብ ያለበት ቃልስ የትኛው ነው?

ምሳሌ፣ የሚቀጥለውን ዓረፍተ ነገር ሃሳብ ተከትለን እንዴት ማንበብ እንደምንችል እንመልከት፡፡

በዚህም ምክንያት ታክስ ከሃገር መልማትና አለመልማት፣ ከኋላ ቀርነትና ከዕድገት፣ ከድህነትና ከብልፅግና ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡

ሀ. ‹‹በዚህም ምክንያት›› ካለ በኋላ ቆምታ ይኖራል (ነጠላ ሰረዝ ቢኖር መልካም ነበር፤ ባይኖርም ግን ቆም ብለን እናነባለን)

ለ. ሁለቱ ነጠላ ሰረዞች ባሉበት ቦታ ቆምታ ይኖራል፡፡

ሐ. ‹‹የጠበቀ›› በሚለው ቃል ውስጥ ‹‹በ›› ረገጥ ተደርጎ ይነበባል፡፡ ይህን ስናደርግ የመጥበቁን ደረጃ ከፍ እናደርጋለን፡፡

ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የሚከተሉትን ስራ/ሪ፡፡

ሀ. በሁሉም ዘርፍ ውጤታማነትን ለማጎልበት የታክስ ድርሻ የማይተካ ነው፡፡

ለ. በዓለም ላይ ያሉ መንግስታት የትኛውንም አስተዳደራዊ ተግባር ሆነ ሌሎች የህዝብ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ያላቸው ብቸኛ የገንዘብ አማራጭ ከዜጎች የሚሰበስቡት ታክስ ነው፡፡

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሁፍ መልስ/ሺ፡፡

   ሀ. ግብር (ታክስ) ከሃገር መልማትና አለመልማት ጋር የሚያያዘው ለምንድነው?

   ለ. ከፍተኛ የታክስ ገቢና ለዚህ የሚመች ስልጡን ማህረሰብ ያላቸው ሃገራት ኤኮኖሚያቸው የሚጎለብተው ለምንድነው?

   ሐ. የግብር ጠቀሜታን ዘርዝር/ሪ፡፡

   መ. በሃገራችን በገቢ አሰባሰብ ስርዓት ድክመት እንደ ምክንያት የተነሱት ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው?

3. ግብር (ታክስ) የሚለውን ፅሁፍ ፀሃፊው/ዋ ለምን ዓላማ እንደ ፃፈው/ችው ለማወቅ ትኩረት በመስጠት ድምፅ ሳታሰማ/ሚ በድጋሚ በማንበብ ግለፅ/ጪ፡፡

4. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት ፍቻቸውን ፃፍ/ፊ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ጎለበተ | መ. መልማት |
| ለ. ፋይዳ | ሠ. መንጠልጠል |
| ሐ. ማቅማማት | ረ. ተግዳሮቶች |

5. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጥ/ጪ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ጧት | መ. ጊደር |
| ለ. ግርድ | ሠ. ወጠጤ |
| ሐ. ጉፋያ | ረ. ህያው |

ማስታወሻ፤ ፈሊጣዊ አነጋገር (ፈሊጥ)

✍ ፈሊጣዊ አነጋገር፣ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝ፣ ለአንድ ማህበረ ተግባቦት (በአንድ ቋንቋ ለሚናገር ማህበረሰብ) የሚያገለግል፣ ከቃላቱ ጥሬ ፍቺ የተለየ ሃሳብ ያለው ሃረግ ወይም አገላለፅ ነው። ለምሳሌ፣ አመድ አፋሽ፣ አመድ መሰለ፣ ጥርስ መንከስ፣ ወዘተ. ብንል፣ የነዚህ ሃረጋት ወይም አገላለጾች ፍቺ የሚታወቀው በዚያ ቋንቋ ለሚጠቀመው ማህበረሰብ ነው። ከዚህ ሌላ፣ ሃረጋቱ የያዙት ሃሳብ ቀጥተኛ ወይም ጥሬውን ፍቺ አይደለም። ‹‹አመድ አፋሽ›› ብንል እንዲያ የተባለው ሰው በርግጥ አመድ የማፈስ ተግባር የሚሰራ ላይሆን ይችላል። ሃሳቡ ግን፣ ለፍቶ መና ቀረ፣ በከንቱ ደከመ ማለት ነው። ስለዚህ ፈሊጥ ከባህል ጋር የተያያዘ ስለሆነ ዘዋራ ፍቺ አለው።

✍ ምሳሌ፣

- አፈር ለበሰ ሞተ
- በሬ ወለደ ውሸት መናገር
- የህልም ሩጫ ከንቱ ሃሳብ
- የወገብ ቅማል ነዝናዛ

✍ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

- የፅናት ምሳሌ የነበረውና ለሰላሳ ዓመት የቆየው ጎጆው ፈረሰ። (ባልና ሚስት ተፋቱ፤ ትዳር ፈረሰ)
- ዘንድሮ የገበሬው ምርት ስለተትረፈረፈ እህል ጥንቡን ጣለ። (እህል በዛ፣ ዋጋው ረከሰ)

6. ቀጥሎ ለቀረቡ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቻቸውን ፅፈህ/ሽ አገባቡን በዓረፍተ ነገር አመልክት/ቺ፡፡

ሀ. ከማን አንሼ
ለ. ሰርግና ምላሽ
ሐ. የእርጎ ዝንብ
መ. የቀለም ቀንድ
ሠ. ሳር ቅጠሉ
ረ. የአዞ እንባ

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የድርሰት አካላትን ተከትለህ/ሽ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡
- በጅምር የቀሩ ፅሁፎችን አጠናቅቀህ/ሽ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ የድርሰት አካላት**

- ድርሰት እንደየአንቀፁ ተግባር መግቢያ፣ ማተቻና መደምደሚያ የሚባሉ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ ከነዚህ መካከል ማተቻ ወይም ሃተታ የሚባለው ክፍል ዋናው ክፍል ስለሆነ ሁልጊዜም ይኖራል፡፡ ከዚህ የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ማዕከላዊ አንቀፅ እየተባለም ይጠራል፡፡ መግቢያና መደምደሚያ ደግሞ እንደየአንቀፁ መጠንና እንደየፀሃፊው ፍላጎት ላይኖሩም ይችላሉ፡፡

### የድርሰት መግቢያ

- ፀሃፊው በድርሰቱ ውስጥ ማቅረብ የፈለገውን ሃሳብ የማስተዋወቅ ተግባር ያለው አንቀፅ ነው፡፡
- በድርሰቱ ውስጥ ሊነሱ የታሰቡ ዋና ዋና ጉዳዮች እንዲሁም የሚፅፍበትንም ዓላማ አስቀድሞ የሚያውጅበት የድርሰት ክፍል ነው፡፡ የድርሰቱ ይዘትና የፀሃፊው ዓላማ ይቀርቡበታል

ማለት ነው፡፡ በድርሰቱ ማተቻ ወይም ሃተታ ክፍል ለሚዘረዘረው ፍሬ ነገር ፍንጭ የሚሰጥ የድርሰት ክፍል ነው፡፡

- አንድ የመግቢያ አንቀፅ ምሳሌ እንመልከት፡፡ ቆየት ባለ ጊዜ ከጋዜጣ የተወሰደ ነው፡፡
- በዚህ ቁንፅል ፅሁፍ ለመገምገም የተነሳሁት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን፣ በተለይም በመቶ ሃያ ፕሮግራም የሚያቀርባቸውን ድራማዎች ነው፡፡ በኪነ ጥበብ ቅርፅና ይዘት ለድራማ ውበት የሚሰጡ ብቻ ሳይሆኑ አሳምነው የሚያረኩ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ከነዚህ ዋና ዋናዎቹን ጠቅሰን ወደ ድክመቶቹ እናነሳለን፡፡
- ይህ የመግቢያ አንቀፅ ነው፡፡ የፀሃፊው ዓላማ መገምገም ነው፡፡ ሁለተኛም የሚያነሳቸውም ጉዳዮች (የድርሰቱ ይዘቶች) ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው፡፡
  - ሀ. ‹‹አሳምነው የሚያረኩ ብዙ ነገሮች›› ከተባሉት መካከል ዋና ዋናዎች
  - ለ. የድራማዎቹ ድክመቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች እነዚህን ያነሳል ብሎ አንባቢ ይጠብቃል፡፡

**ማተቻ (ማዕከላዊ አካል)**

- በመግቢያ አንቀፁ ይነሳሉ ተብሎ ፍንጭ የተሰጠባቸው ወይም የተጠቆሙ ጉዳዮች ደረጃ በደረጃ የሚብራሩበት፣ በምሳሌና በማስረጃ የሚታተቱበት ክፍል ነው፡፡ ማተቻ የተባለው ለዚህ ነው፡፡ ሃተታ የሚቀርብበት ለማለት ነው፡፡
- የሃተታ አንቀፅ በይዘት ጥልቅ፣ በቁጥር አንድና ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡

- ሆኖም የማተቻ አንቀፅ ስፋትና ጥልቀት እንደሚብራራው ጉዳይ ይወሰናል፡፡ ለመግቢያ አንቀፅ ምሳሌ እንዲሆኑ ካቀርብናቸው የመጀመሪያውን ወስደን አንድ ማዕከላዊ አንቀፅ እናንሳ፡፡
- የመጀመሪያውና ዋነኛው ተአማኒ መሆን ነው፡፡ በማስመሰል እውነታ መጠቀም የሚቻል ቢሆንም የሚፈጠሩት ገፀ ባህርያት ድርጊታቸውና ንግግራቸው ተአማኒ መሆን አለበት፡፡
- ፀሃፊው፣ ‹‹አሳምነው የሚያረኩ›› ካላቸው መካከል አንዱን ማለትም ተአማኒነትን ሲያነሳ እናያለን፡፡ ሌሎችንም ወደ ታች ወረድ ሲል ያነሳል፡፡ ስለዚህ አነሳለሁ ያላቸውን ሁሉ ያነሳቸዋል፡፡

### መደምደሚያ አንቀፅ

- ይህ ክፍል እንደ ስሙ ነው፡፡ የድርሰቱ ሃሳብ የሚሰበሰብበትና የሚጠናቀቅበት ክፍል ነው፡፡
- ፀሃፊው በመግቢያው አንቀፅ የጠቆማቸውን ጉዳዮች በማተቻው (በሃተታው፣ በማዕከላዊው) ክፍል እያብራራ ከቆየ በኋላ በመደምደሚያው የድርሰቱን ሃሳብ ይቋጫል፡፡
- ከአንድ ፅሁፍ መጨረሻ የተወሰደ አንድ አንቀፅ በምሳሌነት እናቅርብ፡፡

  በአጠቃላይ፣ ድርሰትን ለማስተማር የትምህርት ዓላማ እንደሚወሰን፣ ከአላማው አንፃርም የማስተማሪያው ዘዴ እንደሚመረጥ ተመልክተናል፡፡ ድርሰትን የመፃፍ ተግባር ከአዕምሮና ችግርን ከመፍታት ሂደት ጋር የተያያዘ መሆኑንም አውስተናል፡፡ ከዚህም ጋር የማሰብ ክሂልንና ችግርን የመፍታት ሂደትን የሚመለከቱ ክንውኖችን በግል ማሰራት ቢቻልም ቡድናዊ ማድረጉ ተመራጭነት እንዳለው ተመልክተናል፡፡ በሂደቱም ሊከሰቱ የሚችሉ

ችግሮችን የማስቀረት ወይም ገድቦ የመቆጣጠር ሃላፊነት የመምህሩ እንደሆነም ለማውሳት ሞክረናል፡፡

- ይህ መደምደሚያ አንቀፅ ነው፡፡ ከላይ ያለውን ዋናውን ክፍል ባናነበውም፣ ፀሃፊው በድርሰቱ ያነሳቸውን ጉዳዮች በዚህ አንቀፅ ማየት እንችላለን፡፡ ከላይ ቢያንስ አምስት ዋና ዋና ጉዳዮች ቀርበው እንደነበር ከዚህ ማጠቃለያ አንቀፅ መረዳት እንችላለን፡፡ አቀራረቡም ከላይ ያነሳቸውን በመዘርዘር ነው፡፡

ቀጥሎ ሶስት ርዕሶች ተሰጥተዋል፡፡ ከሶስቱ አንዱን መርጠህ/ሽ አንድ የመግቢያ አንቀፅ፣ አንድ ወይም ሁለት ሃተታ አንቀፅ፣ አንድ መደምደሚያ አንቀፅ ፃፍ/ፊ፡፡ ይህን በመፃፍ ሂደት ከዚህ በፊት ስለ አንቀፅ አፃፃፍ የተማርከውን/ሽውን ማስታወስና መተግበር ይገባል፡፡

ሀ. የትምህርት ቤታችን ገፅታ

ለ. የተማሪዎች ስብሰባ

ሐ. የልጅነት ጊዜዬ

መ. ትምህርት ቤቴ

ቀጥሎ አንድ ውጥን ታሪክ ቀርቦአል፡፡ ውጥን ታሪኩን ደጋግመህ/ሽ በማንበብ ቀሪውን ሃሳብ አሟልተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ማስታወሻ፤ ውጥን ታሪክ መጨረስ

- ውጥን (ጅምር) ታሪክ ማለት ጅምር ታሪክ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ውጥን ታሪክን መጨረስ ማለት፣ አንድ በጅምር ላይ ያለን ሃሳብ፣ መሰረታዊ አካሄዱ ሳይዛነፍ ማጠናቀቅ ማለት ነው፡፡

- የተወጠነውን ታሪክ ለመጨረስ ወይም ለመደምደም ዋናውን ሃሳብ ማወቅ ይገባል፡፡ ለዚህም ደጋግሞ በጥሞና ማንበብና የቃላቱን አገባብና የሃሳቡን አወራረድ ማጤን ጠቃሚ ነው፡፡

- ቀጥሎ የሚሞላው ሃሳብ ከመነሻው የተለየ እንዳይሆን

መጠንቀቅ ይገባል፡፡ በሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተቻለ መጠን በአገላለፅ ጭምር የተለየ እንዳይሆን ማሰብ ይገባል፡፡

✍ ጅምር ፅሁፉን ካጠናቀቅን በኋላ ከመነሻው ሃሳብ መለየት አለመለየቱን ደግመን በማንበብ ማየት፣ ከተቻለ ሌሎች ሰዎችም አንብበው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ብናደርግ መልካም ይሆናል፡፡

## ውጥን ታሪክ

በአንድ ወቅት በአንድ ትምህርት ቤት አካባቢ ‹‹በጥረት ለመኖር›› የሚል አነስተኛ ሱቅ ነበር፡፡ ተማሪዎች በእረፍት ጊዜያቸው የተለያዩ ነገሮችን ከዚያ ሱቅ እየሸመቱ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ባለ ሱቁ ግን ራስ ወዳድ ስለነበር፣ ‹‹በጥረት ለመኖር›› የሚለውን ሃሳቡን ትቶ በአጭር ጊዜ ለመክበር ያስብ ጀመር፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን የዕቃዎቹን መሸጫ ዋጋ አለ አግባብ ከፍ አድርጎ መሸጥ ጀመረ፡፡ የአዲሱንም ዋጋ ዝርዝር በሱቁ በር ላይ ለጠፈ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ውሎ ሳያድር አንድ ሌላ ሰው ከዚህኛው ሱቅ ፊት ለፊት ሌላ ሱቅ ከፈተ፡፡ የሱቁንም ስያሜ ‹‹ሁሉም አለ›› አለ፡፡ እርሱም በተራው የዕቃዎችን መሸጫ ዋጋ በሱቁ በር ላይ ለጠፈ፡፡ ከራስ ወዳዱ ሰውዬ ባነሰ ዋጋ መሸጥ ጀመረ፡፡

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

## ክፍል አምስት፤ ሰዋስው

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- ሰዋስዋዊነታቸው የተጠበቀ ዓረፍተ ነገሮች ትፅፋለህ/ ትፅፊያለሽ፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች አሉባቸው፡፡ ስህተቶቹን ለይተህ/ሽ በምሳሌው መሰረት አስተካክለህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ምሳሌ፣ ከበደ ትልቅ በግ ገዝቶ አረዳቸው፡፡

ስህተቱ የቁጥር ነው፡፡ የተገዛው በግ አንድ ነው፡፡ በግሱ የተገለፀው ቁጥር ግን ብዙ ነው፡፡ ‹‹አረዳቸው›› ሲል ስለብዙ በጎች ያወራል፡፡

ይህ ተስተካክሎ ሲፃፍ፣ ‹‹ከበደ ትልቅ በግ ገዝቶ አረደው›› ወይም ‹‹ከበደ ትላልቅ በጎች ገዝቶ አረዳቸው›› ይሆናል፡፡

ሀ. ድንጋዩ እግሬን መታች፡፡
ለ. ባልጉዳ ሆዱን ስላመማት ወደ ሃኪም ቤት ሄደ፡፡
ሐ. ሃርሚቱ ጎበዝ ተማሪ መሆንዋን የክፍልዋ ተማሪዎች ነገረኝ፡፡
መ. ባለፈው ሳምንት እንደተነጋገርነው ትናንት አንድ በሬ ይገዛል፡፡

# ክፍል ስድስት፤ ስነ ፅሁፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የግጥም ምትንና ዜማን ጠብቀህ/ሽ ታነባለህ/ታነቢያለሽ፡፡
- ቤት መምቻና ቤት መድፊያ ሆሄያትን ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- የግጥምን መልዕክት ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡

1. ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም ድምፅ በማሰማት ምቱንና ዜማውን ጠብቀህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

## እኩል አድራጊ ሞት

ሃብታምና ደሃ ሞተው ሲቀበሩ፣
መቃብራቸውን ሰዎች ሲቆፍሩ፡፡
እጅግ አርጎ በጣም ስለ ተቃረበ፣
ሃብታም ተቆጥቶ እንዲህ ተሳደበ፡፡
ምነው አንተ ደሃ እንደዚህ ደፈርከኝ፣
ምንስ አንተን ዛሬ ለማጥቃት ቢያውከኝ፡፡
ራቅ እንደ ማለት እኔን ተመልክተህ፣
አጠገቤ እንደዚህ በጣም ተጠግተህ፡፡
እንዴት ይገባሃል ደፍረህ መተኛት፣
ተነስ ሂድ አሁንም ከምትሄድበት፡፡
ምን አምጥቶ ጣለህ እኔ ግን ከጥንት፣
ወትሮም ልማዴ ነው መሬት መተኛት፡፡
ኀበዝ አይል ፈሪ ደሃ ባለጠጋ፣
ሁሉን አስተካካይ ሞት አለ አደጋ፡፡

*(ከበደ ሚካኤል፣ ታሪክና ምሳሌ አንደኛ መጽሐፍ፣ 2007፣ 58)*

ማስታወሻ፤ ቤት መምቻና ቤት መድፊያ

- በአንድ ስንኝ መጨረሻ የሚገኝ ሆሄ ወይም የመጨረሻ ቃል የመጨረሻ ፊደል ቤት ይባላል፡፡
- ቤት በሁለት ይከፈላል፡፡ ቤት መምቻና ቤት መድፊያ በመባል፡፡
- በአንድ ቤት የቀረቡ ሁለት ስንኞች ቢሆኑ፣ የመጀመሪያው ስንኝ የመጨረሻው ሆሄ ወይም የስንኙ የመጨረሻ ቃል የመጨረሻ ሆሄ ቤት መምቻ ሲባል፣ በሚቀጥለው ስንኝ፣ ከርሱ ትይዩ ያለው (ወደ ታች) ባለው ቃል የመጨረሻ ሆሄ ቤት መድፊያ ይባላል፡፡

ምሳሌ፤

- ሃብታምና ደሃ ሞተው ሲቀበሩ፣ የተሰመረበት ቤት መምቻ
  መቃብራቸውን ሰዎች ሲቆፍሩ፣ የተሰመረበት ቤት መድፊያ
- ይህ ግጥም ባለአንድ ቤት ይባላል፡፡ በ‹‹ሩ›› ቤት የተገጠመ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ግጥም ያልነው እነዚህ ሁለት ስንኞች ነው፡፡

ለምሳሌ፣

- ምን አምጥቶ ጣለህ እኔ ግን ከጥንት፤
  ወትሮም ልማዴ ነው መሬት መተኛት፡፡
  ጎበዝ አይል ፈሪ ደሃ ባለጠጋ፤
  ሁሉን አስተካካይ ሞት አለ አደጋ፡፡
- ይህኛው ግጥም ደግሞ ባለ ሁለት ቤት ግጥም ነው፡፡ በ‹‹ት›› እና በ‹‹ጋ›› ቤት የተገጠመ ነው፡፡

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ግጥም መሰረት መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ግጥሙ ስንት ቤት አለው?

ለ. የግጥሙ አራተኛው ስንኝ ቤት መምቻው ሆሄ የቱ ነው?

ሐ. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

መ. ግጥሙ ስንት ሃረጎች አሉት?

ሠ. የግጥሙ የመጨረሻ ስንኝ ቤት መድፊያ ሆሄ ምንድነው?

ረ. ‹‹እኩል አድራጊ ሞት›› በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም መልዕክት ምንድነው?

# ምዕራፍ ስምንት

## የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂ

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- እያዳመጥህ/ሽ ቁልፍ ቃላትንና ሃረጋትን ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- ያዳመጥከውን/ሽውን በራስህ/ሽ አባባል ትገልፃለህ/ትገልጫያለሽ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

‹‹በግብርናው ዘርፍ የአይ ሲ ቲ ሚና›› የሚለውን ፅሁፍ ከማዳመጥህ/ሽ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. በግብርናው ዘርፍ የአይ ሲ ቲ ቴክኖሎጂ ጠቀሜታ ምን ይመስልሃል/ሻል?

ለ. የአይ ሲ ቲ ቴክኖሎጂ ምን ምን ጉዳዮችን ሊያካትት ይችላል?

#### ሂደተ ማዳመጥ ተግባር

‹‹በግብርናው ዘርፍ የአይ ሲ ቲ አጠቃቀም›› በሚል ርዕስ መምህርህ/ሽ ሲያነቡልህ/ሽ በንቃት እያዳመጥህ/ሽ ቁልፍ ቃላትንና ሃረጋትን በመለየት በደብተርህ/ሽ ላይ ፃፍ/ፊ፡፡

#### ድህረ ማዳመጥ ተግባር

1. ባዳመጥከው/ሽው ፅሁፍ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. በግብርናው ዘርፍ ያለውን የአይ ሲ ቲን አጠቃቀም በማህረሰቡ ውስጥ ለማስፋፋት ምን መደረግ አለበት?

ለ. የአይ ሲ ቲ ቴክኖሎጂ ለግብርናው ማህበረሰብ ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?

2. የቀረበውን የማድመጥ ፅሁፍ በራስህ/ሽ አገላለፅ በአጭሩ ተናገር/ሪ፡፡

ማስታወሻ፤ በራስ አገላለፅ ለማቅረብ የሚረዳ መመሪያ

- የሚነበበውን ፅሁፍ ፍሬ ነገሮችን በጥሞና መጨበጥ፣
- በራስ አገላለፅ ማቅረብ የተወሰነውን የፅሁፍ ክፍል እንዳለ ማቅረብ ሳይሆን ሃሳብን በተረዱበት መጠን በራስ ቋንቋ መግለፅ ነው፡፡
- ዋናውን ሃሳብ ሳይለቁ አሳጥሮ ማቅረብ ነው፡፡

3. ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላት ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት ትርጉማቸውን ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ማጣመር ሐ. ማጎልበት

ለ. ማላመድ መ. ሰርፃ

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ጉዳይ በሰው ፊት ቀርበህ/ሽ ምልልስ ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ፡፡

ቀጥሎ የቀረበውን ምልልስ ሚና ወስደህ/ሽ በመለማመድ በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

## የምልልሱ ዳራ

ዓለሚቱና ደራርቱ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ከአምስተኛ ክፍል ጀምረው የሚዋደዱ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ በሁለቱ ቤተሰቦች መካካል ያለው የኑሮ ደረጃ ሲታይ ግን ልዩነቱ የሰፋ ነው፡፡ የዓለሚቱ እናት ወይዘሮ ትዕግስት ልጆቻቸውን ያለ አባት ከማሳደጋቸውም በላይ ኑሮዋቸውን የሚመሩት ጉልት ተቀምጠው እና ቸርችረው በሚያገኙት ገንዘብ ነው፡፡

የዓለሚቱ እናት ወይዘሮ ትዕግስት ብዙ ጊዜ በህመም ይሰቃያሉ፡፡ ለመታከም እያሰቡም እጅ እያጠራቸው የተውበት ጊዜ በርካታ ነው፡፡

ደራርቱ ለቤተሰቧ አንድ ልጅ ከመሆንዋ በላይ ቤተሰቧ ጥሩ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ቤተሰቧ ደራርቱ የጠየቀችውን ሁሉ ያሟሉላታል፡፡ ለኪስም ለምንም ብለው ከሚሰጧት ገንዘብ፣ አልፎ አልፎ ዓለሚቱን ትደግፍበታለች፡፡ እርስዋም ትምህርትዋን በመውደዷና ጎበዝ በመሆንዋ በየሴሚስተሩ ከየትምህርት ሃላፊዎች ለወላጆቿ ምስጋና ሲቀርብ ቆይቷል፡፡

ዓለሚቱ፤ እኔ ትምህርቴን ለመማር ጥረት ባደርግም ቤታችን ውስጥ ባለው ችግር ምክንያት ብዙ ነገሮች አልተሳኩልኝም፡፡

ደራርቱ፤ በእናንተ ቤት ያለው ችግር ምንድነው? እኔ የማላውቀው ነገር አለ? እማማ አመማት? ትናንት ሃሙስ ከትምህርትሽ የቀረሽው ለዚህ ነው?

ዓለሚቱ፤ ሰሞኑን እንኳ ደህና ነች፡፡ ነገር ግን የልጆቹ ሁኔታ እየረበሸኝ ነው፡፡ አባታችን ከሞተ በኋላ በእናታችን ላይ ያለው ጫና ከባድ ነው፡፡ ፍላጎታቸውን ማሟላት አልቻለችም፡፡ በዚያ ላይ ታማሚ ናት፡፡ ቀኑን ሙሉ

ጉልት ተቀምጣ ውላ ማታ ስትመለስ ያለውን ሁኔታ አስቢው…

ደራርቱ፤ አትጨነቂ፤ እኔ ለአባዬና ለእማዬ ያለውን ሁኔታ እነግራቸዋለሁ፡፡ መረዳዳት ባህላችን ነው፡፡ ምን ችግር አለ ብለሽ ነው?

ዓለሚቱ፤ እስከ መቼ ድረስ በዚህ መንገድ የሰውን እጅ በማየት መኖር ይቻላል? እኔ ትምህርቴን አቋርጬ እናቴን መርዳት ይኖርብኛል፡፡ ወንድሞቼ ጎዳና ወጥተው በኋላ …(ሁለቱ እየተነጋገሩ ሳሉ የዓለሚቱ ወንድም ቶሼ ወደ ቤት ይገባል)፡፡

ቶሼ፤ እማማ ሄደች እንዴ?

ዓለሚቱ፤ አዎ፣ ሄዳለች፡፡ እስካሁን ድረስ እቤት ትቀመጣለች ብለህ ነው?

ቶሼ፤ ብር ፈልጌ ነበር፡፡ ትምህርት ቤት ለቡድን ስራ አስር ብር አዋጡ ተብለናል፤ ለዛሬ ነበር የምፈልገው…

ዓለሚቱ፤ ለዛሬ ነው የፈለግኸው? (ደራርቱ ወዲያው ‹‹እኔ እሰጥሃለሁ›› ብላ አስር ብር አውጥታ ሰጠችው)

ዓለሚቱ፤ ያንቺ ውለታ በምን ይመለሳል? ሁልጊዜ የኛ ቤት ጫና በአንቺ ላይ ያርፋል፡፡ እግዚአብሄር ይስጥሽ፡፡ አሁን ይህን ብር ባያገኝ ኖሮ ቶሼ ይሰማው ነበር፡፡ ዮናስ ቢሆን ብዙም አይጨነቅም፡፡ ቶሼ ነግሬሻለሁ፤ በአንደኛ ሴሚስተር ከክፍሉ አንደኛ ነው የወጣው፡፡ በትምህርቱ በጣም ጎበዝ ነው፡፡ ካልቸገረው በቀር እንዲህ አፍ አውጥቶ አይጠይቅም፡፡

(ደራርቱና ዓለሚቱ በዚህ ሁኔታ ከተነጋገሩ በኋላ ይለያያሉ። ከሶስት ቀን በኋላ፣ ሰኞ ዕለት፣ ትምህርት ቤት ይገናኛሉ)።

ደራርቱ፤ ሰላም ዓለሚቱ! እንደምን ሰነበትሽ? እማማ እንዴት ናት?

ዓለሚቱ፤ እንዴት ነሽ? የእማማ ነገር ባክሽ ያዝ ለቀቅ ነው። ትናንት በጣም አሟት ነበር። እኔም ዛሬ ከትምህርት ቤት ልቀር ነበር። ሃሙስና ዓርብን ስላልመጣሁ ዛሬ መቅረት የለብኝም ብዬ ነው የመጣሁት።

ደራርቱ፤ ምነው ምን ሆነች? በጣም አመማት እንዴ? በፊት የሚያማት ነው ያመማት?

ዓለሚቱ፤ አስቸጋሪ ነው ባክሽ። በጣም አሟታል።

ደራርቱ፤ በቃ እሺ! አይዞሽ! ችግር የለውም።

ዓለሚቱ፤ አንቺንም እያስጨነቅሁሽ ነኝ።

ደራርቱ፤ እንደዚህ አትበዪ ባክሽ... ምን ማለትሽ ነው? ለአባዬና ለእማዬ የእማማንና የልጆቹን ሁኔታ ነግሬያቸዋለሁ። አብረን እንመጣለን።

ዓለሚቱ፤ ምን ማለትሽ ነው? ቆዩ፣ ምን ብለሽ ነው የነገርሻቸው?

ደራርቱ፤ እሱን ተዪውና አሁን ወደ ክፍል እንግባ።

ዓለሚቱ፤ እሺ፣ እኔ በዕረፍት ሰዓት ወጥቼ እሄዳለሁ።

(ከሰዓት በኋላ ደራርቱ፣ ወይዘሮ አልማዝና አቶ ጋቼኖ እነ ዓለሚቱ ቤት ይመጣሉ)

ወ/ሮ. አልማዝ፤ ሁሉንም ደራርቱ አጫውታናለች። ለመሆኑ ጤንነትሽ እንዴት ነው? ተሻለሽ ወይ? እኔና ጋቼኖ

በዚህ ጉዳይ ተነጋግረናል፡፡ ዛሬ የግድ መታከም አለብሽ፡፡ የህመምሽ ምንነት መታወቅ አለበት፡፡

አቶ ጋቼኖ፤ ደራርቱ ስትነግረን በጣም አዝነናል፡፡ ያኔ በአደጋው ጊዜ ብቻ መጥተን በዚያው ቀረን፡፡ አሁን የጤንነትሽ ሁኔታ እንዴት ነው?

ወ/ሮ. ትዕግስት፤ እ… እግዚአ… ብሄር ይመስገን፡፡ እኔ … ይኸው አለሁ፡፡ (እያቃሰተች)

አቶ ጋቼኖ፤ አሁን ቶሎ ብለሽ መታከም አለብሽ፡፡ ልጆቹም ቢሆኑ ትምህርታቸውን ማቋረጥ የለባቸውም፡፡ እኔና አልማዝ ተማክረናል፡፡ አስፈላጊውን ሁሉ እናደርግልሻለን፡፡

ወ/ሮ. ትዕግስት፤ እህህ… እህ… እ… ሰው አለኝ ለካ…! እኔ ከጎኔ ማንም የ.. ለኝም ብዬ …ነበር፡፡ ልጆቼን በትኜ … እኔም … እንዳባታቸው ወደማይቀረው … ልሄድ ነበር፡፡ አንድ ነገር ብሆን እንኳ… ልጆቼ … አሁን ተስፋ አላ…ቸው፡፡

አቶ ጋቼኖ፤ አይዞሽ ምንም አትሆኚም፡፡ ደግሞ ልጅ ይዞ ክፉ ማሰብ አያዋጣም፡፡ መልካም መልካሙን እያሰቡ ፈጣሪን ተስፋ ማድረግ ነው እንጂ፡፡

ወ/ሮ. ትዕግስት፤ እሺ፣ ደራርቱን … ለኛ ቤተሰብ የሰጠን… እግዚአብሄርን …አመሰግናለሁ፡፡ (እንባዋ ዱብ ዱብ ይላል)፡፡ ከናንተ ጋር … እንድንገናኝ ድልድይ… ሆነችን፡፡ በዚህ ዘመን … እንደናንተ ያለ ሰው … ይኖራል ብዬ … አልሜም… አስቤም አላውቅም፡፡

ወ/ሮ. አልማዝ፤ ሁሉ አላፊ ነው፡፡ ችግርም ያልፋል፡፡ ደራርቱ ስለ ልጆቹ ብዙ ጊዜ ነግራናለች፡፡ በጣም ጎበዝ ተማሪዎች እንደሆኑ ነግራናለች፡፡ ምንም ሳይሰማቸው ትምህርታቸውን መቀጠል አለባቸው፡፡ ጥሩ ስራ ሰርቶ ለህሊና መኖር ደስ ይላል፡፡ ገንዘብ ቢያከማቹት ምን ደስታ ይሰጣል ብለሽ ነው! በይ ተነሽ መኪና ውጪ አለ፤ እንሂድ፡፡

ወ/ሮ. ትዕግስት፤ እንግዲህ … ምን እላለሁ! እግዚአብሄር… ብድራታችሁን ይክፈላችሁ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- አንድን ምንባብ በተወሰነ ደቂቃ አንብበህ/ሽ የምንባቡን ዋና ሃሳብ በአጭሩ ትገልፃለህ/ትገልጪያለሽ፡፡
- ለቃላትና ሃረጋት አጠቃቀማዊ ፍቺ ትሰጣለህ/ ትሰጪያለሽ፡፡

### ቅድመ ማንበብ ተግባራት

ቀጥሎ በቀረቡ ቃላት የጥንድ ውይይት በማድረግ ግምታዊ ፍቻቸውን ስጥ/ጪ፡፡

ሀ. ቀባጣሪ

ለ. ብልጭ አለ

ሐ. መናበብ

መ. ተነበየ

## ሂደተ ማንበብ ተግባራት

‹‹የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂ›› የሚለውን ምንባብ ለማንበብ የሚሰጥህ/ሽ ጊዜ አምስት ደቂቃ ነው። በዚህ የአምስት ደቂቃ ማንበብ ውስጥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዕምሮህ/ሽ ይዘህ/ሽ ለመዝለቅ ሞክር/ሪ።

ሀ. ፅሁፉ የተዘጋጀበትን ዋነኛ ዓላማ ለይቶ መጥቀስ ይቻላል?
ለ. ፀሃፊው ለማስተላለፍ የፈለገው ዋና ሃሳብ ምንድነው?
ሐ. በአንተ/ቺ አመለካከት የመጪውን ዘመን ቴክኖሎጂ ፀሃፊው ያሰበበት (የደረሰበት) ደረጃ ይኖራል ብለህ/ሽ ትገምታለህ/ትገምቺያለሽ?

### የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂ

አዳዲስ አሰራሮችን ለመረዳት አሁን ያለንበት ዘመን የመጀመሪያውን አውሮፕላን ያበረሩት ወንድማማቾች ከኖሩበት ዘመን የተሻለ ነው። ሁለቱ ወንድማማቾች አንድ ሰው የምትይዝ አውሮፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርተው ሲበሩ ወደ ፊት አውሮፕላን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አሳፍሮ ይጓዛል፣ ከድምፅ በበለጠ ፍጥነት የሚበሩ አውሮፕላኖች ይኖራሉ ብሎ የተነበየን ስራ ፈትና የማይመስል ነገር ቀባጣሪ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። የዚህ ዓይነቱም አባባል ሳይንሳዊ ልቦለድ የሚል ቅፅል ተሰጥቶት ነበር።

በአደጉት አገሮች የ3D ቴክኖሎጂ በፋብሪካዎች ውስጥ ሸቀጣ ሸቀጥ በጥራትና በብዛት ለማምረት እየቀረ ሄዶ በቀጣዮቹ አስራ አምስት ዓመታት በየቤቱ የሚመረት ይሆናል።

አሁን የስልጣኔ ምልክት የምንላቸው ትላልቅ የዕቃ መጓጓዣ መርከቦች፣ ግዙፍ አውሮፕላኖች፣ ሰፋፊ አውራ ጎዳናዎችና የባቡር መስመሮች ሁሉም ምርቶች በየቤቱና በየአካባቢው በ3D ህትመት በሚመረቱበት ሁኔታ ‹‹ምን ጥቅም ይኖራቸዋል?›› ብላችሁ አስቡ።

በእርግጥ የምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ በየትም ዓለም ደረጃቸው ተመሳሳይ ሆኖ በየቤታችንና በየአካባቢያችን በኮምፒዩተሮች መካከል በሚኖር መናበብ ከተመረቱ፣ ከውጪ ተጓጉዘው እንዲመጡ አያስፈልግም።

የወደፊቱ የሰው ልጅ መጓጓዣ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ አሁን በስራ ላይ ያሉት በአካባቢ የሚመረቱ ዕቃዎችን ከቤት ወደ ቤት ለማጓጓዣ ሊጠቅሙ ይችላሉ የተባሉት ኦቶኮፕተሮች ናቸው። ይህን አሰራር ለመተግበር አማዞን የስራ ፈቃድ ጠይቋል፤ ወደ ፊት የሰው ልጅም ሰውን በሚያሳፍሩት ኦቶኮፕተሮች ይጓጓዛል ተብሎ ይገመታል።

መርከቦች፣ ባቡሮች፣ መኪናዎች፣ አውሮፕላኖች ብቻ ሳይሆኑ የባቡር ሃዲዶች አስፋልት ጎዳናዎች ሁሉ አስፈላጊ የማይሆኑበት ዘመን ላይ እንደርሳለን።

*(የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂና ኑሮ፣ 2007፣ ከሚለው መፅሃፍ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)*

### ድህረ ማንበብ ተግባር

1. ምንባቡን በድጋሚ በማንበብ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ/ሺ።

   ሀ. በምንባቡ መሰረት ከድምፅ በበለጠ ፍጥነት የሚበሩ አውሮፕላኖች ይበራሉ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

   ለ. ‹‹የዚህ ዓይነቱም አባባል ሳይንሳዊ ልቦለድ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ፣ ‹‹የዚህ ዓይነቱም›› የሚለው ምንን ያመለክታል?

   ሐ. ‹‹በየቤታችንና በየአካባቢያችን በኮምፒዩተሮች መካከል በሚኖር መናበብ ከተመረቱ፣ ከውጪ ተጓጉዘው እንዲመጡ

አያስፈልግም›› በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተገለፀውን ሃሳብ አስረዳ/ጂ።

መ. ፀሃፊው ለማስተላላፍ የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው?

2. ቀጥሎ የቀረቡ ቃላት በቅድመ ማንበብ ደረጃ ጥንድ ጥንድ በመሆን የተወያየህባቸው/ሽባቸው ናቸው። በምንባቡ መሰረት፣ እንዲሁም የውይይቱን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ለቃላቱ ፍቺ ስጥ/ጪ።

ሀ. ቀባጣሪ ሐ. ብልጭ አለ

ለ. ተነበየ መ. መናበብ

3. ቀጥሎ በቀረቡ ምሳሌዎች መሰረት የጥንድ ውይይት በማድረግ በስሩ ያሉትን ቃላት በተለምዷዊ አባባሎች አሟልተህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

ምሳሌ፣ ማር ------------- ይቆረጣል

አብሲት ------------ ይጣላል ይባላል።

ሀ. ዳቦ ______________ መ. እንጎቻ ______________

ለ. እንጀራ ______________ ሠ. ቆሎ ______________

ሐ. ጠጅ ______________ ረ. አረቄ ______________

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- የመፃፍ ደረጃዎችን ጠብቀህ/ሽ ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ።

ማስታወሻ፤ የመፃፍ ደረጃዎች

- የመፃፍ ክሂላችን በአንድ የመፃፍ ተግባር አይዳብርም። መፃፍ ሂደትን ይጠይቃል። ደግሞም ደጋግሞ መፃፍን ይጠይቃል።

እየፃፍን የተሳሳትነውን እየሰረዝንና እየደለዝን እናርማለን። እነዚህንና የመሳሰሉ ተግባራትን የምናከናውንባቸው ሶስት ደረጃዎች አሉ።

**ቅድመ መፃፍ ደረጃ**

- ዋናውን ሃሳባችንን በወረቀት ላይ ከማስፈራችን በፊት ያለውን ተግባር ይመለከታል። በዚህ ደረጃ ለመፃፍ ዝግጅት እናደርጋለን፤ ርዕስ እንመርጣለን፤ ርዕሱ ሰፊ ከሆነ እናጠበዋለን።

**የመፃፍ ደረጃ**

- በዚህ ደረጃ ፀሃፊው እፅፋለሁ ያለውን ባሰበውና ባዘጋጀው ልክ ያከናውናል። ይህን ሲያደርግ ስራው ማንኛውም ዓይነት ስህተት ሊኖርበት ይችላል። የሰዋስው፣ የቃላት ምርጫ፣ የቅደም ተከተል ወዘተ. ስህተት ሊኖርበት ይችላል።

**ድህረ መፃፍ ደረጃ**

- በዚህ ደረጃ ሁለት ዋና ዋና ስራዎች ይከናወናሉ። አንደኛው የክለሳ ስራ ነው። ክለሳ፣ ፀሃፊው አነሳለሁ ያላቸው ጉዳዮች ተነስተው እንደሆነ ተመልሶ የሚያይበት ደረጃ ነው። ትኩረቱ በሃሳቡ ላይ ይሆናል። ሁለተኛው፣ የእርማት ጉዳይ ነው። የፊደል ግድፈት፣ የሰዋስው፣ የድግግሞሽ፣ ወዘተ. ስህተቶችን የሚያርምበት ወይም የሚያቃናበት ደረጃ ነው።

ቀጥሎ ከቀረቡ ርዕሶች መካከል አንዱን መርጠህ/ሽ የመጻፍ ደረጃዎችን ጠብቀህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

- የልጅነት ጊዜዬ
- የምወደው የበዓል አከባበር
- የትምህርት ቤት ጓደኛዬ
- ትምህርት ቤቴ

## ክፍል አምስት፡ ሰዋስው

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- ከቃላት ላይ ምዕላዶችን ትለያለህ/ትለዪአለሽ።
- ምዕላዶችን አጣምረህ/ሽ ቃልን ትመሰርታለህ/ትመሰርቺያለሽ።
- የጥገኛ ምዕላዶችን አገባብ ለይተህ/ሽ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ።

1. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙ ምዕላዶችን በምሳሌው መሰረት አውጣ/ጪ።

ምሳሌ፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብልጢት | ብልጥ - ኢት | ጫማዋ | ጫማ - ዋ |
| ቃላት | ቃል - ኣት | ስላመማት | ስለ - አመም - ኣት |

ሀ. ልጆች　　　　ሐ. መንደሮቻችሁ

ለ. በሬዎች　　　　መ. ምሳሌዎቻችንን

ማስታወሻ፤ ምዕላድ

- ምዕላድ፣ ፍቺ ያለው አነስተኛ የቋንቋ ቅርፅ ነው፡፡ ፍቺው በራሱ ሲቆም ወይም ከሌሎች ምዕላዶች ጋር ሲቀናጅ ሊሆን ይችላል፡፡

- ከቅርፁ አንፃር፣ ምዕላድ በሁለት ይከፈላል፡፡ ከዚህ አንፃር ነፃና ጥገኛ ምዕላድ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ነፃ ምዕላድ የሚባለው፣ በራሱ ላይ ሌላ ምዕላድ ያልጨመረ፣ ከመነሻውም ብቻውን የቆመ ቃል ሲሆን፣ ጥገኛ ምዕላድ የሚባለው ግን በሌላ ምዕላድ፣ ማለትም በነፃ ምዕላድ ላይ የተቀጠለ ምዕላድ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አፈር፣ ድንጋይ፣ ዛፍ ብንል እነዚህ በራሳቸው ላይ ምንም ያልጨመሩ ስለሆኑ ነፃ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ነገር ግን /አፈርማ/ ብንል በ/አፈር/ ላይ /-ማ/ ስለተጨመረ የተጨመረው ጥገኛ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም /ድንጋይ -ኦች/፣ /ዛፍ -ኡ/ ብንል ከላይ ነፃ ምዕላድ ባልናቸው ላይ የተቀጠሉት ጥገኞች ናቸው ማለት ነው፡፡
- ጥገኛ ምዕላዶችን ያስጠጋው ቅርፅ ግንድ ይባላል፡፡ አልፎ አልፎ አምድም ይባላል፡፡
- ከአገባብ አንፃርም ጥገኛ ምዕላዶች ቅድመ ግንድ፣ ውስጠ ግንድና ድህረ ግንድ ተብለው ይጠራሉ፡፡ ቅጥያውን ከሚቀበለው ዋና ቃል ቀድሞ የገባ፣ በውስጡ የገባ፣ በኋላ የገባ እንደማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፣

- /እንደፈላለጉ/ በሚለው ቃል ውስጥ /እንደ-/ ቅድመ ግንድ፣ /-ላ-/ ውስጠ ግንድ፣ /-ኡ/ ድህረ ግንድ ይሆናል፡፡ /ፈለግ/ግን ግንድ ነው፡፡ ሌሎቹን ቅጥያዎች ያስጠጋው እርሱ ስለሆነ፡፡

1. ቀጥሎ የቀረቡ ምዕላዶችን አጣምረህ/ሽ ቃላትን ፃፍ/ፊ።
   ሀ. ብልህ-ኣት-ኧኛ-ነት-ኡ
   ሐ. ትንሽ-ኢት-ኡ
   ለ. አስ-ቸገር-ኧች-ኣቸው
   መ. አስ-አረፍ-ኧች-ኡ (ው)

2. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ በመጀመሪያ ግንዱን ለይተህ/ሽ አውጣ/ጪ። ከዚያም ጥገኛ ምዕላዶቹን ቅድመ ግንድ ውስጠ ግንድና ድህረ ግንድ በማለት ለይ/ዪ።
   ሀ. እንደአዛዦቹ
   ሐ. ኮቱ
   ለ. ስለዶሮዎቻችን
   መ. እንደየደብተሮቻችን

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- እያዳመጥሽ/ህ ማስታወሻ ትይዢያለሽ/ትይዛለህ።
- ለአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ትሰጫለሽ/ትሰጣለህ ።

**ቅድመ ማዳመጥ ተግባር**

1. ‹‹ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች›› የሚለው የሚደመጥ ፅሁፍ ከመቅረቡ በፊት ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያ የቡድን ውይይት በማድረግ የደረሳችሁበትን ሃሳብ በተወካይሽ/ህ አማካይነት አቅርብ/ቢ።

   ሀ. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ማለት ምን ማለት ነው?

   ለ. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ምን አይነት ችግር ያለባቸው ናቸው?

**ሂደተ ማዳመጥ ተግባር**

2. መምህር የሚያነቡትን ፅሁፍ እያዳመጥህ/ሽ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከትምህርት እንዲገለሉ የሚያደርጓቸውን ምክንያቶች በመለየት በማስታወሻህ/ሽ ላይ ጻፍ/ፊ።

**ድህረ ማዳመጥ ተግባር**

3. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጥከው/ሽው ምንባብ መሰረት በጽሁፍ መልስ/ሺ።

ሀ. ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ከትምህርታቸው እንዲገለሉ የሚያደርጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ወላጆችና ማህበረሰቡ ስለአካል ጉዳተኝነት ባላቸው የተዛባ አመለካከት የሚታዩ ችግሮች ምን ምን ናቸው?

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- የሰበሰብሽውን/የሰበሰብከውን መረጃ መሰረት አድርገሽ/ህ በሰው ፊት ንግግር ታደርጊያለሽ/ታደርጋለህ፡፡

1. ቀጥሎ የቀረበውን ፅሁፍ መነሻ በማድረግ እንዲሁም የህብረተሰብ ሳይንስ መምህርህን/ሽን በመጠየቅና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ በአየር ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮችን በዝርዝር በመለየት ለክፍሉ በንግግር አቅርብ/ቢ፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ማለት ከተፈጥሮ የሁኔታዎች መለዋወጥ እና ከሰዎች የተለያዩ ተግባራት የተነሳ በሂደት በከባቢ አየር ላይ የሚከሰት ለውጥ ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ችግር በአብዛኛው የሚከሰተው የግሪን ሀውስ ጋዞች ክምችት በከባቢ አየር ውስጥ እንዲጨምር በሚያደርጉ የሰው ልጆች ተግባራት የተነሳ ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሙቀት መጠን እንዲጨምር፣ የባህር ጠለል ከፍ እንዲል፣ የአየር ጠባይ እንዲለዋወጥ፣ እንዲሁም ለመተንበይ አዳጋች የሆኑ ሌሎች ከባድ የአየር ጠባይ መለዋወጥ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የዝናብ ስርጭት ለውጦች፣ የጎርፍ ክስተቶች፣ የድርቅ ሁኔታዎች መስፋፋት፣ ተደጋጋሚ የሰደድ እሳት አደጋዎች መከሰት፣ የውሀ መድረቅ መኖር፣ ወዘተ.

እንዲፈጠሩ ያደርጋል። የእነዚህ ተጽእኖዎች ድምር ውጤት የግብርና ምርቶች መቀነስን፣ የምግብ ዋስትና ማጣትን፣ የውሀ አቅርቦት ችግር መባባስን፣ የስነ ምህዳር መጎዳትን እንዲሁም የጤና ችግር መስፋፋትን ያስከትላል ።

*(በሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ዙሪያ የአየር ንብረት ለውጥ መረጃ 2006 ዓ.ም ገጽ 14 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)*

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የቀደመ እውቀትሽ/ህን ተጠቅመሽ/ህ ግምታዊ ሃሳብ ትሰጪያለሽ/ጣለህ።
- ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ትሰጪያለሽ/ጣለህ።
- ለቃላትና ሃረጋት አጠቃቀማዊ ፍቺ ትፅፊያለሽ/ፋለህ።

### ቅድመ ማንበብ ተግባር

‹‹የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት›› በሚል ርእስ ስር የቀረበውን ምንባብ ከማንበብህ/ሽ በፊት ከዚህ በፊት ያለህን/ሽን የቀደመ እውቀት መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተርህ/ሽ ላይ በመገልበጥ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ረድፎች በመሙላት አሳይ /ዪ።

| የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት | | |
|---|---|---|
| ስለ አካቶ ትምህርት የማውቀው | ስለ አካቶ ትምህርት ከምንባቡ ማወቅ የምፈልገው | ስለ አካቶ ትምህርት ከምንባቡ ያወቅሁት |
| | | |

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

‹‹የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት›› የሚለውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰማ/ሚ በማንበብ በቅድመ ማንበብ ላይ ‹‹ማወቅ የምፈልገው›› በሚለው ዓምድ ስር የዘረዘርካቸውን/ሻቸውን ነጥቦች በምንባቡ ውስጥ መኖር ያለ መኖራቸውን እያስተዋልክ/ሽ በዝግታ አንብብ/ቢ፡፡

### የአካቶ ትምህርት አስፈላጊነት

አካቶ ትምህርት ማለት ሁሉም ተማሪዎች አካል ጉዳተኞቹም ሆኑ ጉዳት አልባ ተማሪዎች፣ በአቅራቢያቸው በሚገኝ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተካተው ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚማሩበት የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተለያዩ ፀሃፊዎች፣ ለአካቶ ትምህርት ከተለያዩ አውዶች ወይም የትኩረት ነጥቦች ማለትም ከትምህርት ተደራሽነት፣ ከትምህርት አደረጃጀት፣ ከድጋፍ አሰጣጥ፣ ወዘተ. አንጻር ትርጉም ስለሚሰጡት እሳቤው ውስብስብ ሊሆን ችሏል ፡፡

እንደ ዩኔስኮ የ2005 (እ.ኤ.አ) አመለካከት ማካተት ማለት የባህልና የማህበረሰብን ተሳትፎን በማሳደግ እንዲሁም ከትምህርት መገለልን በመቀነስ የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማስተናገድ

የሚያስችል ሂደት ከመሆኑም ባሻገር የመደበኛ ትምህርት አካል ነው፡፡

አገራችን፣ የአካል ጉዳተኞች በትምህርት ስርአቱ በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ተካተው የመማር መብት እንዳላቸው ዕውቅና የሚሠጠውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2006 (እ.ኤ.አ) የአካል ጉዳተኞች ጥበቃ ስምምነት በ2002 ዓ.ም ተቀብላ አጽድቃለች፡፡ ይህ መብት በህገ መንግስቱ አንቀጽ ዘጠኝ መሰረት የሃገሪቱ ህገመንግስት አካል ሆኗል፡፡

ምንም እንኳን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአካል ጉዳተኞችና የመማር ችግሮች ያሉባቸው ህጻናትና ወጣቶች በአካቶ ትምህርት ስርአት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ድጋፍ እየተደረገላቸው ቢማሩም፣ ቁጥራቸው አነስተኛ ያልሆነ ከፍተኛ የአካል ጉዳት፣ የአእምሮ እድገት ውስንነት፣ ኦቲስቲክ ልጆች፣ መስማትና ማየት የተሳናቸው፣ ወዘተ. በልዩ ትምህርት ቤቶች ወይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ልዩ ክፍሎች ውስጥ ልዩ ስልጠና እየተሰጣቸው ይገኛል፡፡ ወይም ለብቻቸው እንዲማሩ ተደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ፣ አካቶ ትምህርት ሁሉም ተማሪዎችና ልጆች ሊማሩ ይችላሉ ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ የትምህርት አሰጣጥ የትምህርት አካባቢው የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች ለማስተናገድ ማስማማት እንደሚኖርበት ግድ ይላል፡፡ ይህም ማለት ምቹ የመማሪያ አካባቢ ካለና ድጋፍ ከተደረገላቸው ሁሉም ልጆች ይማራሉ የሚለውን የአካቶ ትምህርት መሰረታዊ ሃሳብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

*(ትምህርት ሚኒስቴር፣2004 ዓ.ም፣<u>የልዩ ፍላጎት (አካቶ) ትምህርት</u> ስትራቴጂ ገጽ 4-5 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)*

## ድህረ ማንበብ ተግባር

1. በቅድመ ማንበብ በደብተርህ/ሽ የገለበጥከውን/ሽውን ሰንጠረዥ በሶስተኛው አምድ ላይ፣‹‹ስለ አካቶ ትምህርት ከምንባቡ ያወቅሁት›› የሚለውን በመሙላት ለክፍሉ አቅርቢ/ብ፡፡
2. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት››፣ ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት እየሰጠህ/ሽ በቃል መልስ/ሺ፡፡

ሀ. በሀገራችን አካል ጉዳተኞች በትምህርት ስርአቱ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ተካተው የመማር መብት እንዳላቸው እውቅና የተሰጠው በ 2000 ዓ.ም ነው ፡፡

ለ. አካቶ ትምህርት፣ አካል ጉዳተኞችም ሆኑ ጉዳት አልባ ተማሪዎች በአንድ ላይ ምቹ በሆነ ሁኔታና አካባቢ የሚማሩበት ማለት ነው፡፡

ሐ. የአካቶ ትምህርት እሳቤ ያልተወሳሰበና ግልፅ ነው፡፡

መ. በጣም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ህጻናት ለምሳሌ፣ እንደ መስማትና ማየት የተሳናቸው ለብቻቸው በልዩ ትምህርት ቤቶች ወይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ልዩ ክፍሎች ውስጥ መማራቸው ተገቢነት አለው ፡፡

ሠ. የአካቶ ትምህርት አቀራረብ የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማስተናገድ የሚያስችል ነው ፡፡

3. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ፍቺ ስጥ/ጪ ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. አካቶ | ሐ. አውዶች |
| ለ. ፀሐፍት | መ. ማስተናገድ |

4. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀማዊ (አውዳዊ) ፍቺ ስጥ/ጪ።

ሀ. ባሏን በሞት በማጣቷ ምክንያት ማቅ ለብሳ ማቅ መስላ መጣች።

ለ. ከሰው ሰርቆ የደበቀው ዕቃ ስለተጋለጠበት መርበትበት ጀመረ።

ሐ. ማልዶ እንደወጣ አልተመለሰም ።

መ. እጅ ስላጠረኝ ተማሪውን ልጄን አይሆኑ ሆኜ ሸኘሁት።

ሠ. ይህ ሁሉ ምልጃ ለምንድነው? ካልፈለገ ተወው፤ ይሂድ።

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

### ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የራስሽን/ህን የህይወት ታሪክ ትፅፊያለሽ/ትፅፋለህ።
- ስለምታደንቂው/ቀው ሰው የህይወት ታሪክ ፅፈህ/ሽ ታነቢያለሽ/ታነባለህ።
- አንድ ፅሁፍ አንብበሽ/ህ ስለምን፣ ለምን እና እንዴት እንደቀረበ በፅሁፍ ታቀርቢያለሽ/ታቀርባለህ።

### ማስታወሻ፤ የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ

የህይወት ታሪክ በሁለት ይከፈላል። የራስና የግለሰብ የህይወት ታሪክ በመባል ይታወቃል።

1. የራሳችሁን የህይወት ታሪክ ስትጽፉ፦
   - የትውልድ ስፍራችሁንና የትውልድ ዘመናችሁን፣ ስለ አስተዳደጋችሁ ሁኔታና ስለ ትምህርት ህይወታችሁ መጥቀስ፤

- የፈጸማችኋቸውን ጉልህ ተግባሮችንና ያበረከታችሁትን አስተዋጽኦ በቅደም ተከተል መዘርዘር፣ ያይዞም ስለ ስራችሁ ያላችሁን የግል አስተያየት መግለፅ
- ታሪካችሁን ቀላልና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ማቅረብ ያስፈልጋል።

2. የግለሰብ የህይወት ታሪክ ስትፅፉ ደግሞ ቀጥሎ ለቀረቡት ነጥቦች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

   - ታሪኩን ስለምትፅፉለት ግለሰብ የተፃፉ ጽሁፎች ካሉ በማንበብና ግለሰቡን የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ፤
   - የሰበሰባችሁትን የግለሰብ ታሪክ በቅደም ተከተል ማደራጀት ይገባል። ለምሳሌ፣ ግለሰቡ የተወለደበትን፣ ያደገበትንና የሞተበትን (ከሞተ) ቦታና ዘመን በቅደም ተከተል ይገለፃል።
   - ስለ ፈፀማቸው ተግባሮችና ስለ አበረከታቸው አስተዋጽኦዎች ማተት፤
   - ስለ አስደናቂ ስራው ያላችሁን የግል አስተያየት ማከል፤
   - የግለሰቡን ታሪክ ቀላልና ግልፅ በሆነ ቋንቋ መፃፍ እና የማስረጃዎችን ምንጭ በተገቢው ቦታ ከግርጌው መጥቀስ ያስፈልጋል።

1. ከላይ የተሰጠውን የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ በመከተል ስለምታውቀው/ቂው ግለሰብ የህይወት ታሪክ ፅፈህ/ሽ ለክፍሉ በመቅረብ አንብብ/ቢ።
2. ከላይ በቀረበው የራስ የህይወት ታሪክ መመሪያ መሰረት ስለራስህ/ሽ የህይወት ታሪክ ፅፈህ/ሽ አቅርብ/ቢ።

3. ከዚህ በታች አንድ አንቀፅ ቀርቦአል፡፡ አንቀፁን በጥሞና አንብበህ/ሽ ስለ ምን (ይዘት)፣ ለምን (ዓላማ) እና እንዴት (የአፃፃፍ ስልት) እንደቀረበ ተንትነህ/ሽ በፅሁፍ አቅርብ/ቢ፡፡

እዋናው እልፍኝ አንድ የጠፍር አልጋ አለ፡፡ ካልጋው በስተጀርባ እግድግዳው ላይ የሟቹ ባላቸው የተለያዩ እቃዎች ተሰቅለዋል፡፡ በስተቀኝ ግድግዳውን ጥግ ይዞ ባለቤቲቱ ራሳቸው ማታ ማታ ጉርሻ ያስለመዷቸው የፍየልና የበግ ሙክት መታሰሪያ ነው፡፡ ከጠፍሩ አልጋ ትንሽ ራቅ ብሎ፣ ፊት ለፊት ላይ ምድጃ አለ፡፡ በዚህ ክፍል ሆኖ የሚታይ በእበት የተለቀለቀ ሌላ ክፍል አለ፡፡ ይህ ክፍል ዙሪያው መደብ ተሰርቶለታል፡፡ በመደቡ ላይ ነጫጭ አጎዛዎች (የፍየል ወይም የበግ ቆዳ) ጣል ጣል ተደርጎበታል፡፡ በስተግራ ከጠፍር አልጋው ራቅ ብሎ እንደገና አሁንም የግድግዳውን ጥግ ይዞ ጥጃች ታስረዋል ፡፡

*(ዳኛቸው ወርቁ፣ <u>አደፍርስ</u> 1962 ዓ.ም መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)*

# ምዕራፍ አስር

## ስርዓተ ፆታ

### ክፍል አንድ፤ አዳምጦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- እያዳመጥህ/ሽ ፍሬ ሃሳቦችን ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡
- ፅሁፍ ሲነበብልህ/ሽ አዳምጠህ/ሽ ሃሳቡን ትለያለህ/ ትለዪአለሽ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ተግባር

‹‹ፆታና ስርዓተ ፆታ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ መምህርህ/ሽ ከማንበባቸው በፊት ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን መልስ/ሺ፡፡

ሀ. ፆታ ምንድነው?

ለ. ስርዓተ ፆታ ማለት ምን ማለት ነው?

#### ሂደተ ማዳመጥ ተግባር

‹‹ፆታና ስርዓተ ፆታ›› የሚለውን ፅሁፍ መምህርህ/ሽ ሲያነቡልህ/ሽ እያዳመጥህ/ሽ ፍሬ ሃሳቡን ለይተህ ፃፍ/ፊ፡፡

#### ድህረ ማዳመጥ ተግባራት

ከዚህ በታች ያሉ ጥያቄዎች ካዳመጥከው/ሽው ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልስ/ሽ፡፡

ሀ. ፆታ ማለት በተፈጥሮ ወንድ ወይም ሴት ሆኖ መወለድ ማለት ነው፡፡

ለ. በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶችና ወንዶች ያላቸውን ሚናና ግንኙነት የሚያመለክተው ስርዓተ ፆታ ነው፡፡

ሐ. ለስርዓተ ፆታ እድገት ቤተሰብ አስተዋጽኦ የለውም፡፡

መ. ስርዓተ ፆታ እንደ አካባቢው ባህልና አኗኗር መወሰን የለበትም፡፡

ሠ. የሀይማኖት ተቋማት፣ ማህበረሰብና ትምህርት ቤቶች ለስርዓተ ፆታ እድገት አስተዋፅኦ የላቸውም፡፡

## ክፍል ሁለት፤ መናገር

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የዲስኩር ቃላትን ትለያለህ/ትለዩአለሽ፡፡
- የዲስኩር ቃላትን ሚና ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡
- በንግግርህ/ሽ ውስጥ ዲስኩር አመልካቾችን ትጠቀማለህ/ትጠቀሚያለሽ፡፡

### ቅድመ መናገር ተግባር

ቀጥሎ ለንግግር ሃሳብ የሚሰጥህ/ሽን ፅሁፍ ከማንበብህ/ሽ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

1. ዲስኩር የሚል ቃል ሰምተህ/ሽ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ? ሰምተህ/ሽ ከሆነ ምን ማለት ይመስልሃል/ሻል?
2. የሰዎች ንግግር ሊያምርና ስኬታማ ሊሆን የሚችለው በምን ምክንያት ነው?

**ማስታወሻ፤ ዲስኩርና አመልካቾቹ**

- ዲስኩር፣ በቃላዊና በፅሁፋዊ ተግባቦት ውስጥ ሀሳብን የማያያዝ፣ መረጃን የማረጋገጥ ወይም የማፅናት፣ ስሜትን የማጉላትና የመሳሰሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ስነ ልሳናዊ ቅርፆች አገባብና ፍቺ የሚያጠና የስነ ልሳን ዘርፍ ነው፡፡
- የዲስኩር አመልካቾች የሚባሉት ደግሞ፣ በንግግር ወይም

በፅሁፍ ተግባቦት ውስጥ ሃሳብን በማያያዝ ፍሰቱን የሚጠብቁ፣ የሚያጎሉ ወይም የመሳሰሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ቃላት ወይም ሃረጋት ናቸው፡፡

- የንግግር ሆነ የፅሁፍ ሃሳብ የሚያምረውም ሆነ የተሳካ የሚሆነው በነዚህ ዲስኩራዊ ቃላት ነው፡፡ ሃሳብን በየዓይነቱ ማስቀመጡ፣ አንዱን ሃሳብ ከሌላው ጋር ማጣመሩ፣ ጠንከር ላላ የሚደረጉ ሃሳቦችን በወጉ መጠቀም በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ውስጥ ሚናው ትልቅ ነው፡፡
- ዲስኩር አመልካቾች በንግግርም ሆነ በፅሁፍም የሚያገለግሉ ቢሆኑም በዋናነት በንግግር ይዘወተራሉ፡፡ በንግግር ሲሆኑ፣ ከቃላቱና ከሃረጋቱ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ስሜቶችንና ጥያቄዎችን ያካትታሉ፡፡ ስሜቶቹ በቃል ብቻ ሳይሆን አብሮ በድምፅም ይገለፃሉ፤ በንግግር ጊዜ፡፡ አንዳንዴ የጥያቄ ዓይነቶችም የዲስኩር ሚና አላቸው፡፡ በዲስኩራዊ ሚና ጥያቄ ሁልጊዜ መልስ ላይሻ ይችላል፡፡ መልስ የማይሻ ጥያቄ አለ፡፡ እንደዚህ ያለ ጥያቄ ንግግራዊ ሚናው ማለትም ሃሳብን የማስተላለፍ ሚናው የጎላ ነው፡፡
- ዲስኩር አመልካቾች በንግግር ወይም በፅሁፍ ውስጥ የተለያዩ ተግባራት አሏቸው፡፡ የሃሳብን ቅደም ተከተል የማሳየት (አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ በመጀመሪያ… እያሉ)፣ ሃሳብን የማፅናት ማለትም ልክ ወይም ልክ አለመሆኑን የማረጋገጥና የመስማማት (እሺ፣ መልካም፣ ገባኝ … እያሉ)፣ ምክንያትን የማሳየት (በዚህ ምክንያት፣ ስለሆነም፣ በመሆኑም … እያሉ)፣ በሃሳብ ላይ የማከል ወይም የመጨመር (ከዚህም በላይ፣ በተጨማሪም፣ አልፎ ተርፎም … እያሉ)፣ ጊዜን የመጠቀም (አሁን፣ ባለፈው፣ አንድ ቀን …እያሉ) ተግባቦትን ሙሉ የማድረግ ተግባራት አሏቸው፡፡ ሌሎች በርካቶች ተግባራትም ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ልዩነትን ወይም ተቃርኖን ማሳየት (ነገር ግን፣ ዳሩ ግን ...) ዓይነቶች፡፡

ዲስኩር አመልካች ቃላትና ሃረጋት ከሚባሉት መካከል የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ እንችላለን፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| • እንዴ! | ማለቴ | እመነኝ | በዚህ ምክንያት |
| • ለካ እነሆ | መልካም | ነገር ግን | በመጀመሪያ |
| • ማ | እስቲ | በርግጥ | ከዚያ ወዲህ |
| • ም | ታዲያ | በትክክል | በዚህ መሰረት |
| • እሺ | አወይ | አሁንማ | ምንድነው መሰለህ? |
| • እንዴታ! | እፎይ | ምክንያቱም | |

ከነዚህ አንዳንዶቹ ‹‹አያያዥ ቃላት›› በሚል ርዕስ ስር የምናውቃቸው ናቸው፡፡ እነዚያ አያያዥ ብለን የተማርናቸው በተግባቦት ውስጥ ሚናቸው ሃሳብን የማያያዝ ነው፡፡ ሃሳብን ማያያዝ ዲስኩራዊ አገልግሎት ነው፡፡ እንግዲያው፣ ዲስኩር አመልካቾች ያልናቸው በንግግር ወይም በፅሁፍ ውስጥ ተግባቦትን ማራኪና የተሳካ እንዲሆን የምንጠቀማቸው ስነ ልሳናዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## ሂደተ ማንበብ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ፅሁፍ ስታነብ/ቢ ከላይ በማስታወሻው በቀረበው መሰረት ዲስኩራዊ ሚና ያላቸውን ቃላትና ሃረጋትን በደብተርህ/ሽ ላይ እየፃፍህ/ሽ አንብብ/ቢ፡፡

በመንገዱ የሚወጡና የሚወርዱትን መኪናዎች፣ በመንገዱ ግራና ቀኝ በቆሙ አምዶች ላይ ባሉት ትላልቅ አምፑሎች የሚበራውን

የኤሌክትሪክ ብርሃን፣ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚንሸረሸሩትን ሴቶችና ወንዶች፣ ግራና ቀኝ ያሉትን ፎቆችና የቀሩትንም ብዙ ትርዒቶች እየተመለከተች፣ በጥጓ የሚያልፍ እግረኛ ስታገኝ፣ ‹‹ስለ መድሃኒዓለም›› እያለች ትለምናለች፡፡

በሆዷ ውስጥ ሰሚዎችን ሁሉ የሚያስደነግጥ ዜና ያለኝ አደገኛ ፅንስ መኖሬን ግን በጭራሽ ረስታዋለች፡፡ አንድ ሰው በጥጓ ሲያልፍ ስለ መድሃኒዓለም አለችውና ሳንቲም ሰጣት፡፡ ያ ሳንቲም በእጅዋ ላይ ከነበረው ሌላ ሳንቲም ጋር ተጋጭቶ ቅጭል ሲል፣ በሆዷ ውስጥ ከተኛሁበት እንቅልፍ ብንን አልሁ፡፡ ከእንቅልፍ መንቃት ብቻ አይደለም፤ ከድንቁርና ስሜትም ነቃሁ፡፡

ማን እንደሆነ ያላወቅሁት ሃይል ምኞትና ነፃነት ወደሌለበት ዓለም የምሄድ መሆኔን እንዳውቅ አደረገኝ፡፡ ከዚህም በላይ፣ ስንት ስፋትና መጠን ያላት ዓለም አሁን ከምገኝባት ጠባብ ሆድ እጅግ የምታንስ መሆንዋን አሳወቀኝ፡፡ እናማ፣ ሙሉ ነፃነቴን እንደ ያዝሁ ባለሁበት የናቴ ሆድ ውስጥ ፍርግጥግጥ አልሁ፡፡ ሆድዋንም በርግጫ ደበደብሁት፡፡

‹‹አዬ ፍዳዬ! እዚሁ ላይ ደረሰብኝ መሰል! ነገሩማ ወዬት ልደርስ ኖሮአል?›› አለች፣ በቀላሉ የምወለድ መስሏት፡፡

‹በጭራሽ አልወለድም!›› አልሁ፣ በጩኸት፡፡ እሷም ሆዷ እንደተለመደው ጩርር ያለ መስሏት ነበር እንጂ፣ እንደዚህ ያለ በሰው ታሪክ ውስጥ እንግዳ የሆነ ነገር ይሆናል ብላ አልተጠራጠረችም፡፡ በሆድ ውስጥ ሆኖ የሚናገር ህፃን? ማን ሊጠረጥር ይችላል? ለኔም ለራሴ ማመን ይቸግረኛል››፡፡

‹‹እስቲ ለማንኛውም ደህና ቦታ ልያዝ መሰል!›› አለች፣ ከመንገዱ

ዳር ወዳለው የካብ አጥር ስር ጠጋ እያለች፡፡

‹‹በፍፁም አልወለድም!›› አልሁ፣ አሁንም ጮክ ብዬ፡፡ ነገሩ ግራ ሆነባት፡፡ ወዲያና ወዲህ እየዞረች ሰው ማየት ጀመረች፡፡ ከዚያም ቀጥላ፣ ‹‹ወይ ግሩም! ሰይጣን ጠራኝ ልበል?›› አለች፡፡

‹‹አዬ! ደግሞ የምን ሰይጣን? እኔ ነኝ፡፡ አልወለድም!›› አልኳት፡፡ ወደ ሆዷ አንገቷን ዝቅ አደረገችና፣ ‹‹አንተ ማነህ?›› አለች፣ በታላቅ ፍርሃትና ጭንቀት፡፡ እንግዳው ነገር የተሰራው በሆዷ ውስጥ ሆነና የምታመልጥበት ዘዴ ባይኖራት እንጂ በዚህ ጊዜ ልቧ እስኪፈርስ ብትሮጥ በወደደች፡፡

‹‹እኔ በሆድሽ ያለሁት ልጅ ነኝ›› አልኳት፡፡

‹‹እ? ... ምን? ... እ... ታዲያ ለምን አትወለድም?›› አለች፡፡

‹‹ተወልጄ በችግር መሰቃየት አልፈልግም››

‹‹እኔ በተቻለኝ መጠን አሳድግሃለሁ››

‹‹ሊያኖረኝ የሚችል ሃብት አለሽ?››

‹‹እንደዚሁ ለምኜም ቢሆን አሳድግሃለሁ››

‹‹ሞት ይሻለኛል! እኔ ማን መሰልሁሽ አንቺ? ልመናን ተማምኜ ነው የምወለድልሽ? በገዛ ሃገርሽ ላይ የምትችዪውን ሰርተሽ በመኖር ፋንታ እንዴት ልመናን ተስፋ አድርገሽ ትኖሪያለሽ? ያንቺ በዚህ ሁኔታ መጎሳቆል አንሶ ደግሞ ማደጊያ የሌለው ልጅ ለምን ትወልጂያለሽ?››

‹‹ተፈጥሮ ያመጣብኝ ጣጣ ነው እንጂ እኔ ምን አደረግሁ?››

‹‹ተፈጥሮ! ተፈጥሮማ ራስሽን ችለሽ እንድትኖሪ ፈቅዶልሽ ነበር፡፡ ለነገሩማ አንቺ ምን ታደርጊ!. . . የቻልሽውን ያህል ለመስራት ለምን አትሞክሪም?››

‹‹በገረድነት እሰራ ነበር፤ የሳንባ በሽታ አለባት ብሎ ሃኪም ስለተናገረ፣ በሽታው ወደ ጌታዬ ቤተሰቦች እንዳይተላለፍ ወዲያው አስወጡኝ!››

‹‹እሺ መሬት አለሽ?››

‹‹የለኝም››

‹‹ቤት አለሽ?››

‹‹የለኝም››

‹‹ትምህርት አለሽ?››

‹‹የለኝም››

‹‹ታዲያ ምን አለሽ?››

‹‹ምንም የለኝም››

‹‹ታዲያ ድህነትን፣ በሽታንና ድንቁርናን ልታወርሺኝ ነው ተወለድ የምትዪኝ?››

‹‹ዕድልህን እንዴት አውቀዋለሁ፣ ልጄ?›› አለች በትካዜ፡፡

*(አቤ ጉበኛ፣ አልወለድም፣ 7ኛ እትም፣ 2009፣ ገፅ 40-44፣ ጥቂት ዲስኩር አመልካቾች ታክለውበት የተወሰደ)*

### ድህረ ማንበብ ተግባር (ዲስኩራዊ ቃላትን መለየት)

3. ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን ዲስኩራዊ ቃላትን ከመለየት አንፃር ስራ/ሪ፡፡
   ሀ. ከምንባቡ ውስጥ ያገኘሃቸውን/ሻቸውን የዲስኩር አመልካቾችን ዘርዝር/ሪ፡፡
   ለ. በፅሁፉ ውስጥ መልስ የሚሹና መልስ የማይሹ ጥያቄዎችን ለይተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡

ምሳሌ፣

‹‹ነገሩማ ወዴት ልደርስ ኖሯል?›› (አንቀፅ አራት)። የህፃኑ እናት ይህን ስትጠይቅ ከማንም መልስ አትሻም። ለራስዋ ያወራችው ነው። ለመውለድ የምትችልበት ቦታ፣ የምትኖርበት ቤት የሌላት መሆኑን በአንክሮ ያሳያል።

‹‹አንተ ማነህ?›› (አንቀጽ ስምንት)። አሁን ግን የህፃኑ እናት በሆዷ ሆኖ የሚናገረውን ስለምታናግር መልስ ሽታለች (ፈልጋለች)።

1. የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ዲስኩራዊ ቃላትና ሃረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና ተናገር/ሪ።

    - ግን፣ ያ፣ ብቻ (አንቀፅ ሁለት)
    - ከዚህም በላይ፣ እናማ (እና -ማ)፣ ፍርግጥግጥ፣ እንደ (በ‹‹እንደያዝሁ›› ውስጥ ያለው) (አንቀፅ ሶስት)

2. ከላይ የቀረበውን ፅሁፍ ሃሳብ ጠብቀህ/ሽ ዲስኩራዊ አመልካቾችን እየተጠቀምህ/ሽ ንግግር አድርግ/ጊ።
3. የጓደኛህን/ሽን ንግግር አድምጠህ/ሽ በንግግሩ የተጠቀማቸውን ዲስኩር አመልካች ቃላት ተናገር/ሪ።
4. የተጠቀማቸው/የተጠቀመቻቸው ዲስኩራዊ ቃላትና ሃረጋት የንግግሩን መልዕክት በማሳየት ረገድ የነበራቸውን ሚና ተናገር/ሪ።

## ክፍል ሶስት፤ አንብቦ መረዳት

**ከክፍሉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

- የቀረበልህን/ሽን ፅሁፍ አንብበህ/ሽ ይዘቱን ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡
- የቀረበልህን/ሽን ፅሁፍ አንብበህ/ሽ መልዕክቱን ትለያለህ/ትለዪአለሽ፡፡

### ሂደተ ማንበብ ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ፅሁፍ እያነበብህ/ሽ በፅሁፉ ውስጥ የተነሱ ጉዳዮችን (ይዘቶችን) በማስታወሻህ/ሽ ላይ ፃፍ/ፊ፡፡

### ስርዓተ ፆታ

ስርዓተ ፆታ፣ በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ተግባራትን፣ አመለካከቶችንና እምነቶችን ወይም ባህላዊ እሳቤዎችን መሰረት በማድረግ ለወንዶችና ለሴቶች የተሰጡ የስራ ድርሻዎችን ወይም ማህበራዊ ሚናዎችን የሚመለከት ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡

ሰዎች ወደዚህ ዓለም ሲመጡ ሴት ወይም ወንድ ሆነው ይወለዳሉ፡፡ ከዚያም ሴቷ በሴትነቷ ማድረግ ያለባት ተግባር ሁሉ እየተነገራትና በተግባርም እየተማረች ታድጋለች፡፡ እንዲሁም ወንዱ በወንድነቱ ማድረግና መሆን ያለበት ሁሉ እየተነገረው፣ በተግባርም እየተማረና እየሆነ ያድጋል፡፡

ከፍ ሲሉም፣ ከቤተሰብ ውጪ በአካባቢያቸው ያለውን ማህበረሰብ በሚመለከት ለእነርሱ ተገቢና ተስማሚ ነው የተባለውን የተግባር ዓይነት፣ አመለካከትና ሚና እየተገነዘቡ ይሄዳሉ፡፡ በዚህም የተነሳ፣ በስርዓተ ፆታ የሚኖራቸው ሚና ከቤተሰባቸውና ከማህበረሰባቸው በቀሰሙት አስተሳሰብ፣ እምነትና ባህል ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

ይህ ለሴቶችና ለወንዶች በማህበረሰብ ውስጥ የሚሰጠው የስራ ድርሻ ወይም ማህበራዊ ሚና እንደየማህረሰቡና እንደየአካባቢው የተለያየ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ለሴቶችና ለወንዶች ማህበረሰቡ የሚሰጠው ማህበራዊ የስራ ድርሻና ሚና ስርዓተ ፆታ ይባላል፡፡

በእርግጥ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጠው ማህበራዊ የስራ ድርሻ በተወሰነ መልክ ተፈጥሮዋዊ የአካል ልዩነትን የተመረኮዘ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አብዛኛው ማህበረሰብ ለሴቶች ልጅ የማሳደግና የመንከባከብን ሃላፊነት ይሰጣቸዋል፡፡

አንዳንድ የስርዓተ ፆታ ልዩነቶች ግን ተፈጥሮዋዊ ያልሆኑ፣ ነገር ግን በሰዎች የተፈጠሩና ማህበራዊውን ግንኙነት መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በአካላዊ ጥንካሬ፣ በሃብት ልዩነት፣ በእምነትና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ እየተንጠለጠሉ የተፈጠሩ ልዩነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ተፈጥሮዋዊ ባለመሆናቸው በሰዎች ስሜት ላይ ጫና ያሳድራሉ፡፡

*(አቻ ለአቻ ካውንስሊንግና ትምህርት ማኑዋል፤ በደ.ብ.ብ.ህ.ክ.መ.ት.ቢሮ ፣ የካቲት 1999፣ ሃዋሳ፣ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ)*

## ድህረ ማንበብ ተግባር

1. ስርዓተ ፆታ የሚለው ምንባብ ያነሳቸውን አራት ዋና ዋና ነጥቦች (ይዘቶች) ለይተህ/ሽ ፃፍ/ፊ፡፡
2. የፅሁፉ መልዕክት (ለማስተላለፍ የሚፈልገው ቁም ነገር) ምን እንደሆነ ፃፍ/ፊ፡፡

## ክፍል አራት፤ መፃፍ

### ተራኪ ድርሰት መፃፍ

**ከክፍሉ የሚጠበቅ ውጤት**

- ጥሩ ተራኪ ድርሰት ትፅፋለህ/ትፅፊያለሽ፡፡
- የፃፍከ/ሽው ድርሰት ተራኪ መሆኑን የሚያመለክቱ መረጃዎችን አውጥተህ/ሽ ትናገራለህ/ትናገሪያለሽ፡፡

**ማስታወሻ፤ ተራኪ ድርሰት**

- ተራኪ ድርሰት፣ ታሪክ የሚናገር ድርሰት ነው፡፡ የተደረገንና የሆነን ነገር እንዲህ ተደረገ እንዲህም ሆነ እያለ የሚያቀርብ የድርሰት አተራረክ ዓይነት ወይም ስልት ነው፡፡
- ይኸ የሚተርከው ጉዳይ በርግጥ የተደረገና የሆነ ወይም በፀሃፊው ምናብ የተፈጠረ ሊሆን ይችላል፡፡
- ተራኪ ድርሰት ባህርያት አሉት፡፡ አንደኛው፣ በታሪኩ ውስጥ ሰው ወይም ገፀ ባህርይ መኖሩ ነው፡፡ ያ የሚተረክለት አካል ነው፡፡ በዓይነቱ ውስጥ እንደጠቀስነው በቦታና በጊዜ የነበረ ወይም ያለ፣ ከዚህም የተነሳ ሊረጋገጥ የሚችል፣ አሊያም ደግሞ በልቦለድ ዓለም ያለ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላኛው ባህርዩ ታሪኩ በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ ውስጥ የሚከናወን መሆኑ ነው፡፡ ሌላኛው ባህርዩ ቅደም ተከተል ያለው መሆኑ ነው፡፡ የድርጊት፣ የጊዜና ታሪኩ የሚፈፀምበት ቦታ ቅደም ተከተል ይኖረዋል፡፡

1. አንድ ርዕስ መርጠህ/ሽ፣ የአንቀፅ አፃፃፍ ደንብ በተከተለ መልኩ ከሶስት አንቀፆች ባልበለጠ አንድ ተራኪ ድርሰት ፃፍ/ፊ፡፡
2. የፃፍከው/ሽው ድርሰት ተራኪ መሆኑን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ከፅሁፉ ውስጥ በማውጣት ለክፍሉ ተናገር/ሪ፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ሀዋሳ ከተማ አስ.ፋ.አ.ል. (2012) ‹‹ወጣትነትና ሱሰኝነት›› አመታዊ መጽሄት፡፡ ቅጽ1፣ ቁ.2፡፡

ሀይሌ ገብረየሱስ (1994) ‹‹የስነቃል ማስተማሪያ፡፡›› ሀ.መ.ት.ኮ፣ ያልታተመ፡፡

መላኩ ተክሌ (2012፣የካቲት27) ‹‹ስደት ለምኔ?›› አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ቁ.176፡፡

ሺበሺ ለማ (2003) አርአያዎቹ፡፡ አዲስ አበባ፣ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ፡፡

በእውቀቱ ስዩም (2010) ተረቶቻችን፡፡ አዲስ አበባ፣ዜድ.ኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (2004) የልዩ ፍላጎት(አካቶ)ትምህርት ስትራቴጂ፡፡ አዲስ አበባ፣ቢ.ኤስ.ፒ.ኢ፡፡

አምባሳደር ማርቆስ ተክሌ እና ሌሎች (2003) የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባህል፣ ሀዋሳ፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ (1979) የአማርኛ ፈሊጦች፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

አቤ ጉበኛ (2009) አልወለድም፡፡ አዲስ አበባ፣ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ (7ኛ እትም)፡፡

ከበደ ሚካኤል (2007) ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መጽሐፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ (7ኛ እትም)፡፡

-----------------(2007) ታሪክና ምሳሌ 2ኛ መጽሐፍ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ (7ኛ እትም)።

ዘሪሁን አስፋው (1992) የስነጽሁፍ መሰረታውያን። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ስነሕዝብ ጤናና አካባቢ ጥምረት (2006) በሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ ዙሪያ የአየር ንብረት ለውጥ መረጃ፣ አዲስ አበባ። (ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ)።

ደ.ብ.ብ.ሕ.ክ.መ.ት.ቢሮ (1999) ‹‹ስርዓተ ጾታ›› አቻ ለአቻ ካውንስሊንግ ትምህርት ማኑዋል።ሀዋሳ፣ ዛኪ ማተሚያ ቤት።

ደ.ብ.ብ.ሕ.ክ.መ. ገቢዎች ባለስልጣን (2012) ‹‹ግብር (ታክስ)›› አመታዊ መጽሄት። ቅጽ.1 ቁ.6።

ዳኛቸው ወርቁ (1962) አደፍርስ። አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ጉጉ መቻ (2011) የአማርኛ አጋዥ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ።

ጌታሁን አማረ (2007) የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (2011) ‹‹ኤች አይ ቪ እና መተላለፊያ መንገዶቹ›› ኤች አይ ቪ ፕሪቬንሺን ፓኬጅ። አዲስ አበባ፣(ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ)።

ጥላሁን ጣሰው (2007) የመጪው ዘመን ቴክኖሎጂ ኑሮ። አዲስ አበባ፣ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ።